# የኤደን እና የሜላት አማርኛ

ኤደን እና ሜላት ገፀ-ባሕርያት አይደሉም። የዉዱ ልጃችን የኀይሌ ገብረ ሥላሴ ሴት ልጆች እንጂ። የሚያማምሩ ቀያይ፣ ቆንጆ ልጆች ናቸው። በይበልጥ እናታቸውን ይመስላሉ፤ ፈረንጅ አይነት። አማርኛ ይከብዳቸዋል፤ እንግሊዝኛ ይቀናቸዋል።

ኤደንና ቤቲ ታላቅና ታናሽ ናቸው። የ2003 የመስቀል በዓል ሲከበር አባታቸው ሀዋሳ ላይ ባስገነባው አዲሱ ‹‹`ኀይሌ ሪዞርት›› ተገኝተው ነበር። ወላጆቻቸው ዓለም እና ኀይሌም ከጎናቸው ነበሩ። ክብረ-በዓሉ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በቴሌቪዥን እየተላለፈ ነበር።

አንድ ልጅ እግር የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ተጠጋቸው። ‹‹በዓል እንዴት ነው?» ሲልም ጠየቃቸው። ኀይሌ በዓላት ከቤተሰብ ጋር ስለሚከበሩ ልዩ ስሜት እንደሚፈጥሩለት ተናገረ።

ጋዜጠኛው ለዓለምም ተመሳሳይ ጥያቄ ካቀረበ በኋላ ወደነ ኤደን ዞረ። ጥቂት ጥያቄ አቀረበላቸው። አማርኛቸው አላስተማመነውም። ጋዜጠኛው በከፊል አግራሞት ተውጦ ኀይሌን ቃል በቃል እንዲህ ሲል ጠየቀው፡-

« (ልጆችህ) እንግሊዝኛ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፤ አማርኛ ላይ ግን እንዴት ናቸው?።

ኃይሌ ይህን ጥያቄ እንዳልወደደው የፊቱ ገፅታ ያሳብቅበታል።

‹‹ልጆች አማርኛ አትችሉም እንዴ?›› ሲል ወደነ ሜላት ዞሮ ጠየቀ። ኀይሌ በዚያ የዘውትር መልካም ፈገግታው ጥያቄውን ለማስተባበል ሞከረ። ‹‹…ኸረ እንዲያውም ተረት ይነግሩሽል…፣ቅኔም (ይዘርፋሉ!)…›› አለ በራሱ ሳቅ ታጅቦ። ወደ አንደኛዋ ልጁ (ወደ ኤደን ) በመዞር እንዲህ አላት፡-

‹‹ተረት ንገሪው እስኪ…፤ ግን አጭር ቶሎ የሚያልቅ›› አላት።

ልጅቱ ተጣጣረች። ተረት ከየት ይምጣ!?

ምንም አልከሰትልሽ ሲላት እርዳታን በመሻት ወደ እህቷ ዞረች። ሀይሌ ትንሽ በሁኔታው የተደናገጠ መሰለ። እህትየውም ምንም ጠብ አልልሽ አላት። ከብዙ ጭንቀት በኋላ ኤደን አንድ ነገር ተነፈሰች።

‹‹እ…እ…እ….ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ!›› አለች፤የሞት ሞቷን።

ሀይሌ በተፈጠረው ሁኔታ በትንሹ ሳይረብሽ አልቀረም። ኾኖም የዘውትር ፈገግታው አልደበዘዘም።ከአፍታ በኃላ ለጋዜጠኛው እነዚህን የማስተባበያ ቃላት ወረወረ፡-

‹‹…ያው… አየኽ… እንግሊዝኛውን… እኔምልከ…የልጆቼ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሁን ብዬ አይደለም። መሆንም የለበትም፤ አላደርገውምም። ያው ልጆቹ…እዚህ ከኛ ከሁላችንም ጋር ስንገናኝ እንትናቸውን ለማዳበር የሚጠቀሙበት እንጂ…;; (ቃል ቢቃል የተወሰደ)

ኃይሌ እንደገና ልጁን ተጣራ፡-

«ሜላት…አማርኛ አትችይም ማለት ነው?»

ሜላት ደስ በሚል ፈገግታ «እችላለሁ» አለች።

ኃይሌ ቀጠለና እንዲህ አለ፡- « በነገርከ ላይ ይቺ (ሜላትን እየጠቆመ) የኛ አይድል ሾው ላይ ብትቀርብ አንደኛ ምትወጣ ሙዚሺያን ናት።»

ጋዜጠኛው የሆነ ዜማ እንድታቀነቅንለት ጠየቃት።



ኃይሌ ይህን ጊዜ ጣልቃ ገብቶ እንዲህ አለ፡- «ሜላት…which one, which one»

የትኛውን ዘፈን ነው የምትዘፍኚው እያላት ነው፤ የጋዜጠኛውን ጥያቄም እያስተረጎመ ይመስላል።

ቆንጂዬዋ ሜላት አይኗን ወደ ሰማይ አንጋጣ ትንሽ ካሰበች በኃላ፡- በእንግሊዝኛ አንድ ለጊዜው የማን እንደሆን የማላስታውሰውን ዜማ አንጎራጎረች። በእርግጥም ሜላት እንግሊዝኛ ማቀንቀን ትችላለች።

ኃይሌ ትንሽ ልጁ ሜላት እንግሊዝኛ በመዝፈኗ ቅር የተሰኘ ይመስላል። አማርኛ ዝፈኚ እንዳይላት ደግሞ ቋንቋው ከየት ይምጣ። ኃይሌ ተከታዩን ማስተባበያ ከመናገር ውጭ የሚለው ነገር አልነበረም፡-

« ዌል! ልጆቻችንን በተቻለ መጠን ማወቅ ያለባቸውን እናሳውቃቸዋለን። …እምልህ የግድ የዛሬ ስንት ዓመት የኖርንበትን ህይወት እንዲኖሩ አንፈልግም። አሁን ወቅቱ ተቀይሯል። ጊዜው ሁሉ ወደ ዘመናዊነት ነው የሚሄደው። ዘመናዊነት የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ማድረግ አለብን። ዛሬ አይተህ ከሆነ ኮምፒውተሩ ምኑ ያው ያለው በእንግሊዝኛ ነው…ያው… እንግዲህ… ።» (ቃል ቢቃል የተወሰደ)

ኀይሌ በፈገግታው ውስጥ ብዙ ለማስተባበል ሞከረ። ከዚህ ሁሉ ማስተባበያ በኃላ እንኳ የኃይሌ ፊት ቅጭም እንዳለ ነበር።

ከያዘ የማይለቀው ጋዜጠኛ ወደማጠቃለያ ተቃረበ። ማይኩን ወደ ሜላት አስጠግቶ ፡- « እስኪ ሜላት ለኢትዮጵያ ህዝብ በአማርኛ እንኳን አደረሳችሁ፣ መልካም በዓል በይ!» አላት። ሜላት ማይኩን ተቀብላ ያዘች፤ ዘለግ ላለ ሰዓት እያሰበች ቆየች። ጋዜጠኛው ጣልቃ ገባ። «አይዞሽ እንኳን አደረሳችሁ በያቸው»

ሜላት የሞት ሞቷን እንዲህ አለች፡-

መ…ል…ካ…ም NEW YEAR!

## ካ!ካ! አማርኛ!!!

ሞገስ ተፈራ ሁለተኛ ዲግሪውን ከሰራ በኋላ የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነ እንጂ ያለፉትን ዘጠኝ አመታት በግል ትምህርት ቤቶች ነው ያሳለፈው። ‹‹ባሳለፍኩት በእያንዳንዱ የሥራ ዓመት አማርኛ ሞገሷን እያጣች ነበር›› ይላል የሠራባቸውን ዘመናት በምልሰት እያሰበ። እንዲህም ይተርካል።

‹‹የትምህርት ቤቶቹን ስም አልጠቅስልህም። መጀመርያ ተመርቄ እንደወጣሁ ያስተማርኩበት ትምህርት ቤት በግቢው ውስጥ አማርኛ ከተናገርክ በደሞዝህ ፈረድክ ማለት ነው። መምህራን በአንድ ዐረፍተ ነገር 15 ብር ይቀጡ ነበር። ለምሳሌ ረስተህ ‹‹ዳስተሩን አቀብለኝ›› ካልክ 15 ብር ትቀጣለህ። ‹‹ቾክ ረሳሁ›› ካልክ ሌላ 15 ብር። በድምሩ 30 ብር። ስለዚህ ከመናገር ዝምታን ትመርጣለህ። አለዚያ ደሞዝህ ተጎማምዶ ይደርስሃል።››

‹‹ተማሪዎች ደግሞ በየሳምንቱ ‹‹language police››የሚባሉ "ሲቪል" ተማሪዎች ይመደቡባቸዋል። ከዩኒት ሊደሩ ቢሮ። ‹‹ላንጉዌጅ ፖሊሶቹ›› ከራሳቸው ከተማሪዎች የተውጣጡ ናቸው። በእረፍት ሰዓት እየተጫወቱ ድንገት ሲያወሩ አማርኛ የቀላቀሉ ተማሪዎች ስማቸው በእነዚህ የተማሪ ፖሊሶች አማካኝነት ለ‹‹ዩኒት-ሊደሩ›› ቢሮ ይተላለፋል። የተለያዩ ቅጣቶች ይፈፀሙባቸዋል።ከሁሉም የማይረሳኝ ግን አማርኛ ከተናገሩ ‹‹I am stupid›› የሚል ባጅ ለጥፈው እንዲዞሩ የሚደረገው የቅጣት አይነት ነው። በወቅቱ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር በብሪቲሽ ካውንስል ረዘም ላለ ጊዜ አገልግለው በጡረታ የተገለሉ በሳል ሰው ነበሩ። ይህ አይነቱ ቅጣት ካልቆመ ሥራ እለቃለሁ እያሉ የትምህርት ቤቱን ባለቤቶች ሲወተውቱ ትዝ ይለኛል። የትምህርት ቤቱ ባለቤት እና ዘመዳቸው/ዩኒት-ሊደሩ/ ግን በጆ አላሏቸውም። ሆኖም እርሳቸው ከመልቀቃቸው በፊት እኔ ለቀቅኩ። በራሴ ምክንያት ነው ታድያ። አሁን እርሳቸው እዚያ ትምህርት ቤት ይኑሩ ይልቀቁ የማውቀው ነገር የለም። ››

‹‹ከዚያ በኋላ የገባሁበት ትምህርት ቤት በአንዲት ሙስሊም አሜሪካዊት እና /ባሏ ሶማሌ-እንግሊዛዊ ዜግነት ያለው ነው/ የሚተዳደር ሲሆን አብዛኛዎቹ የፓርላማ አባላትና መለስተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ልጆቻቸውን የሚያስተምሩበት ዝነኛ ትምህርት ቤት ነበር።

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ እንቀጥቅጣ ነበር የምትገዛን። ጥሩ ደሞዝ ብትከፍልም ጥብቅ ዲሲፕሊን ታራምድ ነበር። በእርሷ ትምህርት ቤት ውስጥ አማርኛ መናገር ከልክል እንደሆነ የሚያሳዩ ማስታወቂያዎች በቅጥር ግቢዋ በየቦታው በጨርቅ ለጥፋለች። ገና ስቀጠር በተሰጠኝ የትምህርት ቤቱ ህግ እና ደንብ መግለጫ ላይ ከአማርኛ መምህር ውጭ በክፍል ውስጥ አማርኛ መናገር ያለምንም ማስጠንቀቅያ እንደሚያሰባርር የሚገልፅ ዐረፍተ ነገር ተቀምጧል።››

‹‹በእርግጥ ሴትዮዋ በትምህርት ጥራት አትደራደርም። በጣም ምስጉን ተማሪዎችን አፍርታለች። ብዙዎቹ ተማሪዎቿ በእንግሊዝኛ ብቃት እኛ መምህራኖቻቸውን ያስከንዱን ነበር። በዚህም በተማሪዎቿ ብትኮራም በኛ ግን ትበሳጭብን ነበር።››

‹‹ሌላ በስም የማስታውሳቸው ትምህርት ቤቶች አማርኛ የሚናገሩ ተማሪዎችን ፊታቸውን ወደ ግድግዳ አዙረው እንዲቆሙ ያደረጉ ነበር። በአንድ ትምህርት ቤት ደግሞ አንድ የአማርኛ ቃል ተሳስቶ ከፍል ውስጥ የተናገረ ተማሪ አንድ ገፅ ሙሉ ‹‹I am sorry›› እያለ እንዲጽፍና እንዲያስፈርመን ይደረግ ነበር።››

‹‹በአጠቃላይ በብዙ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ትወገዝ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ወላጆችም ይህ በመደረጉ አድናቆት እንጂ ቅሬታ ሲያቀርቡ ሰምቼ አላውቅም። በትርፍ ሰዓቴ ልጆቻቸውን አስጠናላቸው የነበሩ ወላጆች ፊደል ያልቆጠሩ ቢሆንም ልጆቻቸው እንግሊዝኛ እያቻቻሉ እንደሆነ ስነግራቸው ይፈነድቁ ነበር። ሂሳብ እያሻሻሉ ነው ብላቸው ግን እንደዚያ አይፈነድቁም። ‹‹እሱን ይደርስበታል፤ዋናው እንግሊዝኛ ላይ ይበርታልኝ›› ይሉኛል።

‹‹አንዳንዴ ሳስበው ወላጆች ከጎረቤት ጋር ቡና ሲጠጡ በልጆቻቸው እንግሊዝኛ የሚፎካከሩ ይመስለኛል። ‹‹ ልጄ መቼ አማርኛ ትሰማና፣ እንደው ብታይዋት ጉድኮ ናት፤የፈረንጅ አፍ ነው የሚቀናት...›› እያሉ።››

## ፈረንጅኛና ጥቅሙ

አዲስባ ባለፉት አስር አመታት መቶ ሺህ ህፃናትን ወልዳለች፤ መቶ ምናምን አዳዲስ ሰፈሮችን ፈጥራለች። ሺ መዋርያ ቤቶችን ገንብታለች። ይህንንም ተከትሎ በታሪኳ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ብዙ የግል ት/ቤቶች መሽቶ በነጋ ቁጥር በቅለውባታል። ሰፋ ያለ ግቢ ያላቸው መኖርያ ቤቶች ድንገት መዋእለ ህፃናት ሆነው ይነጋል። ትምህርት ቤት መክፈት ኪዮስክ ከመክፈት

ዘለግ ያለ መሰናዶ የሚደረግለት አይመስልም።

ወላጆች ለአብራክ ክፋዮቻቸው ት/ቤቱ ሲመርጡ የቅድሚያ መመዘኛቸው ት/ቤቱ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠው ክብደት ብቻ ነው። ይህን እውነታ የተገነዘቡ አዳዲስ ት/ቤቶች መላ አፈጣጠራቸውን ፈረንጅኛ ለማድረግ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ጥረታቸው የሚጀምረው ደግሞ ለት/ቤት ከሚሰጡት ስያሜ ነው። በአሁኑ ሰዓት በህይወት ካሉ ት/ቤቶች ምሳሌ ብጠቅስ ሙግቴን ያጠናክርልኝ ይሆናል።

‹‹ጊብሰን አካዳሚ፣ ‹‹ስኩል እፍ አሜሪካ አካዳሚ»፣ ‹‹አሜሪካና አካዳሚ» ፣ ‹‹ካምብሪጅ አካዳሚ» ፣ ‹‹ኦክስፎርድ አካዳሚ» ፣«ማክሚላን አካዳሚ» ፣ ‹‹ማጂክ ካርፔት ስኩል»፣ ‹‹ሂል ሳይድ አካዳሚ»፣ ‹‹ብሪቴይን ት/ቤት»፣ ‹‹ሜርሲ አካዳሚ»፣ ‹‹ፓራዳይዝ አካዳሚ»፣ ‹‹ሆራይዝን አካዳሚ ››፣ ‹‹ሲቲ አካዳሚ» ፣«ሰንሻይን አካዳሚ»፣ ...ወዘተ

ት/ቤቶቹ ብዙ ተማሪ እንዲመዘገብላቸው በክረምት ወራት በሚያስለፍፏቸው የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች ውስጥ አንድ ፈረንጅ እንዲታይ ያደርጋሉ።‹‹ይህንን አለማድረግ ከፍተኛ ኪሳራን ያስከትላል›› ይላል በተለያዩ የግል ት/ቤቶች ለዘጠኝ አመት በመምህርነት የሰራው አቶ ሞገስ። እርሱ እንደሚለው ምስላቸው በቴሌቪዥን እንዲታይ የሚደረጉት ፈረንጆች እንዳንዴ ለማስታወቅያው ብቻ በኪራይ መልክ የሚመጡበት አጋጣሚ አለ። ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት በሚያመጡበት ሰዓትና ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት በሚወስዱበት ሰዓት እነዚህ ፈረንጆች በር ላይ ሆነው የማስተባበር ግዴታ ይጣልባቸዋል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያነጋገረው አንድ መምህር በአንድ ወቅት ባስተማረበት የግል ት/ቤት የነበረ ጃማይካዊ ወላጆች በሚገኙበት ሰዓት ከፈረንጅ መምህራን ኋላ እንዲሆን በትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች ስለተነገረው ከፍተኛ ቅሬታ ተፈጥሮበት ት/ቤቱን መልቀቁን ያስታውሳል።

ለግል ት/ቤቶች የፈረንጅ ምስል የህልውና ጉዳይ ነው። በጉልህ የሚታየው የደሞዝ ልዩነትም ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው። አንድ በግል ት/ቤት የሚገኝ ምንም አይነት ዲፕሎማም ሆነ ዲግሪ የሌለው ፈረንጅ የቆዳ ቀለሙ ነጭ በመሆኑ ብቻ ማስተርስ ካለው ኢትዮጵያዊ በአምስት እጥፍ የበለጠ ደሞዝ ያገኛል። የአንድ ፈረንጅ አማካይ ደሞዝ ከ 5-11 ሺ የኢትዮጵያ ብር ይደርሳል። በአንጻሩ ሁለተኛ ዲግሪና ረዥም የስራ ልምድ ያለው ኢትዮጵያዊ መምህር 3 ሺ ብር የከፍያ ጣርያው ነው።

በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ከፈረንጆች ቀጥሎ ጥሩ ክፍያ የሚያገኙት ህንዶች፣ ጃማይካዎችና ሌሎች የአፍሪካ ዜግነት ያላቸው መምህራን ናቸው። ሆኖም በስደት ወደ ሶስተኛ አገር ለመሄድ አዲስ አበባ የሚኖሩ አፍሪካውያን በ‹‹ሀበሻ›› ደሞዝ ሊቀጠሩ ይችላሉ።

## Amharo-phobia

በግል ት/ቤት የሚማሩ ልጆች ጠጠር ያሉ የአማርኛ ቃላትን አይረዱም። ለምሳሌ ‹‹እርሻ ለአንድ አገር እድገት ይበጃል›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹ይበጃል›› የሚለው ቃል ግር የሚላቸው የ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ያጋጥማሉ። የአማርኛዋን «ቀ» ፊደል የማያውቁ ጎረምሳ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ማግኘት ብርቅ አይደለም። አንድ የአማርኛ መምህር «ቀ»ፊደልን እንዳይረሷት «እስከስታ ሲመታ» እያልኩ አስረዳቸዋለሁ ብሎኝ ያውቃል። ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች። የአማርኛ ዲቃላ ፊደላት ለነዚህ ተማሪዎች የፊዚክስ ያህል ይከብዷቸዋል። ለአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሚሰጠው ክብርና ዋጋም በግል ት/ቤቶች የወረደ ነው። ለምሳሌ ፈተና እየተቃረበ ሲመጣ ተማሪዎች የስፖርትና የአማርኛ ክፍለጊዜዎች ታጥፈው በነርሱ ምትክ እንግሊዝኛን እንዲያጠኑ ይደረጋል።

የግል ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን ትቢያ ለማድረግ የዘየዱት ሌላኛው መንገድ በቅጥር ግቢያቸው አማርኛ መናገር ነውር እንደሆነ ማወጅን ነው። ከጥቁር ሰሌዳው ጎን በጉልህ ‹‹በአማርኛ መናገር ፈፅሞ የተከለከለ ነው›› የሚል ማስታወቅያ ይሰቅላሉ። አማርኛ መምህራንም ቢሆን ከክፍላቸው ውጭ በእንግሊዝኛ ብቻ እንዲነጋገሩ ይገደዳሉ።

‹‹ኢትዮጲካሊንክ›› የተሰኘ የሬድዮ ፕሮግራም በአንድ ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ባቀረበው ዳሰሳ ‹‹አማርኛ መናገርና ድንጋይ መወርወር ክልክል ነው›› የሚል ማስታወቅያ በአንድ የግል ትምህርት ቤት ተሰቅሎ ማየቱን ዘግቧል።

በግል ት/ቤቶች መምህራን ተማሪዎችን በፍፁም አካላዊ ቅጣት መቅጣት አይፈቀድላቸውም። በመሆኑም አማርኛ የሚናገሩ ህፃናት ፊታቸውን ወደ ግድግዳ አዙረው ለተወሰኑ ሰአታት እንዲቆሙ ይደረጋል። ይህ ከፍተኛው የቅጣት አይነት ነው። እኔ በተማርኩባቸው የመንግስት ት/ቤቶች ጆሮ መያዝ፣ እስከሪብቶ በሁለት መሀል ጣቶች ከትቶ መጭመቅ፣ በማስመሪያ

# በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንስ ከተማ

«ሰላም ባስ» ወደ መቀሌ በየዕለቱ በረራ ካላቸው አገር አቋራጭ አውቶቡሶች መካከል ግንባር ቀደሙ ነው። መነሻውን ከመስቀል አደባባይ አድርጎ የደሴን፣ የሐይቅን እና የወልዲያን ከተሞች አቋርጦ በአላማጣ እና በማይጨው ጋራዎች ሰንጥቅ መቀሌ ለመግባት ሁለት ቀናት ይወስድበታል። ይህን አድካሚ ጉዞ ቀላል ለማድረግ «ሰላም ባስ» ተንቀሳቃሽ ፍሪጅ፣ የሙቀት መቆጣጠሪያ እና የጥንቃቄ ቀበቶ ለተሳፋሪዎቹ አዘጋጅቷል። ከዚህም ባሻገር በውስጡ ሁለት የማይታክቱ የቴሌቪዥን ስክሪኖች ተገጥመውለታል። ቴሌቪዥኖቹ ከተጨቆኑ ቀልዶች አንስተው ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ውዳሴ እስከተዜሙ የትግርኛ ዜማዎች ድረስ ተሳፋሪዎቻቸውን ያስኮመኩማሉ። በዚህ የ780 ኪሎ ሜትር የመቀሌ ጉዞ ተጓዡ ከቴሌቪዥኖቹ በብዛት እንዲኮመኩም የሚጋበዘው ግን የኤርትራ ሙዚቃዎችን ነው።

በአመዛኙ በኤርትራ ሙዚቃዎች የሚታጀበው የሁለት ቀናት ጉዞ ሲጠናቀቅም ቢኾን ዉዷ መቀሌ የራሷን ዜማዎች አሰናድታ አትጠብቅም፤ ይባስ ብላ እሷም በኤርትራ ቅኝት ያሰዐረፍት ትደንሳለች።

ይህ ኹኔታ አሥመራ ተወልዶ ላደገው ጸጋዬ ገብረ ትንሣኤ የፈጠረበት ስሜት ከአግራሞትም በላይ ነው። ለ23 ዓመታት በኤርትራ ሲኖር ራሱን ከሙዚቃ ነጥሎ አያውቅም። ከሁለቱ

ጎረቤት አገራት የከረረ ጦርነት በኃላ ግን ኢትዮጵያዊ የትግርኛ ሙዚቃዎችን በአሥመራ ሊሰማቸው አልታደለም ነበር። በኤርትራ የኢትዮጵያ ሙዚቃዎችን በይፋ መስማት ክልክል መኾኑን የሚናገረው ጸጋዬ ከሦስት ዓመታት በኃላ በቀይ መስቀል እርዳታ ለእናቱ አገሩ ሲቢቃ ተመሳሳይ ኹኔታ እንደሚያጋጥመው እርግጠኛ ነበር። ኾኖም መቀሌ ከተማ ሲደርስ ያጋጠመው የተገላቢጦሹ ነው።

ጸጋዬ « እርነት እና ሰማዕታት» በሚባሉት የአሥመራ ጎዳናዎች ዘወትር የሚንቆረቆሩት የኤርትራ ዜማዎች « የጠላት አገር» ተብላ በምትፈረጀው መቀሌ አሁንም አሁንም በየሄደበት ሁሉ ሲደመጡ ያሰበትን እስኪጠራጠር ድረስ ተገርሟል። ጸጋየ ግርምቱን «‹ ዘይሕሰብ ነገር!» በማለት ነው የሚገልፀው።።‹ የማይታሰብ ነገር!»

ከኢትዮጵያ ታላላቅ ከተሞች ተርታ የምትመደበው መቀሌ በቅርቡ ይፋ በኾነው የሕዝብ ቆጠራ መሠረት 215 ሺህ ነዋሪዎችን ታቅፋለች። መቀሌ ከአቻ የኢትዮጵያ ከተሞች የምትለይበት አንዱ ምክንያት ግልጽ ባልኾነ ኹኔታ እስከዛሬም ለኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያ አለመታደሏ ነው። በክልሉ ራሱን «የግል ሬዲዩ ጣብያ» እያለ የሚጠራው « ድምፀ ወያኔ» የሚያስተላልፋቸው ፕሮግራሞች ብቻ የሚደመጡ ሲኾን የኢትዮጵያ ሬዲዮ እስከ አሁንም በጥራት በከተማዋ የመሰማት አቅም አላገኘም። እነዚህ ሁሉ ተደማምረው መቀሌን ያረመመች ከተማ አስመስለዋታል።

ይኹን እንጂ በዛ ካሉ መዝናኛ ሥፍራዎቿ በሁሉም አቅጣጫ የሚሰሙት በከበሮ የደመቁ ሙዚቃዎች ከተማዋን ያለ ዕረፍት ያስደንሷታል፤ይንጧታል። ምንም እንኳ የብዙዎቹ ቅኝትና ምንጭ ከኤርትራ ቢኾንም።

በከተማዋ ዘመናዊ የምሽት ክበቦች ውስጥ አንዱ በኾነው «ክለብ አቢሲኒያ» ሙዚቃ የሚያጫውተው «ዲጄ» አማኑኤል በከተማዋ ስም ካላቸው የሙዚቃ አጫዋቾች አንዱ ነው። ዐማኑኤል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እና በየምሽቱ ከሚያጫውታቸው ሙዚቃዎች በአማካይ 90 ከመቶ የሚኾኑት የኤርትራ ሙዚቃዎች እንደኾኑ ይናገራል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ ኹኔታ የተወሰነ መሻሻል እያሳየ እንደ ኾነ ያስባል። « በአንድ ምሽት እስከ አምስት የሚደርሱ የእኛን አገር የትግርኛ ሙዚቃዎች ለመቀላቀል እሞክራለኹ።» ይላል አማኑኤል።

ዲጄ ዐማኑኤል በከተማዋ ያለው የኤርትራ የሙዚቃ የበላይነት በሙዚቃ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን ይገልጻል። እርሱ በንብረትነት የሚያስተዳድረው የቪሲዲ ማከራያ እና ማከፋፈያ ማዕከል ብዙዎቹ ደንበኞች የሚፈልጉት ከትግርኛ ሥራዎች ይልቅ የኤርትራ ድራማዎችን እና ፊልሞችን ነው።

በመቀሌ ከተማ ያሉት የሙዚቃ ቤቶች ከዐማኑኤል ሐሳብ ጋር የሚጣጣም ሥራ የሚሰሩ መኾናቸውን የሚመሰክር የራሳቸው የዕለት ዕለት ትዕይንት ይስተዋልባቸዋል። ብዙ መደብሮች « አዲስ የኤርትራ ድራማዎች አስገብተናል» የሚሉ ማስታወቂያዎችን ከደጃቻቸው ያስደምጣሉ፤ የውስጠኛው ገጽታቸውም ይህንኑ እውነታ በሚያዉጁ ማስታወቂያዎች የተሞላ ነው።

የከተማዋ ሰፋፊ ከፊቴሪያዎች እና ድራፍት ቤቶችም በየሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ደንበኞቻቸውን የሚያስኮመኩሙት ከኤርትራ የሚሠራጨውን «ሞይዛክ» የተሰኘውን የሙሉቀን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነው። በእነዚህ ቀናት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሥርጭቶቹን የሚያስተናግድ ካፌ ማግኘት አዳጋች ነው።

ከዓመታት በፊት በኤርትራ ቴሌቪዥን ዘወትር ዐርብ እና እሁድ ይተላለፍ የነበረው ተከታታይ ድራማ የከተማዋን ነዋሪ ቀልብ ገዝቶ ነበር። ይህ «ዝባን ሕጊ» (በህግ እምላክ እንደማለት ነው) የተሰኘው ተከታታይ ድራማ ይቀርብ በነበረበት ወቅት ብዙዎቹ የከተማዋ መዝናኛ ቤቶች በተመልካች ይጨናነቃሉ። አንዳንዶቹም ድራማው በሚታይበት ወቅት ለሚሰጡት ማንኛውም አገልግሎት ተጨማሪ ክፍያን ይጠይቁ ነበር። «ዝባን ሕጊ» የከተማችን ፕሪምየር ሊግ ኾኖ ቆይቶ ነበር» ይላል በወቅቱ የነበረውን ኹኔታ የሚያስታውሰው የከተማዋ ነዋሪ እታኸልቲ ገብረ ሕይወት።

የመቀሌ የቪሲዲ ማከራያ መደብሮችም ቢኾን ከአገር ውስጥ የትግርኛ ሙዚቃዎች እና ሌሎች የጥበብ ሥራዎች ይልቅ በኤርትራ ፊልሞች እና የሙዚቃ ክሊፖች የተሞሉ ናቸው። ከኤርትራ ቴሌቪዥን እየተቀዱ በሲዲ ተዘጋጅተው በመላው ትግራይ በሺዎች የሚሰራጩት እነዚህ ልዩ ልዩ የጥበብ ሥራዎች መቀሌን እምብርታቸው ያደረጓት ይመስላሉ። ዐማኑኤል « የኤርትራ ‹MP3ዎች እና የዘፈን ክሊፖች ከአዲስ አበባ ጭምር እየተዘጋጁ ወደ መቀሌ ይላካሉ» ይላል በመደብሩ የ«ሳየንስ» እና የ«ሊቫንጋዲ» ሪከርድስ ዓርማን የያዙ ብዛት ያላቸው ሲዲዎችን

እያመለከተ። እንደ አማኑኤል ገለጻ ትልልቅ አሳታሚዎች ጭምር በዚህ ዘርፍ መሠማራታቸው የኤርትራ ሙዚቃዎች በክልሉ ያላቸውን የገበያ ስፋት እና ተቀባይነት የሚያሳይ ነው።

የመቀሌ ነዋሪ የኾነው አታኽልቲ የኤርትራ ሙዚቃ ለትግራይ ሕዝብ ባለው የቋንቋ ቅርበት ምክንያት ተቀባይነት እንዳገኘ ይገምታል። «ሙዚቃ ድንበር የለውም» የሚለው አታኽልቲ አንድ በነበሩ ሕዝቦች መካከል ይህን ያህል መወራረስ መከሠቱ አስገራም እንዳልኾነ ያምናል። ከሙዚቃ እና ድራማዎች ባሻገር የኤርትራውያን የኾኑ ቃላትም ሰርገው እንደገቡ አታኽልቲ እንደማስረጃ ያቀርባል። እንደ ምሳሌም አሁን አሁን በመቀሌ እና አካባቢዋ እየተዘወተሩ የመጡ ቃላትን ይጠቅሳል። «ኣይደል?» ለማለት «ሙሽ?»፣ «እሺ» ለማለት ደግሞ «ሃራይ»... ወዘተ የእኛ ትግርኛ ያልኾኑ ነገር ግን አሁን በስፋት የተለመዱ ውርስ ቃላት ናቸው።»

የኤርትራ ኮከብ ድምፃዊ የነበረው አብረሃም አፈ ወርቂ ድንገተኛ ሞት ከሁለት ዓመታት በፊት ሲሰማ በመቀሌ ትልቅ መነጋገርያ እንደ ነበር የሚያስታውሰው አታኽልቲ ይህም የሕዝቦቹን ትስስር አጉልቶ የሚያሳይ እንደ ኾነ ይሞግታል።

23 ዓመታትን በአሥመራ ቆይታ ያደረገው ጸጋዬ ገብረ ትንሣኤ የግጥም እና የዜማ ደራሲ ነው። ሥራዎቹን ሰማቸው ጎልተው ለሚወሱ የኤርትራ ድምፃውያን አበርክቷል። እንደ እርሱ አመለካከት የትግርኛ ዘፈኖቻችን ከኤርትራ ሙዚቃዎች የማይተናነስ አቅም አላቸው። « ችግሩ በስፋት ለመደመጥ ቦታ አለማግኘታቸው ነው» ባይ ነው።

ጸጋዬ በኤርትራ ቆይታው የአብረሃም ገብረ መድኅንን « ምግበይ» የተሰኘውን አልበም ከእንግሊዝ አስመጥቶ አሥመራ ውስጥ ለማሰራጨት ቀዳሚ እንደ ነበር ይናገራል። ያን ጊዜ የሙዚቃውን ከፍተኛ ጥራት እና ተቀባይነት ተከትሎ ሰዎች ድምፃዊው «ኤርትራዊ ልጃችን ነው» በማለት እስከ መከራከር ደርሰው እንደነበር ይተርካል። «ይህ የሚያሳየው እነርሱ እኛ ፍጹም ሙዚቃ እንደማንችል አድርገው እንደሚያስቡን ነው።»

የትርሃስ ታረቀኝን « ኮበለይ» የተሰኘውን ተደማጭ ሙዚቃ የስቱዲዮ ቀረጻ እና የድምጽ ተዋሕዶ (ሚክሲንግ) ሥራ የሠራው ፍቅረ ተሾመ በበኩሉ የትግርኛ ሙዚቃ አቀናባሪ ነው። እንደ እርሱ አመለካከት ይህ በክልሉ የሚታየው የኤርትራውያን የሙዚቃ የበላይነት ከአሁን በኋላ ብዙ አይቀጥልም። ፍቅረ «ተስፋ የሚጣልባቸው ዕምቅ አቅም ያላቸው ዘመናዊ ትግርኛ ሙዚቃ መጫወት የሚችሉ ወጣቶች ብቅ እያሉ ነው» ይላል። ኾኖም በኅብረተሰቡ ውስጥ የሠረጸው የኤርትራ ሙዚቃን አልቆ የማየት አባዜ ፍቅረን ያንገበግበዋል። ሰው አሪፍ የትግርኛ ሙዚቃ ሠርተን እንኳ የሚያደንቅልን «ቁጭ የኤርትራ ዘፈን ነው የሚመስለው'ኮ በማለት ነው»። ይላል በቁጭት።

ለዓመታት በዲጄነት ቆይታ ያደረገው ዲጄ ዐማኑኤል በዚህ ይስማማል፤ « አገር ውስጥ ጥሩ ጥሩ የትግርኛ ዘፈኖች ተሠርተው የኤርትራ ባለመኾናቸው ብቻ ተውጠው ይቀራሉ።»

ዲጄ ዐማኑኤል በሚያዘጋጃቸው ‹፣የ«ዴይ ፓርቲዎች»ም ኾነ በምሽት ክበቦች ታዳሚዎቹ የኤርትራ ሙዚቃን እንዲጋብዛቸው አስጨንቀው እንደሚጠይቁት ይናገራል።«ሰውን የምታዝናናው በሚወደው ሙዚቃ ነው፤ በግድ የእኛን ስማ ብለኽ አትግተውም» ይላል የኤርትራ ሙዚቃዎች በነዋሪዎቹ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ሲያብራራ።

ዲጄ ዐማኑኤል የኤርትራ ሙዚቃዎች በከተማዋ እንዲህ ሥር መስደድ እንደ ዐቢይ ምክንያት የሚያነሣው የእኛ የትግርኛ ዘፋኞች አዲስ እና ያልተለመደ ሥራን ይዘው ለመቅረብ አለመድፈራቸውን ነው። « የእኛዎቹ ሥራዎች በባህል የተደረቱ እና የትግል ዜማዎች የሚበዙባቸው ናቸው።»

የትግርኛ ሙዚቃ አቀናባሪው ፍቅረም ኾነ ዲጄ ዐማኑኤል የሚስማሙበት ነጥብ በከተማዋ የጥበብ ሥራን ሊያሳድግ የሚችል ሚዲያ አለመኖሩ ለሙዚቃው መርገምት መኾኑን ነው። ዐማኑኤል « ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ቢኖር አዲስ አቅም ያላቸው ሙዚቀኞች የመደመጥ ዕድል ይኖራቸው ነበር» ይላል በቁጭት።

የ«ሱዳን ትሪቡን» ድረ ገጽ ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከጦርነት መልስ ለመጀመርያ ጊዜ የኤርትራ ሙዚቃዎችን ማሳየት መጀመሩን ትልቅ ዜና አድርጎ ዘግቦታል። መቀሌን አላያትም ማለት ነው። በእርግጥም መቀሌ በኤርትራ ሙዚቃ ደንሳ የምትደከም አትመስልም። ሙዚቃ ጦርነት አይገባውም እንዴ?

---

*©ይህ ፅሁፍ በጥር 2፤2001 በወጣው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ሰሻል አምድ ላይ ታትሞ እንደነበረ ይታወሳል፡ ፡ በፈረንጆች 2009 የውጭ ሚዲያ ወኪል ጋዜጠኞች ማህበር ከአሜሪካና ፈረንሳይ ኤምባሲዎች ጋር በመተባበር ባዘጋጀው የሚዲያ ፅሁፍ ውድድር በጋዜጣ ዘርፍ ተሸላሚ ፅሁፍ ነበር፡፡*

# የወሲብ ፊልሞች ሊግ

በከተማችን ያሉ፣ የሚደረጉ ግን ደግሞ የሌሉ የማይደረጉ የሚመስሉን ተቃርኖዎች ሞልተዋል። የልቅ ወሲብ ፊልሞች ዝውውር ከእነዚህ ጉዳዮች ይደመራል። መሐመድ ሰልማን ከመርካቶ እስከ ቦሌ፣ ከ«ሕሪ በከንቱ» እስከ «ዶሮ ማነቂያ»፣ ከ«ምናለሽ ተራ» እስከ

«ሰባተኛ» ያሉ የወሲብ ዝውውሮችን ሰንሰለት ይፈትሻል።

---

ይህ « ዶሮ ማነቂያ» ነው። የ« ዶሮ ማነቂያ» መንገዶች የሚተናነቁት ደግሞ ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ነው። ጫት የሚቅሙ እና የሚያስቅሙ፣ ቁርጥ የሚቆርጡ እና የሚያስቆርጡ፣ ወሲብ የሚያዩ እና የሚያሳዩ፣ ሁሉም ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ያነጋሉ። አንገቶቻቸውንም ቀና ያደርጋሉ።

እነ «ሕልማዜ ቤት»ም ሁሌ ጊዜ ከምሽቱ 12:30 « የወሲብ ሊግ» ፍጥጫው ያይላል። የሊጉ ቋሚ ተመልካቾችም ወደዚህ ስቴዲየም የሚተሙት ሰዓት ሳያዛንፉ ነው። የሙሉ ልብስ

ማሳመሪያ ክራቫት እያላሉ ከመሥሪያ ቤት በቀጥታ ወደዚህ «ስቴዲየም» የሚታደሙ ብዙ ናቸው። የጋብቻ ቀለበታቸው በከፊል ጨለማ ውስጥ እያብረቀረቀ ሚስት እና ልጃቸውን እንኳ ሳይሰሙ ይህን ቤት የሚሳለሙ ቁጥራቸው የዋዛ አይደለም።

በዚያች ቤት በአግዳሚ ወንበር በግምት 60 የሚኾኑ ታዳሚዎች በጉጉት የሕንቅ ተይዘዋል። የቤቱ ባለቤት የኾኑት ወይዘሮ የ30 ደቂቃ የልቅ ወሲብ ለማየት የሚያስችል ትኬት በአንድ ብር ያድላሉ። የቤቱ ግድግዳዎች በአውሮፓ ታላላቅ ቡድኖች ፎቶ ግራፍ ቢለበጡም ፊት ለፊት ከተደቀነው ቴሌቭዥን የሚታየው ግን የወሲብ ጥሎ ማለፍ ነው። በዚህ ቤት ስሜት እንጂ ጨዋነት የለም። የወሲብ ኀል ሲቆጠርም ቢኾን ትንፍሽ የሚል አይገኝም። ኹሉም ተመልካች «ሰው እንስሳ እንደኾነ» የሚያስረግጥ የሚመስለውን ፊልም ይመለከታል። አንድ ከጎልማሳነት እየተላለፉ የሚመስሉ ግለሰብ የሚታየውን የልቅ ወሲብ በሞባይላቸው ቀርጸው ለማስቀረት ከቴሌቪዥኑ ሥር አድፍጠዋል። ከዐሥር ደቂቃ በላይ በሞባይላቸው መሥሉን ለማስቀረት ተጉ።

ከቴሌቭዥን የሚታየው ነገር የሚታይ እንጂ የሚጻፍም፣ የሚነገርም አይደለም። ሰው እንደበሬ፣እንደ ፈረስ እና እንደ ውሻ ይዋሰባል። በቪዲዮ ቤቱ የሚሰማው ድምጽም በሚያቃስቱ ሴቶች እና በሚያጓሩ ወንዶች የተሞላ ነው። ያዩትን ወደ ተግባር መለወጥ የሚችሉት ዕድላቸውን ለመሞከር ሹልክ እያሉ ይወጣሉ። እነዚህ ጥድፊያው አላስቆም አላስቀምጥ ያላቸው ናቸው። ይህ ያልኾነላቸው ደግሞ ጣጣቸውን እዚያው ለመጨረስ እጃቸውን ወደ ወንድነታቸው እየሰደዱ ይታሻሉ። ጥቂቶች በበቃኝ ቤቱን ለቀውት ውልቅ ቢሉም የወሲብ ሊጉ ግን አይቋረጥም። 1፡30 ሰዓት ላይ የሊጉ ሁለተኛው ጨዋታ ይቀጥላል። ሁለተኛውን ጫወታ ማየት የፈለገ ከአልማዝ ሌላ ትኬት መቁረጥ ይኖርበታል።ሌላ ውጥረት፣ ሌላ ሲቃ፣ ሌላ ጡዘት... ።

## የአንትን ፊልም ይናርኻል?

የልቅ ወሲብ ፊልሞችን ለመጀመርያ ጊዜ የሚመለከት ሰው «ወደ ላይ» የሚልበት ከጭኖቹ መሀል ብቻ ሳይኾን ከጉሮሮውም ጭምር ነው። እያንዳንዱ ትዕይንት የማቅለሽለሽ ስሜትን ይፈጥራል። በልቅ ወሲብ ፊልሞች ውስጥ ምድር ለወሲብ ብቻ የተፈጠረች ይመስላል። አማዞን

ጫካ፣ የዐረብ በረሃዎች፣ቋጥኝ ሥር፣ አሳንሰር ውስጥ፣ጋራዥ ቤት፣መኪና ማቆሚያ፣ የመኪና ኮፈን፣ የመኪና ወንበር፣ ሣር፣ አስፋልት፣ ደረጃ አልፎ አለፎ ደግሞ አልጋ ላይ ልቅ ወሲብ ሲፈፀም ያሳያሉ። የእነዚህ ፊልሞች ኹሉ መድረሻ ግን መኝታ ቤት ገብቶ፣ አልጋ ላይ ወጥቶ፣ አንሶላ እና ብርድ ልብስ ደርቦ መስኮት እና በር ቆልፎ እንደገናም ደግሞ መብራት አጥፍቶ ካልኾነ በቀር ፍቅር መሥራት የማይኾንለት ኢትዮጵያዊ ዘንድ ነው።

በግል የንግድ ሥራ የሚተዳደረው ፈቃዱ አየለ (ስሙ የተቀየረ) እንደ እነዚህ ያሉ ልቅ የወሲብ ፊልሞችን በማየት ሱሰ ከተጠመዱት ጎልማሶች ይመደባል። ከመዋዕለ ሕፃናት በላይ ቪዲዮ ቤቶች በበዙበት አዲስ ከተማ የተወለደው ፈቃዱ ተንከባክበው ያሳደጉትን መዓተኛ ቪዲዮ ቤቶች አይረሳቸውም። «32 ቀበሌ፣ መርካቶ 18 ቀበሌ ድል በትግል አዳራሽ፣ 31 ቀበሌ ...» እያለ ቆጥሮ አይዘልቃቸውም። በተለይ 18 ቀበሌ የነበሩ ቪዲዮ ቤቶች ከአእምሮው አይጠፉም። ከእነዚህ ቤቶች ደጅ ወጥተው «ስፔሻል አንድ ብር፣ አንድ አንድ ብር ስፔሻል!» እያሉ መንገደኛውን የሚጠሩ የወሲብ ቤት «ወያላዎች» እንደነበሩ አይረሳውም። ቪዲዮ ቤቶቹ ሲሞሉም ከደጅ ኾኖ በቀዳዳ አጮልቆ ለማየት 50 ሳንቲም መክፈል ግዴታ ነበር። ዛሬ ፈቃዱ «ስፔሻል ቤት» ገብቶ ለመታደም ክብሩ አይፈቅድለትም። ፊልሞቹም ቢኾኑ ወደ እርሱ ይመጣሉ እንጂ እርሱ ወደ እነርሱ አይሄድም።

## የወሲብ <<ሲራራ ነጋዴዎች>>

ደሳለኝ ከመጻሕፍት አዟሪነት ወደ ሲዲ አዟሪነት የተሸጋገረው ከዓመት በፊት ነው። እንደ ሲራራ ነጋዴ ቀን እና ምሽት ኪሎ ሜትሮችን እየተጓዘ እና በየመዝናኛ ቤቶች እየዘለቀ የግዙኝ ልምምጡን ሲያቀርብ አይታከተውም። በመዳፉ አምስት የሚኾኑ መዝሙር እና ሌሎች አዳዲስ የኮሜዲ ቅጂ ሲዲዎችን ይዟል። በእጁ ከሚይዛቸው አዳዲስ ሲዲዎች በላይ ግን ለእርሱ በልቶ ማደር ምስጢር የኾኑትን ሲዲዎች የሚይዛቸው ጀርባው ባዘለው ሻንጣ ውስጥ ባለች ሌላ ትንሽ ሻንጣ ውስጥ ነው። ደሳለኝ የትኞቹ ደንበኞቹ ምን እንደሚፈልጉ ጠንቅቆ ያውቃል፣ ይረዳል። « የአንትን ሲዲ አለህ?» የሚሉትን አዳዲስ ደንበኞቹንም ሳያሳፍራቸው የሚፈልጉትን ያቀብላቸዋል፤ እጁን ከሻንጣው ውስጥ ወዳለችው ትንሽ ሻንጣ በመስደድ።

ከመጻሕፍት ወደ ሲዲ አዟሪነት «ያደገው» ደሳለኝ በገቢ ደረጃ ሲዲ መሸጥ የተሻለ እንደኾነ አስረግጦ ይናገራል። « መጻሕፍት እጅህ ላይ ይቆሸሻል፣ በዚያ ላይ ሰው አይገዛህም፣ ሲዲ ግን

ቢያንስ አንድ «ፒቢ» (የወሲብ ፊልም) ሳትሸጥ አታድርም።»

በቀድሞ ጊዜ በዴክ ካሴት(VHS) ብቻ ይቀርቡ የነበሩት እነዚህ ፊልሞች ዛሬ በዲቪዲ በቪሲዲ እና በኢንተርኔት እንደ ልብ ይገኛሉ። በተለይም በየመንገዱ ሲዲዎችን አዝለው የምናያቸው የደሳለኝ ባልደረቦች በጀርባቸው በሚያዝሉት « አንቀልባ» ውስጥ የወሲብ ሲዲ አይጠፋም። ሃይማኖታችን አይፈቅድም እያሉ ይህንን ሲዲ ከመያዝ የሚቆጠቡ አዟዋሪዎችም ጥቂት አይደሉም።«ላጥ ላጥ»፣ «ጭው ጭውን»፣ «ፒቢ»፣«ስፔሻል»፣ « ፈረንሳይ ካራቴ» ወዘተ... በሚሉ የዳቦ ስሞች የሚታወቁት የወሲብ ፊልሞች ግን ከካሴት አዟሪዎች እና ቪዲዮ ቤቶች ሌላ በከተማችንም በዋናነት በቪዲዮ ካሴት ማከራያ ሱቆች እንደ ልብ ይገኛሉ።

## ሴቶች እና ሲዲዎች

የቻይና፣ የሳቲን፣ የፈረንሳይ የጥቁሮች የዐረቦች አንዳንዴም የሐበሾች የወሲብ ፊልሞች በሲዲ ገበያ ላይ እንደሚገኙ አዟሪዎቹ ይናገራሉ። እውን ሐበሾች የሚተውኑበት የወሲብ ሲዲ አለ?

ካሴት አዟሪው ደሳለኝ ከመርካቶ «ጎንደር በረንዳ» «ሐበሾች የተወኑበት ነው» ተብሎ በአራት ብር የሚገዛውን ሲዲ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወስዶ ከ 8 እስከ 15 ብር ድረስ ይሸጠዋል። ኾኖም ደሳለኝ ለደንበኞቹ በፍጹም ርግጠኝነት « የአበሻ ፒቢ» እየሸጠላቸው እንደኾነ ይነገራቸው እንጂ እርሱ ግን ዐይቶ ያረጋገጠው አንዳችም ነገር የለም። ለረዥም ዓመታት የወሲብ ፊልሞችን በማየት ልምድ ያካበተው ፈቃዱ በኢትዮጵያውያ ሴቶች የተሠራ ፊልም አለ የሚለውን ጥርጣሬ አይቀበለውም። በእርግጥ የ«ፖርንስታር» ዘውዱ ዓርዐያ የምትባል ኤርትራዊት የተሳተፈችበት ፊልም ማየቱን ያስታውሳል። «ምናልባት ያንን ይኾናል የሀበሻ እያሉ የሚሸጡት።»

ሴቶች ለሲዲ አዟሪው ደሳለኝ «ምቹ» ደንበኞቹ ናቸው። በዛ ያሉ የሴት ደንበኞች እንዳሉት የሚናገረው ታሳኝ «ስለሚፈሩ የተባሉትን ዋጋ ከፍለው ቶሎ ይሄዳሉ» ይላል። ከሁለት ዓመት በፊት «የወሲብ ፊልሞች ፍጆታ በአዲስ አበባ ነዋሪዎች» በሚል ርዕስ በአንድ ተማሪ በተደገረ መለስተኛ ኢ-መደበኛ ጥናት ይህንኑ የሚያጠናክር ውጤት ታይቷል። ፒያሳ አካባቢ በሚገኙ ስድስት የሲዲ ማከራያ ቤቶች መዝገቦች ላይ በተደረገው በዚህ መጠናዊ ምርምር ልቅ የወሲብ ፊልሞችን ከተከራዩት ደንበኞች ውስጥ 42 በመቶ የሚኾኑት ሴቶች ኾነው ተገኝተዋል።

## የወሲብ ፊልም ኢንዱስትሪ

የዚህ ጥናት ባለቤት የኾኑት እና በልቅ የወሲብ ፊልሞች ላይ ተደጋጋሚ ኢ-መደበኛ ምርምር ያካሄዱት፣ኾኖም ስማቸው ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋራ እንዲነሳ የማይሹ ግለሰብ ልቅ የወሲብ ፊልሞችን በሁለት ዋና ዋና ዘርፍ (genre) ይመድቧቸዋል። «ሃርድኮር»እና «ሶፍት ኮር» በሚል። በመጀመሪያዎቹ ዐይነት ዘርፎች ሥር ያሉ ፊልሞች ሴትን ልጅ በማዋረድ ላይ የተመሠረቱ እጅግ አጸያፊ እና በሕሊና የሚከብዱ እንስሳዊ የወሲብ ትዕይንቶች የሚቀርቡበት ነው። ከእነዚህም መሀል «gangbang» (የደቦ ወሲብ) «incest» (በስጋ ዘመዶች መሀል የሚደረግ)፣ cumshot (ሴቶችን ከፉኛ በሚያዋርዱ ትዕይንቶች የተሞላ)፣ «animal sex»(ሰዎች ከእንስሳት ጋር የሚያደርጓቸው ወሲቦች) ያካትታል።

በሁለተኛ ዘርፍ የሚመደቡት «ሶፍት ኮር» ተብለው ሲጠሩ እነዚህ ፍቅረኛሞች አብረው ቢመለከቷቸው ወይም በለዘብተኛ ቤተሰብ መሀል ቢታዩ ያን ያህል አጸያፊ ሲባሉ የሚችሉ አይደሉም። ግልጽ ከመኾናቸው ውጭ ጨዋ እና ተፈጥሯዊ ወሲቦችን ብቻ ያሳያሉ። ጥናት አድራጊው እንደ እነዚህ ዐይነት ፊልሞች በውጭው ዓለም በቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሊገኙ እንደሚችሉ ይናገራሉ። እንደ ምሳሌም የስዊድኑን «TV 1000 ቻናል፣ የአሜሪካኑን « Ultrablue Channel እንዲሁም የፈረንሳዩን XXL Channel ይጠቅሳሉ። የልቅ ወሲብ ፊልሞች በብዙ አገሮች በትልቅ ካፒታል የሚቋቋሙ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚመረቱ ሲኾን ልክ እንደ ኦስካር ኹሉ የ« ፖርን ኦስኮር» ተብሎ የሚጠራውን «AVN» የተሰኘ ዓመታዊ የፊልም ሽልማት በድምቀት ያካሄዳሉ። ይኸው የወሲብ ፊልሞች ኢንዱስትሪ በአሜሪካ ብቻ ከ13 እስከ 19 ቢሊዮን ዶላር ዓመታዊ ገቢን ያስገኛል። የካሊፎርኒያዋ «ሳን ፈርናንዶ» መንደርም የልቅ ወሲብ ፊልሞች ማዕከል ተደርጋ ትታያለች። ከ1200 በላይ የወሲብ ፊልም ካምፓኒዎች ይገኙባታል። ከእነዚህ መሀል « Huaker Video»፣ « vivid pictures»፣ «Digital Play Ground»፣ «Extreme Associates» በዋናነት ይጠቀሳሉ። የ« Husler Video» ታዋቂዎቹን አቀንቃኞች ኤሚኒም እና ስኑፕ ዶግን በወሲብ ፊልሞች ላይ እንዲተውኑ በማድረጉ ይታወቃል።

ደጆቻቸውን ከፍተው ከትዕይንቱ አዳራሽ የሚወጡ ታዳሚዎችን በፊልም ያያችሁትን በእውን ታዩት ዘንድ የሚል ድምፅ የለሽ ጥሪ ያቀርቡላቸዋል።

ዐሥራ አምስት ዓመታትን በወሲብ ፊልሞች ባህር ያሳለፈው ፈቃዱ ፊልሞቹን ካየ በኃላ ሁሌጊዜም በፀፀት ይነዳል። ቀጣይ ደቂቃዎችን የሚያጠፋውም ዳግም ላለማየት ከራሱ ጋራ ጥብቅ መሐላ በመግባት ነው። የመሐላዎቹ ዕድሜ ግን ከሁለት ቀናት ተሻግሮ አያውቅም።መሀላዎቹ ግን ከሁለት አስርተ አመታት በላይ ተሻገሩ። በዚህም የተነሳ «በስተርጅና ዘመኔ የወሲብ ፊልሞችን ላለማየቴ ምንም ማረጋገጫ የለኝም» ይላል ሲጋት ቢደመነው ገፅታ።

# ዱቬ እና CV

የገጠር የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ነኝ። ወጣት የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ። መታወቂያዬ ላይ ከስሜ ትይዩ "ሌክቸረር" የሚል ማዕረግ አለበት። ኑሮ እና ሕይወቴ ግን ማዕረግ አልባ ነው። ደሞዜ ሁለት ሺሕ ስድስት መቶ ብር ይደርሳል። ይህ ብር ግርማ ሞገሱ አፍ ይሞላል። ሲኖሩበት ግን ወፍ ነው፤ ይበራል። እውነት እውነት እላችኋለሁ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድሮ ፀጉራቸው አፍሮ ሳለ የገቡትን ቃል ባያሳኩትም እንዳላሳፍራቸው በሚል በቀን ሦስቴ ልብላ ብዬ በተውተረተርሁ ቁጥር ወር ሳይደርስ በዱቤ እጥለቀለቃለሁ። አስተማሪ ካልበላና ካላነበበ ራሱንም ትውልድንም ይገድላል። በርግጥ ማንበብ ከተውኩ ዘመን የለኝም። መብላት ግን መተው የማይቻል ኾኖብኝ ይኼው በዱቤ እኖራለሁ።

በደሞዜ ላይ 160 ብር የቤት አበል ጠብ ይደረግበታል። አንዲት አነስተኛ ክፍል ተከራይቼ፣ አነስተኛ ምግብ በልቼ፣ ቲቪ ከጎረቤታችን አይቼ እኖራለሁ። ለነገሩ የተከራየሁት ክፍል ብቻም ሳይኾን እውቀቴም አነስተኛ ነው፤ በግሌ ለዩኒቨርሲቲ መምህርነት የሚያበቃ ዝግጅትም ኾነ ክምችት ኖሮኝ አያውቅም። አንዳንድ እድሜ ጠገብ የዩኒቨርሲቲያችን ፕሮፌሰሮች እንደእኔ አይነቶቹን ወጣት በደንብ ያልተማሩ ሌክቸረሮችን « ጥቃቅንና አነስተኛ ሌክቸረሮች» እያሉ

ይጠሩናል። እውነቱን ለመናገር ብዙም ማስተማር አልችልም። ትምህርት ሚኒስቴር ትችላለህ ካለኝ ግን ምን አደርገዋለሁ። ለምን መንግሥቴን "ዋሸ" አስብላለሁ። ትችላለህ ካለኝ እችላለሁ። እኔ ከመንግሥቴ በላይ ስለ'ኔ ካወቅኩ ቡዳ ነኝ ማለት ነው።

መምህር በመሆኔ ምሳሌ እወዳለሁ። ስለዚህ ከላይ ያነሳሁትን ጭብጥ በምሳሌ አስረዳለሁ። በደርግ ጊዜ አንድ ዶክተር ሬሳ ክፍል ገብቶ የተረሸኑ ወጣቶች ህይወታቸው እንዳለፈ «ቼክ» አድርጎ ሁሉም መሞታቸውን ካረጋገጠ በኃላ ለተረኛ ጠባቂ ክፍሉን አስረክቦ ይወጣል። ይህንን ተከትሎ «'ጓድ እከሌ አብዬታዊ እርምጃ የተወሰደባቸውን ወጣቶች ጎበኙ» የሚል ዜና ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በሰፊው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንዲያነብ ስለተፈለገ አንድ ከፍተኛ ጓድ ሬሳዎቹን የመጎብኘት ፕሮግራም ይያዝላቸዋል። ይመጣሉ።እቅፍ አበባ ተበርክቶላቸው፣የሬሳ ክፍሉን ሪቫን ቆርጠው ወደሬሳ ክፍል ይገባሉ፤ ሬሳዎቹ በተገቢው ሁኔታ አብዮታዊ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ዞር ዞር እያሉ ከጎበኙ በኃላ በሚያስገመግም ድምፃቸው «ኢትዮጵያ ትቅደም»የሚል መፈክር አሰምተው ክፍሉን ለቀው ሲወጡ መፈክሩ ያባነነው አንድ ከተረሸኑት ውስጥ የነበረ የኢህአፓ ወጣት ከሬሳዎቹ መሀል ተነስቶ «ጓድ! ይምጡ! ያድኑኝ! በህይወት አለሁ! አልሞትኩም! እባከዎ ያድኑኝ!» አላቸው። በዚህን ጊዜ ጓዱ ቆግ አሉ፤ «ስማ አንተ አድሀሪ! በዶክተር አስመርምረንሀል፤ ዶክተራችን መሞትህን አረጋግጦልናል። ባለሙያው አንተ ነህ እርሱ?» አሉት- አሉ።

አሁን ይህንን ታሪክ ምን እዚህ ሰነቀረው? ይቅርታ! መምህር በመሆኔ ምሳሌ እወዳለሁ።

የገጠር የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ በመኾኔ ብቻ ሰዎች ትልልቅ ጉዳዮችን ያማክሩኛል። እናቴ ሲያማት ሐኪም ቤት ሄዳ ላልተፈለገ ወጪ መዳረግ አትወድም። የተማረ ልጅ አለኝ እያለች ሰፈራችን አቅራቢያ በሚገኝ "ኪዮክስ" እየሄደች "ሚስኮል" ታደርግልኛለች። ለእርሷ እኔ የህክምና ዶክተርም ጭምር ነኝ። እስካሁን ያልተገለጠላት ነገር ቢኖር ለምን በየወሩ ብዙ ብር እንደማልክላት ነው። ለምን ትልቅ ቤት እንደማልገዛላትም በደንብ አይገባትም። ግን ተስፋ ታደርጋለች። በእውነት እላችኋለሁ እንኳን ቤት ልሰራላት ይቅርና ባለቆቡን ሚስማር እንድገዛላት የሚያስችል ብር የለኝም። ለእማዬ ግን ይህን ማስረዳት ቅስሟን መስበር ነው።

አሁን አሁን ዩኒቨርሲቲ ማስተማሬን ተከትሎ ሰዎች በተዘዋዋሪ በሚያሳዩኝ አክብሮት እጅግ እየተሰቃየሁኝ እገኛለሁ። ቢያንስ ክብሬን የሚስተካከል ብር ሊኖረኝ ይገባል ስል አስባለሁ። በዚህ ረገድ መንግሥቴን ተቀይሜዋለሁ። ደመወዝ እጨምራለሁ እያለ ሲያወራና ሲያስወራ

ይኸው ስንት ዘመኑ።

አብረውኝ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋራ በትርፍ ሰዓታችን ስለ ደመወዝ ጭማሪ ማውራት አይታክተንም። ሰው ሁለት ዓመት ሙሉ እንዴት ስለደሞዝ ጭማሪ ብቻ ያወራል? ወሬውን ማን እንደፈጠረው አላውቅም። ሆኖም ከአጎራብች ዩኒቨርስቲዎች እንደተሰማ እገምታለሁ። ወይም ደግሞ ለማስተርስ ትምህርት አዲስ አበባ ሄደው የተመለሱ ጥቃቅንና አነስተኛ መምህራን ወሬውን ከዲግሪያቸው ጋራ ይዘውት መጥተው ሊኾን ይችላል የሚል መላምት አለ።

ምንም ይኹን ምን እንዴት ለሁለት ዓመት ሰው አንድ ወሬ ያመነዥካል? ደመወዝ ጭማሪ፤ ደመወዝ ጭማሪ፣ ደመወዝ ጭማሪ. . .። አንድ ወቅት ሁላችንም ተሰላችተን ይህን ጉዳይ ላናነሳ ተማምለን ነበር። አዲስ የተቀጠረ አንድ "ጥላቢስ" የኾነ አስተማሪ "ጓደኛዬ ጋዜጣ ላይ ደመወዝ እንደሚጨመር አነበበ" ብሎ በማውራቱ የደመወዝ ወሬ በዩኒቨርሲቲው ዳግም አገረሸ። ጋዜጣውን አነበበ የተባለውን ልጅ ስልክ እንዲሰጠን ተማጸንነው። በጄ አላለም። "ላውድስ ፒከር" ላይ አድርጎ ራሱ ጓደኛውን እንዲያወራው ለመንነው። በሰቡብ ላይ ሰበብ እያበዛ ነገ ዛሬ እያለ አሸን። በዚሁ ተናደን አገለልነው። ሲያንሰው ነው፤ በሰው ሕይወት ይቀልዳል እንዴ። ገጠር ውስጥ ማግለልን የመሰለ ቅጣት አይገኝም።

## አዲስ ሐሳብ መከሰት

ሰሞኑን ባልተለመደ ኹኔታ የምኖረው ኑሮ እጅግ መረረኝ፤ አንገሸገሸኝ። አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ኾኖም እንደ ድንገት ድንቅ ሐሳብ ተከሰተልኝ። ዲቪ መሙላት። ቢንጎ!! ይህ ሐሳብ ለምን እስከዛሬ እንዳልተከሰተልኝ ገረመኝ። ያን ቀን ምሽት ደስ ብሎኝ አመሸሁ። ለመጀመርያ ጊዜ የገጠር ሕይወቴ በተስፋ ተሞላች። ሌሊቱን ደስ ደስ የሚሉ ህልሞችን አየሁ። በተከታታይ ያየኋቸው ህልሞች መቼታቸውን በአሜሪካ ከተሞች ያደረጉ ነበሩ።

በነጋታው ጠዋት ስነቃ ግን ሞራሌና ወኔዬ ከዳኝ። እንዴት እኔ ዲቪ እሞላለሁ። የት ሄጄ እሞላለሁ። ሰው ቢያየኝስ። ደግሞ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ እንደ ተራ ዜጋ ዲቪ ይሞላል እንዴ!?

በመሠረቱ ዲቪ ከእኔ ስብእና ጋራ በፍፁም አይሄድም። ከልጅነቴ ጀምሮ መለመንና የሰው መመኘት አልወድም። እናቴ እንጀራ ከጎረቤት ተበድረህ ይዘህ ና ስትለኝ እንኳ በጄ ብያት

አላውቅም። ጦሜን ማደር እመርጣለሁ። ትምህርት ቤትም ቢኾን ላጲስ ተውሼ አላውቅም። የተሳሳትኩትን ጽሑፍ በምራቂ አክኬ፣ ፊትን አጠፋለሁ። እከካም ልትሉኝ ትችላላችሁ። ግን እውነቱ ይኸው ነው። ሁለተኛ ክፍል አብረውኝ ይቀመጡ የነበሩ ልጆችን መቅረጫ ብያቸው አላውቅም። እርሳሴን ከግድግዳ ጋር እያፋጨሁ አሾላለሁ፤ እቀርጻለሁ።አሁንም እከካም ልትሉኝ ትችላላችሁ። ግን እውነታው ይኸው ነው።

ዲቪ የአሜሪካ መንግስትንና ህዝብን እባካችሁ አገራችሁ አሳድሩኝ እያልኩ የምትለማመጥበት ሕጋዊ ማመልከቻ ነው። ይህን ማመልከቻ ሞላሁ ማለት የአሜሪካ መንግሥትን ተንበርክኬ ውሰታ ዋልልኝ እያልኩት ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ፍፁም ከኔ አፈጣጠር እና ስብዕና ጋራ አብሮ የሚሄድ አይደለም። የአሜሪካ መንግሥትን በማመልከቻ ከምለምን በአሜሪካን ጊቢ አድርጌ! በሀብተጊዮርጊስ ድልድይ እያሳበርኩ በእግር ወደ አሜሪካ ብሄድ ይቀለኛል። የዲቪ መሙላት ሐሳብ ውስጤ ላይ ከፍተኛ መናወጥን ሊያስከትል የቻለው በዚህ የተነሳ ነው። ራሴን የከዳሁት ያህል ተሰማኝ።

የተፈጠረብኝን ድብታና የስሜት መላሸቅ ለማስታገስ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር ሄድኩኝ፤ የዲቪ ወሬን እንዴት ብዬ እንደማነሳባቸው እያውጠነጠንኩ። ቀድሜ ጉዳዩን እኔው ካነሳሁት "አጅሬው! ዲቪ ሞላሽ እንዴ!" እያሉ ዓመቱን ሙሉ መዘባበቻ ሊያደርጉኝ ይችላሉ። በዘዴ ነገሩን ማንሳት እንዳለብኝ እያሰላሰልኩ ዘወትር የምንገለትበት ቦታ ደረስኩ። ሁሉንም እዚያው ተሰብስበው አገኘኋቸው። ያው እንደተለመደው የደሞዝ ጭማሪን ጉዳይ እያመነዠኩ ነበር። ‹‹ጋሽ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በፓርላማ መክፈቻ ንግግራቸው ላይ የደሞዝ ጭማሪ ጉዳይን አንስተዋል» የሚል አዲስ መረጃ በመስማቴ የሁሉም ፊት ፈካ ፈካ እንዳለ ለማስተዋል ቻልኩ። ኾኖም ጭማሪው ለዩንቨርሲቲ መምህራን ብቻ ሳይኾን ለሁሉም የኢትዮጵያ ሠራተኛ መኾኑ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን አንዳንድ ሂሳብ-ዘመም መምህራን ለጉባዔው ለማስረዳት ሞከሩ። በደስታችን ላይ ዉኃ ቸለሱበት። የደሞዝ ጭማሪው ወሬ እየበረደ ሲመጣ የዲቪውን ጉዳይ ለኮስ ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ።

"እናንተ! የዘንድሮ ተማሪዎች ደግሞ ጭራሽ የእንግሊዝኛ ፊደል ሳይጨርሱ ነው እንዴ ዩኒቨርስቲ የላኳቸው?" አልኩ ድምፄን ጎላ አድርጌ። ቀጥል የሚል ምልክት ተሰጠኝ።

‹‹አንዱ ስሙን ሲጽፍ አይቼው በጭራሽ "ቫውል" አይጠቀምም፤ ታምናላችሁ? ስሙ ተሻለ ነው። እንዴት "ሰፔል" እንዳደረገ ታውቃለህ "ቲ፣ኤስ፣ኤች፣ኤል"። ባወራሁት ነገር ማንም

አልተገረመም።

‹‹ሌላ ተማሪዬ ደግሞ <<one>> የሚለውን ቃል ደብሊው ኤ ኤን /wan/ ብሎ አይፅፍ መሰላችሁ!?»

«እና ምን ይጠበስ!» አይነት ፊት አሳዩኝ። አንዳንዶቹ ይልቁንም ከዚህ የባሰ የሚሉትን እያነሱ ማስረዳት ጀመሩ። አሁን ወደ ዲቪው ጉዳይ መግቢያ ሰዓት እንደኾነ ተሰማኝ። የ"ስፔሊንጓን" ወሬ ኾነ ብዬ እንጀመርኳት አልገባቸውም።

"ስሙኝማ! ከተማ ትናንት ተለጥፎ ያየሁትን ልንገራችሁ። ዲቪ እንሞላለን የሚለው ጽሑፍ ላይ "Good Luck" የሚለውን ቃል እንዴት ጽፈውት በየሁ መሰላችሁ፣ "Good Lack"።" አይገርሙም?»

ከገመትኩት በላይ ሳቁልኝ። ሳቃቸው እንደበረደ ከመሐላችን አንዱ "ዲቪ ተጀመረ እንዴ?" ሲል ጠየቀ። በቀጥታ ሊመልስለት የደፈረ ግን አልነበረም። "እኔንጃ"፣ "መሰለኝ"፣ "ኸረ ባክህ?!"፣ አሉ፤ የተወሰኑት።

ሁሉም አውቀው ነው። መቼ እንደተጀመረ አይደለም ስንት ሰዓት ላይ እንደተጀመረ ያውቃሉ። እንዳላወቀ ሰው የሚሆኑት የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ኾኖ ዲቪ መሙላት ስላሳፈራቸው ነው። ተነቃቅተናል።

## DV regardless of CV

የገጠር ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ እንደሆንኩ ደግሜ ላስታውሳችሁ። በዘራችን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እንኟ የዩኒቨርሲቴ አስተማሪ ለመሆን የበቃ ሰው እምብዛምም ስለሌለ ብርቅዬ ነኝ። እኔን የመሰለ አንድ ለናቱ ታድያ ዲቪ መሙላት አለበት? ይበለውና እኔ ዲቪ ደርሶኝ ከአገር ለቀቅኩ ማለት ቢያንስ የአንድን ብሔረሰብ ኩራትና ተስፋ ማጨለም አይሆንም?

ለማንኛውም ያለንባት ከተማ በኦባማ ፎቶዎች ከተጥለቀለቀች ሁለት ሳምንታት አልፈዋታል። ኦባማ ለዚህ የበቃው ዲቪ ደርሶት ነው የሚል ወሬ በከተማዋ ሲናፈስ ነበር። ዲቪ እንሞላለን የሚሉ ማስታወቂያዎች የትም ነው የተሰቀሉት።የትም! ! ለምሳሌ በከተማዋ የህዝብ ሽንት ቤት መግቢያ ላይ- ለምሳሌ በከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ደጅ ላይ፣ ወዘተ። ከሁሉም የገረመኝ ግን ይህን ማስታወቂያ ዩኒቨርስቲያችን ውስጥ በትልቅ ባነር ተሰቅሎ ማየቴ ነው። የተማሪዎች ካውንስል በቅናሽ ዋጋ ዲቪ ማስሞላት በመጀመሩ የካፌ ሰልፍን የሚያስንቅ ረዥም ሰልፍ በዩኒቨርስቲው

ተፈጥሯል። ዲቪ ለመሙላት ረዥም ሰልፍ። በዩኒቨርሲቲ!

በፊት አዲሳባ ሳለሁ በኢሚግሬሽን በኩል ጠዋት ጠዋት ሳልፍ አየው የነበረው ሰልፍ ታወሰኝ። ለአረብ አገር ግርድና ለመብቃት -ሰልፍ! በዚያው ቅፅበት ሰንት ዘመዶቼ በቤይሩት ኩሽና ውስጥ እንዳሉ ለማሰብ ሞከርኩ። ሰንት ዘመዶቼ የጅዳን የሸንት ቤት መቀመጫ እየወለወሉ እንዳሉ ታሰበኝ፡ያለእረፍት! ምንጣፍና መስታወት የሚያፀዱ ወገኖቼ። መቼ ለታ ኩዌት ውስጥ ከፈ..ኽ..ም ህንፃ፣ ከሰንትና ሰንተኛ ፎቅ ራሷን የፈጠፈጠችው ፋጡማ የሰፈራችን ልጅ አይደለችም እንዴ! እንዲያውም ሲወራ የነበረው እንደዚያ አይነት ረዥም ፎቅ በአገራችን ገና ስላልተሰራ እንደ ፋጡማ የመከስከስ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች እድሉን አገር ውስጥ ማግኘት አይችሉም። ስለዚህ ወደ አረብ አገር «ሪፈር» መባል አለባቸው። ይህ ሁሉ እውነታ በአገሬ እያለ ዲቪን ማንቋሸሽ ተገቢ ነውን?

በዩኒቨርስቲያችን ለዲቪ የተደረገው ዝግጅት ከዚህ የመነጨ ይመስለኛል። ዝግጅቱን ለማየት በግቢው መዘዋወር ጀመርኩ። የዲቪ ማስታወቂያዎች በተማሪዎች ካፌ፣ በመማርያ ክፍሎች፣ ደጅ ባሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ እንዲሁም የግሬድ መለጠፊያ ሰሌዳዎች ላይ፣ በቤተ መጻሕፍቱ በር ላይ ወዘተ ተለጣጥፎ አየሁ። የማስታወቂያው ይዘት ተማሪዎች ዕድሉ እንዳያመልጣቸው እና እንዲጠቀሙበት የሚያባብል ነው። የተማሪዎች ካውንስል ነው ይህንን የዲቪውን ጉዳይ የሚያስተባብረው። በኔ ጊዜ የነበረው የተማሪዎች ካውንስል የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ ያስተባብር እንደነበር ለአፍታ ሸው አለብኝ።

ወደራሴ ጉዳይ ተመለስኩ። በእርግጥ አሳፋሪ ነው። ሆኖም አገሬና እኔ ካለንበት ሁኔታ አንፃር ዲቪ ብሞላ «ይሁዳ» አያስብለኝም ስል ራሴን አፅናናሁ። ማንም ሳያውቅ ዛሬውኑ ዲቪ መሙላት አለብኝ። እንዴት? በትንሽ ከተማ ውስጥ እንኳን እኔ ሙሁሩ ሰው ይቅርና ያለሰፈሯ የመጣች መሀይም ዝንብ እንኳ ትታወቅ የለም እንዴ!? በእርግጥ በከተማዋ ድህነት እየተንሰራፋ ስለመጣ ቆሻሻ ዝንቦች በዝተዋል። ድሮ ዝንብ አልነበረም ለማለት አይደለም። ቀድሞ የነበሩ ዝንቦች ቢያንስ ቢያንስ ተጣጥበው ነው ወደከተማ የሚወጡት። አሁንኮ ቆሽሸዋል። የግል ንፅህናቸውን እንኳ አይጠብቁም።

ለማንኛውም ዲቪ ያለኮሽታ የምሞላበትን አማራጭ ለማየት ከዩኒቨርሲቲው ወደ መሀል ከተማ የሚወስድ ታክሲ ለመያዝ ተንቀሳቀስኩ። ዩኒቨርሲቲው ዋና በር ላይ ታክሲው እስኪሞላ ብዙ ነገር ለመታዘብ ቻልኩ። ቀድሞ የተማሪ "ሃንድአውት" በማባዛት ይጠመዱ የነበሩ ፎቶኮፒ ቤቶች መስኮቶቻቸው በዲቪ ማስታወቂያ አሸብርቋል። እዚህም ዲቪ ለመሙላት ብዙ ተማሪዎች ተሰልፈዋል። በእጃቻቸው የሚባዙ ‹‹ሃንድ አውቶች» ሳይኾን በከፊል የተሞሉ የዲቪ ፎርሞችን ነበር የያዙት።

ከተማ ደርሼ ከታክሲው እንደወርድኩ ወደ አንድ ኢንተርኔት ካፌ ጎራ አልኩኝ። ከተደረደሩት ኮምፒውተሮች ወደ አንዱ ጠጋ ብዬ ኢንተርኔት የምበረብር መስዬ የቤቱን ደንበኞች መበርበር ጀመርኩ። ሰዎች ነጭ አቡጀዲ እየተደገፉ ተራ በተራ ፎቶ "ቀጭ" ይደረጋሉ። ብዙ ወጣቶች፣ ጥቂት ጎልማሶች፣ ጥቂት ትልልቅ ሰዎች፣ ባልና ሚስት፣ ባል ሚስት እና ሰባት ልጆቻቸው፣ ጋዝ ልትገዛ የተላከች የቤት ሰራተኛ፣ መካኒክ ከቱታው፣ ያስተማርኳቸው ተማሪዎች፣ የቀን ተማሪዎቼ፣ የማታ ተማሪዎቼ፣ «ኤፍ» የሰጠኃቸው ተማሪዎቼ፣ ወልደው ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎቼ፣ ወዘተ፤ ቤቱ የማያስተናግደው ዐይነት ሰው የለም። ሁሉም ለዲቪ ስኬት የጭንቅ አማላጁን ስም ይጠራል። ይህ ሕዝብ አገሩን አይፈልጋትም እንዴ። ለምን አንድነቱን በግልፅ ጨረታ ሸጧት አይሄድም? ሆ!

በዚህ ኢንተርኔት ቤት ጠረጴዛ ላይ ዲቪ የተሞላበት ወረቀት ተከምሯል። በአሙቁ መጨረሻ የማርማቸውን የተማሪዎቼን ፈተና ወረቀቶች አስታወሰኝ። ለነገሩ የዚህን ዘመን ተማሪዎች ፈተና ከማረም የሰሊጥ እርሻ ማረም ይሻላል። ወይም ደግሞ የኔን ተማሪዎች ፈተና ከማረም ይህንን የዲቪ ክምር ማረም ሳይሻል አይቀርም። ሁለቱም ‹‹ስፔሊንግ›› ማረም ስለሆነ ስራው ብዙም አይራራቅም። የአገሬ መንግስት የዩኒቨርሲቲ ፈተና አራሚ ከሚያደርገኝ የአሜሪካ መንግስት ዲቪ አራሚ አድርጎ ቢቀጥረኝ ይሻል ነበር ብዬ አሰብኩ፤ ለአፍታ። ሐሳቤ በራሱ ፈገግ አሰኘኝ። አይ አሜሪካ ስላንቺ ማሰብ በራሱ ፈገግታን ይፈጥራል ለካ።በኋላ ላይ ደግሞ ያሰብኩት ነገር ከአንድ እኔን ከመሰለ ምሁር የሚጠበቅ ባለመሆኑ ግለሂስ አደረግኩ። ራሴን አወገዝኩ። ኮነንኩ።

በዚህ ኢንተርኔት ካፌ ብዙ ሰው ዲቪ ለመሙላት የሚሽቀዳደመው ከዚህ ቀደም በዚህ ቤት ዲቪ የሞሉ አራት የከተማዋ ነዋሪዎች ዲቪ ደርሷቸዋል በመባሉ ነው። ‹‹ገድ አለው!» ይባላል ይህ ቤት። የዲቪ ገድ!! ቤቱ በር ላይ የተለጠፈውም ይኸው ነው። እንዲህ ይላል፡- «ባለፉት ተከታታይ አመታት ብዙ ዜጎችን ዲቪ እንዲያሸንፉ ያስቻለው ድርጅታችን እንሆ ዘንድሮም...» የሚል ረዥም ጉረኛ ማስታወቂያ ለጥፈዋል። ልጆቼን አስተምሮ ለቁም ነገር ያበቃ ወላጅ እንኳ እንዲህ አይኩራራም።

ወደራሴ ጉዳይ ልመለስ። ዘንድሮ ወጣም ወረደ ዲቪ መሙላት እንዳለብኝ የተነጋገርን መሰለኝ። ስለዚህ እዚሁ «ገዳም ነው!» የሚባልለት ቤት ለምን አልሞላም?!። የማስተምራቸው ልጆችና የሚያውቁኝ ሰዎች ከቤቱ ተጠራርገው መውጣታቸውን እርግጠኛ ከኾንኩ በኋላ ፎቶ የምታነሳዋን ልጅ ዲቪ መሙላት ፈልጌ እንደመጣሁ ነገርኳት፤ የሞት ሞቴን፤ በሹክሹክታ።

"እሺ ቲቸርዬ! እንዴት ነህ! አስተምረኸኛል፣ ጠፋህ!» አለችኝ። አከታትላ።

እ!?

«አንድ ኮርስ ሰጥተኸኛል። እንዴት ነህ ቲቸር፣ አስር ብር ከፍለህ ፎቶ ትነሳና ይህን ፎርም ሞልተህ ትሄዳለህ። ነገ ማረጋገጫ እሰጥሃለሁ፤ ወይም ቢሮ ይገባልህ ልምጣ ቲቸር?»

«እእ...እሺ አዎ!!»

«ማን ቲቸር ለምን እንደሆነ ባላውቅም አንተ ዲቪ የምትሞላ አይመስለኝም ነበር፤አንተ ከሄድክ ማን ያስተምረናል?» አለች ጮኽ ብላ።

ክው ብዬ ቀረሁ።

ምኗ ክውካዋ ነገር ናት ባካችሁ። ይችን ክውካዋ ማስተማሬ አበሳጨኝ። በአቅራቢያችን ፎቶ «ቀጭ» ለመደረግ ይጠባበቁ የነበሩ ሰዎች ሁሉም ዞር ብለው በትኩረት፣ በትዝብት፣ በንቀትና በአክብሮት አዩኝ። አይናቸው ወጋኝ።አቃሰትኩ። የተወሰኑት ግን በኔ ዲቪ መሙላት ኩራት ቢጤ የተሰማቸው ይመስለኛል። የተማረ የሚሞላውን ነገር እየሞሉ እንደሆነ በመረዳታቸው መሰለኝ። ልጅቷን ግን ታዘብኳት። ምናለ ቢያንስ ቲቸር መሆኔን ዝግ ባለ ድምፅ ብትናገር! እኔን ከአሜሪካ አሽማቆ ለማስቀረት የሚደረግ ጥረት መሆኑ ነው? ምቀኛ! አልንበረከክም!

እንደተረዳሁት ከሆነ በከተማዋ የኢንተርኔት ፍጥነቱ ቀን ቀን ቀርፋፋ ስለሆነ ኢንተርኔት ቤቶቹ ዲቪ ፎርሙን ቀን ቀን በወረቀት ብቻ እያስሞሉ ሌሊት ሌሊት በኢንተርኔት ይልኩታል። በነጭ ወረቀት ለሞሉት ሰዎች በነጋታው የማረጋገጫ ደብዳቤ ይታደላቸዋል። በዚህ መሀል የስም ስህተት ቢከሰት ግን ማን ተጠያቂ እንደሚሆን አልገባኝም። እድሌን ማበላሸት የለብኝም። "እመለሳለሁ" አልኳትና ሹልክ ብዬ ወጣሁ።

ወጥቼ መንገድ ከጀመርኩ በኋላ ግን ተማሪዬ ያነሳችኝን ፎቶ ትዝ አለኝ። ለተማሪዎቼ አሳይታቸው መሳለቂያ ያደርጉኝ ይሆን? እያልኩ በማሰብ ተረበሽኩ። ፎቶዬን «ዲሊት» አድርጊው ልላት ፈለኩ። ሆኖም ያን ማድረግ ይበልጥ ትኩረት መሳብ ሆኖ ስለተሰማኝ ተውኩት። ደግሞ ያነሳችኝ ፎቶ በጣም ያሳዝናል፤ አንድም የአስተማሪነት ግርማ ሞገስ የለኝም። ድሮስ አስተማሪ ግርማ ሞገስ አለው እንዴ? አስተማሪ ትከሻ አለው እንዴ? አስተማሪ ትከሻው ቾክ ነው!! ብናኝ!

በከተማዋ ያሉ ሁሉም ኢንተርኔት ቤቶች (ጥቂት ቢኾኑም) ደንበኞቹ ባሉበት ዲቪ እንደማይልኩ ተረዳሁ። ይህ መልካም ነገር አይደለም። ለምን ብዬ እድሌን አበላሻለሁ። ሌላ አማራጭ መፈለግ ነበረብኝ። በከተማዋ ወደሚገኘው አንድዬ ፖስታ ቤት አመራሁ። በሩ ላይ ከፍተኛ መጨናነቅና ፀብ የሚመስል ግርግር አየሁ። ጥቂት ፖሊሶች ስርዓት ለማስያዝ እየሞከሩ ነበር። በቅርቤ ያገኘኋትን የገጠር ቆንጆ ስለጉዳዩ ጠየቅኳት። «ዱርዮዎች ያለወረፋቸው እየገቡ አስቸግረው ነው» አለችኝ። ዲቪ ለመሙላት ጠዋት ወረፋ የያዙ ሰዎች በከተማዋ ጎረምሶች ስልፋቸው ተረብሸዋል። የፖስታ ቤቱ ሰራተኞች ደግሞ በስነስርዓት ወረፋ ካልተያዘ አናስተናግድም ብለው ማመፃቸውን ልጅቱ ጨምራ አብራራችልኝ።

ተገረምኩኝ። የምር ተገረምኩኝ።

ፖስታ ቤት በር ላይ ያሉትን ማስታወቂያዎች ለማንበብ ሞከርኩ። ዲቪ ዘንድሮ ለአንድ ወር ብቻ እንደሚቆይ፣ የቀሩት ቀናት ጥቂት እንደሆኑ፣ ዲቪ በፖስታ ቤት መሙላት ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት፣ ለምሳሌ ዲቪው ሲመጣ የስም ስህተት ቢኖረው ፖስታ ቤት ለአሜሪካ ኤምባሲ ቀጭን ደብዳቤ የመፃፍ ብቸኛ ባለመብት እንደሆነ ወዘተ ይናዘዛል።ፖስታ ቤት መንግስታዊ ድርጅት ነው። ዜጎቹን በተዘዋዋሪ ሌላ አገር እንዲሄዱ ተግቶ እየሰራ እንደሆነ ነቃሁበት።

ተዳፈርኩ አትበሉኝና ሳስበው ሳስበው የአገሪቱ ርእሰ-ብሄር ራሳቸው ዲቪ የሚሞክሩ ይመስለኛል። እርሳቸው ባይሞክሩ እንኳ ልጆቻቸው፣ ልጆቻቸው ባይሞክሩ እንኳ የልጅ ልጆቻቸው እንደሚሞክሩ ደመ-ነፍሴ ይነግረኛል። ለምን ይዋሻል? ስንት ባለስልጣን አይደል እንዴ ለአገር ጉዳይ እንደወጣ የቀረው? የአገሬ ጋዜጠኞች ሲሰዎቹ ዜና ይዘን እንምጣ ብለው አይደል እንዴ የአሜሪካ ጅብ የበላቸው! የሀበሻ ሀብታም ሚስቶች አሜሪካ ሄደው የሚወልዱት የአሜሪካ ገንፎና አጥሚት ጣፍጧቸው ነው? አይመስለኝም።በቀደም ማን የምትባለዋ ዘፋኝ እንትን በሚባለው መፅሄት ምነው ጠፋሽ ስትባል «ልጅ ለመውለድ አሜሪካ ሄጄ ነው» አይደል እንዴ ያለችው!? ምን ማለቷ ነው? የኢትዮጵያ መንግስት አገር ውስጥ ልጅ መውለድ ቫት ያስከፍላል የሚል ህግ አውጥቶ ነው እንዴ ህዝበ አበሻ አሜሪካ እየሄደ የሚያምጠው? እውነታው ወዲህ ነው። ልጃቸው ኢትዮጵያዊ እንዳይሆንባቸው የሚፈሩ ዜጎች ከእለት እለት

ቁጥራቸው እያደገ ነው።

ሌላውን ሁሉ ትተን ድህ ዘመዶቼ በስሀራ በረሃ ዣንጥላ ይዘው ፤ በኤደን ሰላጤ ራሳቸውን ጥለው፣ በሜዲትራኒያን ባህር ከወረቀት በተሰራች ጀልባ ወደ አውሮፓ ለመሻገር የሚሞክሩት ለምን ይኾን? ሁሉን ቢናገሩ ሆድ ባዶ ይቀራል።

ለነገሩ እንኳን እኔ ቱባ የመንግስት ባለስልጣናትም ዲቪ ይሞላሉ። ከዚህ ቀደም የቀድሞው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ዲቪ ደርሷቸው ቀስ ብለው ሲሄዱ ቢሉ አይደል እንዴ የተደረሰባቸው። እኔ የምሰራበት ዩኒቨርሲቲ የ‹‹ምርምርና አካዳሚክ›› ም/ፕሬዝዳንትም ሰሞኑን ዲቪ ሲሞሉ እንደታዩ በወሬ ወሬ ሰምቻለሁ። ሰውየው እድሜያቸው ገፍቷል እኮ።በዚያ ላይ አሜሪካ ነው የተማሩት ሲባል ነበር። ተንቀዥቅዠው መጥተው ነው ጉድ የሆኑት ማለት ነው። ይኼኔ ዲቪ ሲሺ እንደማይመርጥ ተረዳሁ።

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ዲቪ መሙላት ይፈልጋል።ከሊቅ እስከ ደቂቅ በሚባለው ክፍፍል ውስጥ እኔ እገኛለሁ፤ለዚያውም ከላይኛው ተርታ። ስለዚህ ዲቪ እሞላለሁ።

ቅድም ወደነበርኩበት ገዳ'ሙ ኢንተርኔት ካፌ ደረቴን ነፍቼ ሄድኩኝ።ፈገግ ብዬ ፎቶ ተነሳሁኝ።ኮስተር ብዬ ፎርሙን ሞላሁኝ። ከኢንተርኔት ቤቱ ስወጣ ግን እንዳች ቀፋፊ ስሜት ሰፈረብኝ።

*From the Library of*

**ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ**

***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES***

## < <ማዘር ቤቶች> >

በአዲስ አበባ የዕለት ጉርስን በርካሽ ዋጋ የሚያቀርቡ ትናንሽ ምግብ ቤቶች (ማዘር ቤቶች) ዝቅተኛ ገቢ ላለው የኀብረተሰብ ክፍል በሚሰጡት አቅርቦት ይታወቃሉ። የአዲስ ነገር ጸሐፊ መሐመድ ሰልማን ሰሞነኛ ቅኝት የኑሮ ዉድነት ማዘር ቤቶችን ይበልጥ ተወዳጅ እንዲኾኑ እንዳደረጋቸው ያሳያል።

ቦሌ ወሎ ሰፈር አካባቢ የሚገኘው «ሐበሻ ሬስቶራንት» ለአንድ የ«ፍስክ በየአይነት» 95 ብር ያስከፍላል። «ሽሮ» በዚህ ሬስቶራንት ውስጥ የ 33 ብር ከብርን ተጎናጽፋለች። እንዲህ ዐይነት የምግብ ዋጋ ዝርዝሮችን በቦሌ እና በአካባቢዋ ባሉ «ደልቃቃ» ሬስቶራንቶች «ሜኑ» ላይ ማንበብ አዲስ አይደለም። «ሜኑዎቹ» ደረታቸውን ገልብጠው የሚያሳዩት የዋጋ እውነት የአዲስ አበባን የኑሮ ፅንፍ ለመረዳት የሚያስችሉ ካርታዎች አሰመስሏቸዋል። በእርግጥም የአንዲት የፅዳት ሰራተኛ የወር ደመወዝ በነዚህ ምግብ ቤቶች ከወዳጅ ዘመድ ጋር ዘና ብሎ አራት ለመገባበዝ በቂ ላይሆን ይችላል።

ከምግብ ዝርዝር አስቀድሞ የዋጋ ሰንጠረዥን ማየት የሚቀናው ቴዎድሮስ ዓለማየሁ ይህ ኹኔታ የዓለም ፍጻሜ የመቃረቡ ምልክት ነው ሲል አጋንኖ ያወራል። ቴዎድሮስ ደረጃቸውን

የጠበቁትን እንደ እነዚህ ዐይነት መደበኛ ሬስቶራንቶችን በደመወዝ ሰሞን እንኳ ለመጎብኘት አይደፍርም፤ ተገቢ ነው ብሎም አያምንም። «ሜኑ-ፎቢያ» ሳይዘኝ አይቀርም» ይላል በራሱ ሲቀልድ። ለቴዎድሮስና ቢጤዎቹ «ሜኑ-ፎቢያ» ኹነኛ ፈውስ የኾኑት «ማዘር ቤቶች»ናቸው። ቴዎድሮስ ከማዘር ቤቶች ጉያ ከወር እስከ ወር የማይጠፋ ታማኝ ልጅ እንደኾነ ሲናገር በኩራት ነው።

## የቃሉ ድፍየና (definition)

«ማዘር ቤቶች» ተማሪዎች እና ሠራተኞች በሚበዙባቸው አካባቢዎች በብዛት የሚገኙ እና ተመጋቢዎች በስማ በለው የሚሄዱባቸው ስም-አልባ አነስተኛ ምግብ ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ቤቶች ውስጥ በባለቤትነት አልያም በምግብ አብሳይነት የሚታወቁ አንድ «እናት» አይታጡም። እነዚህ እናቶች የቤቱ «አድባር» ኾነው ስለሚታዩ «ማዘር» በመባል ይጠራሉ። ብዙዎቹ ማዘር ቤቶች በባለቤቶቹ የግል መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሚቀረቆሩ ምግብ ቤቶች ሲኾኑ ለአገልግሎታቸው የሚጠይቁት ዋጋም እንጻራዊ በኾነ መልኩ « አነስተኛ» ነው። ማዘር ቤቶች ብዙዉን ጊዜ ቋሚ ደንበኞች ስላሏቸው ከተመጋቢዎች ጋር ከፍተኛ የመተማመን ስሜት እና ቤተሰባዊነትን መፍጠር ችለዋል። በዚህም ምክንያት በአንዳንድ ማዘር ቤቶች ሂሳብ በቅድሚያ መጠየቅ እንደ ነውር ይቆጠራል። ተመጋቢውም ቀድሞ ከተጠየቀ ሊከፋው ወይም ሊያኮርፍ ይችላል

## ብሔር -ተኮር ማዘር ቤቶች

አንዳንድ ማዘር ቤቶች በአካባቢያቸው ያሉ ነዋሪዎችን «፡ወንዛዊነት» ተመርኩዘው የሚፈጠሩ ናቸው። ለዚህ እንደ አብነት ከሚጠቀሱት መካከል የትግራይ ተወላጆች በሚበዙበት ተክለኃይማኖት አካባቢ የሚገኘው «አደይ ቤት» ነው። በትግራዊ ሹሩባ አሠራር ተውበው ደንበኞቻቸውን ለማስተናገድ ተፍ ተፍ የሚሉት እና በዕድሜ ጠና ያሉት የቤቱ እማወራ (ዐደይ) ላለፉት ዐሥር ዓመታት ደንበኞቻቸውን መግበዋል።

ዐደይ በእነዚህ ዓመታት ኹሉ አንድም ቀን የፍስክ ምግቦችን አላቀረቡም። ሽሮ፣ ክክ፣ምስር፣ ተልባ በእንጀራ፣ ጎመን እና ሕልበት (ከአብሽ የሚሰራ) ምግቦችን እንደልብ ለደንበኞቻቸው አቅርበዋል።ዐደይ ቤት የኹሉም ዐይነት ምግቦች ዋጋ ሰባት ብር ነው።

የወላይታ እና የዶርዜ ብሔረሰቦች በሚበዙባቸው ሽሮ ሜዳ እና አዲሱ ሚካኤል ጀርባ ባሉ ሠፈሮች ብሔር- ተኮር ማዘር ቤቶች በብዛት ይገኛሉ። ደንበኞቻቸው «አዬ» ብለው ይጠሯቸዋል። በዶርዝኛ «እናት» እንደማለት ነው። በእነዚህ ማዘር ቤቶች ለብሔረሰቡ ቅርብ የኾኑ እንደ «በሶ»፣ «ቦርዴ» እና «ፈቴሌ» የመሳሰሉት ምግቦችና መጠጦች ይዘወተራሉ። ዋጋቸውም ሁለት ብር ከ50 ሳንቲም ነው። ፈቴላ የሚባለው ጎመን፣ በቆሎና ድንች ተቀላቅለው በጆግ የሚቀርብ ጣፋጭ ምግብ ሲኾን ተመጋቢው ዘይት ከራሱ በትንሽ ብልቃጥ ይዞ መምጣት ይኖርበታል።

## ማዘር ቤቶች በመሥሪያ ቤቶች

ከአንበሳ ግቢ ከፍ ብሎ በሚገኘው የኢኮኖሚ እና ልማት ትብብር ሚኒስትር መሥሪያ ቤት በር ላይ ዘወትር ስድስት ሰዓት ላይ በርካታ ግሰቦች ይኮለኮላሉ። ሰዓቱ እየገፋ በመጣ ቁጥር ደግሞ ረዘም ያሉ ሰልፎች የተመልካችን ዐይን ይስባሉ። ከዚህ ቤት ሰልፉ መበርታቱ የሚታደል ብር ኖሮ አይደለም። መስሪያ ቤቱ በጉያው ማዘር ቤት በማቋቋሙ እንጂ።

ከመስሪያ ቤቱ ተሰላፊዎች መሀል የሁለተኛና የሦስተኛ ዲግሪያቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እየሠሩ የሚገኙ ወጣት እና ጎልማሳ ምሁራን ይበዙበታል። ከፊሎቹም ለትምህርት የሚረዷቸውን ላፕ-ቶፕ ኮምፒውተሮቻቸውን በትከሻቸው እንዳዘሉ ነው ከዚህ ቤት የሚታደሙት። « እዚህ ንጹህ ምግብ በርካሽ ዋጋ ታገኛለህ» ይላል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪውን እየሰራ ያለው ታዲዮስ ገዛኸኝ።

አንድ ልሙጥ ሽሮ 5.00 ብር፣ ሥጋ ወጥ በአይነት በአይነቱ ከ6.00 ብር እስ 8.00 ብር ይገኛል። ከ10.00 ብር በላይ ዋጋ የሚጠይቅ የምግብ ዐይነት የለም። ለየምግብ ዐይነቱ ራሳቸውን የቻሉ ዘለግ ያሉ ሰልፎች ይፈጠራሉ። የሥጋ ሰልፍ፣ የሽሮ ሰልፍ፣ የፓስታ እና የማኮሮኒ ሰልፍ ወዘተ...። አስተናጋጆች የመጠጥ ዉኃ ከማቅረብ የዘለለ ተግባር የላቸውም። ኹሉም ደምበኛ የሚፈልገውን ዐይነት ምግብ ለማግኘት ሰልፉን ጠብቆ ወደ መስኮቶቹ በመቅረብ ወጥ የማስጨለፍ ግዴታ አሰበት።

ወ/ሮ እቴነሽ ሰፈሳ በዚህ መሥሪያ ቤት ለ17 ዓመታት ያህል የወጥ ጨላፊ በመኾን አገልግለዋል። ተስተናጋጆች እርሳቸውንም ኾነ ባልደረቦቻቸውን እንደ እናት እንደሚያይዋቸው ይናገራሉ።

አጨላለፍ ላይ መጠነኛ አድልዎ ይፈፀማል የሚለውን የአንዳንዶቹን ቅሬታ አይቀበሉትም።« ለኔ ኹሉም ተመጋቢ እኩል ነው...ዕድለኛ የኾነ አጥንት ይደርሰዋል። እጄ እንዳመጣልኝ ነው የምጨልፈው» ይላሉ። የዚሁ መሥሪያ ቤት «እህት ኩባንያ» የኾነውና አምስት ኪሎ አካባቢ የሚገኘው የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር መሥሪያ ቤት ተመሳሳይ አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህ መስሪያ ቤት ማዘር ቤት ኹሉንም የምግብ ዐይነቶች ከ10.00 ብር በታች ማግኘት ይቻላል። ለሠርግ ድግስ ሊከራዩ የሚችሉ እና በአንድ ጊዜ ሁለት መቶ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችሉ የመሥሪያ ቤቱ አዳራሾች ዘወትር በምሳ ሰዓት ጢም ብለው ይሞላሉ። ኹሉም ደምበኛ በዕድር ቤቶች በብዛት የምናያቸውን አይነት ሳህኖች እያነሳ ምሳውን እያስጨለፈ ተመግቦ ሲያበቃ በርካሽ ለመመገብ ያስቻሉትን ፈጣሪን እና ግዙፉን መሥሪያ ቤት ሽቅብ እያየ ውልቅ ይላል።

በእነዚህ ሁለት እህት የመሥሪያ ቤቶችና ማዘር ቤቶች በቀን እስከ አምስት ኀላ ድስት ( ግዙፍ የድግስ ድስት) ሽሮ እንደሚያልቅ የቤቱ ታማኝ ጨላፊዎች ነግረውኛል።

ውልና ማስረጃ ጽሕፈት ቤት፣ ፈተናዎች ድርጅት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ምንሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኹሉም በውስጣቸው ማዘር ቤቶችን የፈጠሩ ተቋማት ናቸው። በተለይ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት የሚገኘው «ማዘር ቤት» አንድ ክትፎ በ12.00 ብር በመሸጥ ዝናን አትርፏል። የምግብ ቤቱ ባልደረባ የኾኑት አቶ የሺጥላ ክትፎ ከ9.00 ብር ወደ 12.00 ብር የገባው በቅርቡ ከተከሰተው የኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ እንደኾነ ይናገራሉ። አቶ የሺጥላ ምግብ ቤቱ ከማንም ምንም አይነት ድጎማ እንደማያገኝ፣ ኾኖም ከብዛት ለማትረፍ በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ እንደሚያቀርብ ይናገራሉ። በዚህ ቤት ሩዝ በሥጋ በ6.00 ብር ብቻ ማግኘት ይቻላል። ይህን «ማዘር ቤት» አንዳንድ ደንበኞች «እምዬ ምንሊክ» እያሉ ይጠሩታል።

## የወጥ ጭማሪ

ማዘር ቤቶች ከደምበኞቻቸው ጥቂት ገንዘብ ተቀብለው ብዙ እናታዊ መስተንግዶ በማቅረብ ይሞካሻሉ። በተለይም ያለ ገደብ የወጥ ጭማሪ ማድረጋቸው የእናትነታቸው አንድ መገለጫ ተደርጎ ይወሰድላቸዋል። « መረቅ ከተጨመረልህ ምን ትፈልጋለህ?» ይላል የማዘር ቤቶች ውለታ የበዛበት ቴዎድሮስ። ይህ ያለ ገደብ የሚለገሰው የወጥ ጭማሪ ግን በኹሉም ማዘር ቤቶች የሚገኝ አይደለም። ለምሳሌ ከተቋማዊ ማዘር ቤቶች አንዱ በኾነው የገንዘብ እና ልማት ትብብር ሚኒስትር ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘው ምግብ ቤት መግቢያ ላይ እንዲህ ተጽፎ አንብቤያለሁ፡- « በቂ ወጥ የምንጨልፍ ስለኾነ ጭማሪ ወጥ አናስተናግድም።»

## ያፈነገጡ ማዘር ቤቶች

ብዙ ማዘር ቤቶች በየጊዜው የሚሰፈነጠረውን የዋጋ ንረት መቋቋም ተስኗቸው አልያም በየዕለቱ የደምበኞቻቸው ቁጥር እያሻቀበባቸው ከማዘር ቤትነት ሊያፈነግጡ የሚችሉበት አጋጣሚ አለ። እንደ እነዚህ ዐይነት ማዘር ቤቶች የደምበኞቻቸውን ብዛት ለመቋቋም ሲሉ ቀስ በቀስ ዋጋ ጭማሪ ያውጃሉ፣ ሜክሲኮ አካባቢ የሚገኘው « እናት ጓዳ» የተሰኘው ምግብ ቤት ምናልባት ከእነዚህ ተርታ የሚመደብ ነው። ከሁለት ዓመት በፊት በዚህ ምግብ ቤት የአንድ ቀይ ወጥ ዋጋ 6.00 ብር የነበረ ሲኾን አሁን 14.00 ብር ደርሷል። ከዚህ የዋጋ ጭማሪ በኋላ ምግብ ቤቱ ከማዘር ቤትነት እንዳፈነገጠ ቢታመንም ዛሬም ድረስ በደምበኛ ብዛት መተንፈሻ ያጣ ሬስቶራንት ይመስላል። መጠሪያ ስሙ አሁንም ድረስ «ማዘር ቤት» ኾኖ ፀንቷል።

## እንግዳ የምግብ ስያሜዎች

ማዘር ቤቶች በብዛት ማንነታቸውን የሚገልጽ የስም ማስታወቂያ ከደጃፋቸው አይሰቅሉም። እውቅ የሚኾኑት በሚያስነግሩት ማስታወቂያ ሳይኾን በዝቅተኛ ዋጋቸው አማካኝነት በሚመጣ ዝና ነው። አንዳንድ ማዘር ቤቶች ደግሞ ለምግቦቻቸው በሚሰጡት እንግዳ ስያሜ ይበልጥ ይታወቃሉ። «ከሸን»፣ «የተቀመመች»፣ «ስፔሻል»፣ «ዘመናዊ»፣ «ሽሮ በከረባት» ... ወዘተ በማዘር ቤቶች የሚገኙ የተለመዱ የምግብ ስያሜዎች ናቸው። ጎጃም በረንዳ አካባቢ ያለ አንድ ስም አልባ «ማዘር ቤት» ቼልሲ እና አርሴናል የሚባሉ ምግቦችን ያቀርባል። አጥንት ያልገባበት ረከስ ያለ የሥጋ ወጥ «ቼልሲ ያለ ድሮግባ» የሚል ስም ተሰጥቶታል። «አንድ ቼልሲ፣ ላምፓርድ በዛ ብሎ» ማለት ደግሞ አልጫው በዛ ያለ ሚስቶ እንደማለት ነው።»

## የፆም ሥጋ

ቴዎድሮስ ማዘር ቤቶችን ከሥጋ ነክ ምግቦቻቸው ይልቅ የፆም ምግብ ይዋጣላቸዋል ብሎ ያምናል። ሽሮ፣ በየዐይነቱ፣ ፓስታ በእንጀራ፣ ምስር ወጥ በግሩም ኹኔታ፣ በርካሽ ዋጋ የሚቀርቡባቸው እነዚህ ማዘር ቤቶች የሥጋ  ምግብ ዘርዝሮቻቸው ግን በጥራታቸው እና

በሥጋ ከምችታቸው ብዙም የሚጨበጨብላቸው እንዳልኾኑ ተጠቃዎች ይስማሙበታል። በማዘር ቤቶች በቀይ ወጥ፣ ሚስቶ፣ ምንቸት እና ተመሳሳይ የምግብ ዐይነቶች የሚገኘው የሥጋ ከምችት አነስተኛ ከመኾኑም በላይ ከሲታ ሥጋዎች ይበዙበታል።ቴዎድሮስ እነዚህን ሥጋዎች «ዖም የሚገድፉ አይመስለኝም». ሲል ይሳለቅባቸዋል። በማዘር ቤቶች የሥጋ ወጦች ውስጥ የደረጁ ሥጋዎችን በበቂ ኹኔታ ያለማግኘት ምክንያት ምናልባትም ወጪያቸውን ለማካካስ የሚያደርጉት ሙከራ ሊኾን ይችላል ተብሎ ይገመታል።

አንዳንድ የማዘር ቤት አዘውታሪዎች በምግብ ቤቶቹ የሚያነሷቸው ቅሬታዎች አሉ። «በርበሬያቸው ያለ ልክ ይፋጃል፣ ከተመገቧቸው በኃላ ቅባታቸውን ለማስለቀቅ ዘለግ ላለ ሰዓት እጅን በሳሙና የመፈተግ ሥነ-ሥርዓት ማካሄድ ያስፈልጋል» ይላሉ። ማዘር ቤቶች ለዋጋ ሲሉ ንጹህ ባልትና መጠቀማቸውን የሚጠራጠሩም አልጠፉም። ቴዎድሮስ ይህንን ክስ ፍፁም የሚቀበለው አይመስልም። « እናት ለልጇ ያንን አታደርግም» ሲል በዚህ እሳት በኾነ ኑሮ በነፍስ የደረሱለትን ማዘር ቤቶች ያሞካሻል።

© ይህ ዘገባ ጥር 23፤2001 ታትሞ በነበረው የአዲስ ነገር ጋዜጣ የሰሻል ለምድ ስር ቀርቦ እንደነበረ ይታወሳል።

# የጀሚላ መዳፎች

አዲሳባ፤ ቦሌ መድኃኒዓለም፤ ውድቅት ሌሊት፤

ፀጥ ረጭ ባለው ሰፈር፤

በግራ እና በቀኝ የተሰደሩት ቪላ ቤቶች ግዙፍ የጋራ በር አላቸው ፤ አንድ የጥበቃ አባል በእነዚሁ የቪላ ቤቶች የወል በር ላይ ቁሞ ገቢ ወጪ መኪናዎችን ይቃኛል። ‹‹ፀጉረ ልውጥ» ታርጋ እንዳይገባ በንቃት የሚከታተል ይመስላል። የጥበቃው ነገር በዚህ አያበቃም። ይባስ ብሎ እያንዳንዱ ቪላ ቤት በተናጥል የራሱ በርና በረኛ ተመድቦለታል። "የተሳካላቸው" ብቻ የሚኖሩበት መንደር መኾኑን ከአካባቢው የሚተነው ዝምታ የዋጠው አየር ያሳብቃል።

በስተግራ አራተኛዋ ቪላ ቤት ግን የተለየ ባሕርይ ይታይበታል። የቪላ ቤቱ በር ገርበብ ተደርጎ የተተወ ነው። ደጅ ላይ ጥቂት መኪናዎች ተኮልኩለዋል። ይህ ቤት የሚታይ፣ የሚዳሰስ በረኛ የለውም። በውስጡ ግን ብዙ ዳሳሽ መዳፎች አሉበት። ለምሳሌ የጀሚላ ተዐምረኛ መዳፍ!

## ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት . . .

ወደ ውስጥ ሲዘለቅ ከሳሎኑ በራፍ ላይ የተሰቀለው የእንግሊዝኛ ማስታወቅያ በደብዛዛ የአምፖል ብርሃን ውስጥ እንዲህ ይነበባል፡፡ "Close the door please! It is cold these days!" የሰሞኑ ብርድ ለጉድ ነው! እባክዎ በሩን ይዝጉት! እንደማለት፡፡ በትንሹ ገርበብ ያለው የሳሎን በር ሲከፈት ቀጭኗ ኮሪደር "ሪሰፕሽን" የሚል ጽሑፍ ከአናቷ ወደተሰቀሰባት ጠባብ ክፍል ታደርሳለች፡፡ በዚች ቀጭን ክፍል ደግሞ ሸንቀጥ ዘለግ ያለች ቆንጆ ተሰይማለች፤ ሕይወት ባለው ፈገግታ ተቀበለችን፡፡

«ምን ልታዘዝ!?»

ሰደንቡ ነው እንጂ የምንፈልገውን ጠንቅቃ ታውቀዋለች፡፡ አጠያየቋ በመረጃ እንደመጣን ለማረጋገጥ ያህል ነው፡፡ በዚህ ውድቅት መቼስ ማኅሌት ለመቆም እንዳልመጣን እኛም፤ እርሷም፤ ሰይጣንም እናውቃለን፡፡ ሻወር አስቀድመን መውሰድ እንደምንፈልግ ከጠየቀችን በኋላ ክፍሎቻችንን አመላከተችን፡፡ በቂ ፎጣዎች፤ የሻወር ጋውን እና ሌሎች የንጽሕና መጠብቂያ ቁሳቁሶችን የተሟሉ መኾናቸውን ዐሳየችን፡፡

"ሻወር ወስዳችሁ ስትጨርሱ አስተናጋጆቻችሁ በየክፍላችሁ ይጠብቋችኋል!
መልካም ምሽት ይኹንላችሁ!"

የበረራ አስተናጋጆችን ዐይነት ቅልጥፍና ይታይባታል፡፡ የሚዘናፈለው ፀጉሯ ወደፊት እየመጣ ሲያስቸግራት አንገቷን ወዝወዝ አድርጋ ትመልሰዋለች፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጣቶቿ ሰብስብ አድርጋ ወደ ጆሮዎቿ የኋሊት ትሰበስበዋለች፡፡ ከአፍታ በኋላ ፀጉሯ መልሶ ወደፊት ብትን ይልባታል፡፡ ዳግም ከአንገቷ ወዝወዝ ትልና ጆሮዎቿን ለሚበተነው ፀጉሯ እንደ ‹‹ታኮ››ትጠቀምበታለች፤ ዘንፋላው ፀጉሯ ቶሎ በጇ አይላትም፡፡ ዳግም አደብ ሊታሲዘው ትሞክራለች፡፡

እንግዶችን በአንደበቷ ብቻ ሳይኾን በጥርሷ፣ በዐይኗ እንዲሁም በፀጉሯ መንከባከብን ታውቅበታለች፡፡ ሥራ የሚፈታ የሰውነት ክፍል የላትም፤ ዳሌዋን ጨምሮ፡፡

"ይቅርታ ሂሳብ ቅድሚያ ነው! በሰው 250 ብር!"

## በሻማ ብርሃን "ማይም ተውኔት"

ሻወር በቅጡ መውሰዴ ትዝ አይለኝም፡፡ ኾኖም ቀጥሎ ለሚኾነው ነገር ጉጉት ያደረብኝ እንዳይመስል ከሻወር ቤት ዘለግ ላለ ሰዐት ፀናሁ፡፡ ያውም ሥራ ፈትቼ፡፡ አእምሮዬን ስራ ለመስያዝ ያህል በፍቃዴ በሀሳብ ነጎድኩ፤ ሻወር ቤቱ በምናብ አጥለቀለቀኝ:: ለእኔ ሽንት ቤት፣ ሻወር ቤትና የመኝታ ቤት ኮርኒስ በሀሳብ ለመመሰጥ ሁነኛ ስፍራዎች ናቸው::

መአዛ ያለው የገላ ሳሙና በገላዬ ላይ ሸርተቴ ይጫወታል:: ከሻወር ቤቱ ቧንቧ በሶስት አቅጣጫ ወደ ገላዬ የሚወረወሩት በፏፏቴ የሚመስሉ የውሀ ሸንተረሮች ሰውነቴ ላይ ሲያርፉ ልዩ ስሜት ፈጠሩብኝ:: የዘመኑ ሲራራ ነጋዴ የኾኑ የመርካቶ ፓስፖርት ያላቸው ወዳጆቼ ወደ ታይላንድ አብዝተው የሚበሩት ጂንስና ጫማ ለመሸመት ብቻ እንዳልኾነ አጫውተውኛል:: እዚያ ሄደው ያዩትን፣ ያደረጉትን፣ የሚደረገውን ሲያወሩኝ መደመሜ አልቀረም::  የሀበሻ ዲታ ነጋዴዎች ታይላንድን የሚያዘወትሩት ስኳራቸው ለመለካት ብቻ እንዳልኾነም በሽሙጥ እየሳቁ ነግረውኛል:: ወደዚህች ቤት ይዘውኝ የመጡትም ታይላንድ ካሏት የትየለሌ ከራማዎች ውስጥ አንዱ በአዲሳባ መከፈቱን በመስማታቸው ነው:: ጉጉቴ ናረ! ድንገት ከሻወር ቤቱ ተስፈንጥሬ ወጣኹ::

ቆንጆዬዋ አስተናጋጅ በጠቆመችኝ መሰረት ወደ ተመደበልኝ ክፍል አቀናኹ:: « ስቱዲዮ - B»፤ ቁንጠኛው በር ገርበብ ብሎ አገኘኹት:: ውስጡ ጭልጭል የሚል የሻማ ብርሃን፣ በጭልጭል የሻማ ብርሃን ውስጥ ደግሞ ለግላጋ ሴት፣ ከርሷ ሥር በአየር የተወጠረ እና ያበጠ የላስቲክ ፍራሽ ጠበቀኝ፡፡  ያልጠበቁት ነገር ነው:: ልጅቱ መደናገጤን ዐይታ ነው መሰለኝ በከፊል ፈገግ አለች፡፡ ወይም ፈገግ ያለች መሰለኝ፡፡

"ሃይ! ጀሚላ እባላለሁ፡፡ ለምሽቱ አስተናጋጅህ ነኝ" ቁንጠኛ ትመስላለች፡፡ በቁንጠኛ አረማመድ ሶስት እርምጃዎችን ከተራመደች በኃላ ገርበብ አድርጌ ትቼው የነበረውን በር ቆለፈችው::

ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለማሰብ በምዘጋጅበት ቅፅበት የሻወር ጋውኔን ገፈፈችው:: መለመላዬን እንዳልቀር በምትኩ የማጣፋው ስስ ፎጣ ሰጠችኝ። ፎጣ ከሚባል ሻሽ ቢባል ይቀላል::

ሁኔታዬን ለአፍታ ከገመገመች በኃላ " ካልወደድከው መተው ትችላለህ" ስትል ወንድነቴ አካባቢ ወዳጣፋኹት ስሱ ፎጣ እየጠቆመች አበሰረችኝ። ኹኖም ፎጣው ለጊዜው እንዲቆየኝ መረጥኩ። አፌ ነው እንጂ ውስጤ በዚህ ውሳኔዬ የተፀፀተ ይመስለኛል::

በአየር በተወጠረው የላስቲክ ፍራሽ ላይ በሆዴ እንድተኛ ካዘዘችኝ በኋላ ዙርያውን ከተደረደሩት ደርዘን ሻማዎች የተወሰኑት በማክሰም የክፍሉን ሰልምልም ብርሃን ይበልጥ አደበዘዘችው። ሻማዎቹ አጫጭርና ቄንጠኛ ናቸው:: የክፍሉ ማብሪያና ማጥፊያ ደግሞ የኳስ ቅርፅ ነው ያለው:: ወደ ግራ ሲሽከረከር የክፍሉ ብርሃን ከአርባ ሻማ ወደ ዜሩ አምፑል ይቀየራል:: ኹኖም አሁን የአምፑል ብርሃኖቹ ሙሉ በሙሉ ጠፍተው በሻማ ብርሃን ነው ያለነው:: የሻማ ብርሃኑ በዐይን ቋንቋ ለመግባባት እንኳ የሚኾን በቂ ብርሃን አይረጭም፤ በመኾኑም የመግባቢያ ቋንቋችን ወደ መዳፍ ተቀየረ። ጀሚላ ‹‹መዳፍኛ›› በሚባል ባእድ ቋንቋ ታናግረኝ ጀመር። የማይም ድራማው ፊሽካ ተነፋ።

እጅግ በስሱ የሚንቆረቆረው በመሣርያ ብቻ የተቀነባበረ የሩቅ ምሥራቅ ሙዚቃ አልፎ አልፎ በምታቃስት የሴት ድምፅ ታጅቦ ከክፍሉ አንድ የኾነ ጥግ ላይ በተወሸቀ "ስፒከር" እየተሞዘቀ ነው። ስፒከሩን ማየት ግን አልቻልኩም:: ኮርኒሱ ላይ ይኹን አሊያም የክፍሉ ግድግዳ ላይ የሙዚቃው ምንጭ ከየት እንደኾነ ማወቅ ተሳነኝ:: ሙዚቃው የቤቱ ግድግዳ ሲተነፍስ የሚወጣ ድምፅ ሳይኾን አይቀርም:: የቤቱ ግድግዳ ሲሰራ ውስጡ የማይታይ፣ የማይዳሰስ የድምፅ ማጉያ ተገጥሞለት እንደኾነ ጠረጠርኩ:: በዚህ አይነት ድብቅ ካሜራ በክፍሉ አንዳች ጥግ እንዳልተገጠመ በምን ርግጠኛ መኾን ይቻላል? የዚህ ቀስቃሽ ሙዚቃ የድምፅ ምጣኔ እውነትም ከሩቅ ምሥራቅ ከተከፈተ አንድ መለስተኛ ቴፕ ባህር አቋርጦ የሚሰማ ነው የሚመስለው። እጅግ ዝቅ፣ዝግ ተደርጎ የተከፈተ ሙዚቃ በመኾኑ ኪጆሮ ሳይኾን ከመንፈስ ይዋኃዳል!

ጀሚላ ልዩ መዓዛ ባለው የክሬም ቅባት በስሱ ትዳብሰኝ ጀመር። አስተሸሸቷ መታሸት ከሚለው ቃል ይልቅ መነካካት፣ መፈታተን እና መዳራት ለሚሉት ቃላት በጣሙን ይቀርባል። ቀጥላ የውስጥ እግሬን በረዣዥም ጥፍሮቿ መጠነቋቆል ጀመረች። በባለ መዐዛው ክሬም ጀርባዬን ካሸችኝ በኋላ ከማጅራቴ ጀምሮ ቁልቁል በጥፍሮቿ እንደመቧጨር፣ እንደመቧጠጥ እንደ...ወዘተ አደረገችኝ። ሰውነቴ ቀስ በቀስ ምላሽ ሰጠ።

ትዕይንቱ ከአፍታ በኃላ እኔን በጀርባ ወደ ማጋደም ተዛወረ። የመሀል ጣቷን ጆሮዬ ውስጥ በመጨመር የተለየ ትርጉም ያለው መልእክት ልታስተላልፍልኝ ሞከረች። አንገቴ አካባቢ ጥሩ ስሜት የፈጠረብኝን አንዳች ነገር አድርጋ ወደ ደረቴ ተንደረደረች። ተመልሳ ደግሞ የመሀል ጣቷን በጆሮዎቼ በመጨመር ቀድሞ እንዳደረገችው ስሜቴን ለማናር ጣረች። የደረቴን ፀጉሮችና ጡንቻዎች በስሜት ታሻቸው ጀመር። ከክሬሙ በቆንጥ በጣቷ ትጠነቁልና የደረቴ ጡቶች ላይ በማሳረፍ በጥፍሮቿ ጫፉን ብቻ እየነካካች ንዝረት ለመፍጠር ታተረች፤ ተሳካላትም። ከዚህ በኋላ እኔን ፍፁም ረስታ ከደረቴ ትናንሽ ጡቶች ጋር እቃ-እቃ መጫወት ጀመረች።በአለንጋ ጣቶቿ ነካክታ የኾነ ነገር ስትላቸው ይመልሱላታል፣ይስቁላታል፣ ይቆሙላታል። እኔን ጭራሹን ዘነጉኝ:: ጀሚላ ይህንን ስታደርግ እንደስራ ሳይሆን ለነፍስና ለፅድቅ ይመስልባት ነበር ።

ረዘም ላለ ደቂቃ በደረቴ ሜዳ ስትፈነጭ ቆይታ ድንገት ቁልቁል ተንደረደረች። ስሷ ፎጣዬም ደጀንነቷ አከተመ። በፈቃዱ ተንሸራተተች። ሽምቅቅ አልኩኝ።

"ታፍራለህ እንዴ!"

እ . .!?

"ታፍራለህ? መሳሻ የመጀመርያህ ነው?"

"ኖ! ኖ !" ሽምጥጥ አድርጌ ዋሸኋት

"ሻማ ትፈልጋለህ?"

"አይ ይቅርብኝ!"

የጠረጠርኩትን ብጠረጥርም በልቤ ሻማ ስለተባለው ጉዳይ ተጨማሪ እውቀት ፈለኩ።

ሻማ በዚህ ምስጢረኛ ቤት ሳሙና ኾኖ እንደሚያገለግል አጫወተችኝ። እየቀለጠ ያለ ሻማ የወንድ ሰውነት ላይ ሲፈስ መልካም ስሜት እንደሚፈጥር አወራችኝ። በቅላጩ የሻማ ጠብታ ሲቃይ ውስጥ መልካም ስሜትን ለመፍጠር የሚደረግ ጥበብ ነው። እንደ ጀሚላ ማብራሪያ ብዙዎቹ የውጭ ዜጎች በተለይም በእድሜ ገፋ ያሉት "የሻማ ስቃይ" ነፍሳቸው ነው። እነዚህ ደንበኞቿ፣ ሳያቸው ላይ በሚቀልጠው የሻማ ሲቃይ ውስጥ ደስታቸውን ያበራሉ። በብዛት አረቦች ብቻ አይደሉም የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ በስም ልትጠራቸው ያልፈቀደቻቸው ጥቂት ታዋቂ ሀበሾችም የጀሚላ እና የሻማዋ ቋሚ ደንበኞች ናቸው።

"እንደ ሺሻ ነው፤ አንዴ ከለመድከው ሱስ ይኾናል"

"እውነትሽን ነው?"

«እህ! ጭንቅላቷን በመነቅነቅ አዎንታዋን ገለጸች፤

ከተሰጠኝ አጭር የሻማ ገለጻ በኋላ ነገርየውን የመሞከር ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ፤ ኾኖም አንዴ ይቅርብኝ ስላልኳት ዳግም ለመጠየቅ ኩራት ተናነቀኝ። ለሰከንዶች ያህል ኩራትና ፍላጎት ተፋለሙ፤ ኩራት አሸነፈ።

## የተውኔቱ ጡዘት እና ፍጻሜው

ጀሚላ በመዳሮቿ ካልኾነ ብዙ አታወራም። ለጥያቄዎቼ ግን በሹክሹክታ አጠር ያሉ ምላሾችን ትሰጠኛለች።

«ጋዜጠኛ ነህ?»

«ምነው ጥያቄ አበዛኹ?»

«እንደዛ ነገር! ደሞ መሳዥ ላይ ብዙ አይወራም፣ ዝም ነው የሚባለው»

ጀሚላ ማሳጅን በቅንጦት ስትጠራው «መሳዥ» ነው የምትለው፤

«ምንድነው የምትሰራው?»

«ነጋዴ ነኝ፤ ዱባይ እመላለሳለሁ»

ዋሸኃት፤

አረብኛ አቀላጥፋ ትናገራለች። ዱባይ ለአንድ ዓመት ተኩል በግሏ በድብቅ ይህን አገልግሎት ትሰጥ እንደነበር ነገረችኝ።ቤት ለቤት አገልግሎት። እዚህ አገርም በግሏ ተመሳሳይ ስራ እንደምትሰራ ጭምር። ብዙ ከማውራት ብዙ መሥራት ትመርጣለች። ሉብር ሳይኾን ለሞያ ፍቅር የምትሥራ ነው የምትመስለው።

ከዚህ በላይ ስለራሷ ከመናገር ተቆጠበች። ትኩረቷ ሰውነቴን ወደ ማናዘዙ ላይ አደረገች። የተውኔቱ የመጨረሻ ክፍል እየተቃረበ እንደኾነ ገመትኩ። ሥራውን ተከናበታለች፤ የእግሮቼን ጡንቻዎች በክሬም በማሸት እና በማሳሳብ ዘና ካደረገቻቸው በኋላ የእግር ጣቶቼ መሀል ጣቶቿን እየከተተች ወሲባዊ መልእክት ለማስተላለፍ ሞከረች። ዐይኖቼን በመጨፈን ምላሽ ለመስጠት ሞከርኩ።

"መሳዥ ታደርገኛለህ?"

"ማንን?"

"እኔን!"

'እ!'

ቤቱን የጠቆሙኝ ሰዎች ይህ እንደሚኾን አልነገሩኝም ነበር።

"እ...ሺ! ግን አልችልበትም … ልሞክር?"

"ሂሳብ ያስጨምርኻል"

"ኸረ? ስንት?"

"200 ብር…ለኔ ነው የምትሰጠኝ! ድርጅቱ አያገባውም"

ተስማማሁ። በነበርኹበት ኹኔታ አለመስማማት አማራጭ አልነበረም። ሻሽ ከመሰለ ‹‹ናይለን» ጨርቅ የተሰራውን ስስ ጋውኗን ጨምሮ ልብሶቿን አንድ በአንድ እያወለቀች

በቆንጥ መስቀያው ላይ አንጠለጠለቻቸው። ጡት ማስያዣዋ እና የውስጥ ሱሪዋ እኔ እንዳወልቃቸው የተተው እንደኾኑ ገመትኩ። በዮጋ ዐይነት አቀማመጥ እግሮቿን አነባብራ በአየር በተሞላው ላስቲክ ፍራሽ ተቀመጠች። እኔ ከጀርባዋ ተሰየምኩ፤ ልክ በድንጋይ ወፍጮ ለመፍጨት እንደተሰናዳች እመቤት አይነት፤ በተራዬ ክሬሙን በስሱ እየጠነቆልኩ ከጀርባዋ ለማሸት ስዘጋጅ በቅድሚያ ጡት መያዣዋን እንድፈታላት ትዕዛዝ ሰጠችኝ።

«አውልቀው!»

« እ...ሺ!»

በዚያ የስሜት ንረት ውስጥ የጡት መያዣዋን ቁልፍ በትክክል በታውን አግኝቶ መፍታት ቀላል አልነበረም። ተወነባበድኩ። ቁልፉን መበጠስ አማረኝ። ጡት መያዣ ከዚያን ቀን በፊት ከፍቼም ዘግቼም አላውቅም። በዘርፉ ምንም አይነት የስራ ልምድ የለኝም። ብወናበድ ለምን ይፈረድብኛል። በእርሷ እርዳታ አወለቅኩት።

«ቴንኪው!» አለችኝ። ቆንጥ በተጫነው ድምፅ።

በጀርባዋም ኾነ በሆዷ ፍራሹ ላይ እንድትጋደም ያቀረብኩላትን ጥያቄ ውድቅ አደረገችው። በሌላ አገላለጽ እርሷን ማሳጅ ማድረግ የምችለው ከወገቧ በላይ ያለውን የሰውነቷን ክፍል ብቻ ነው ማለት ነው። የውስጥ ሱሪዋም የማይደፈር ግዛቷን የሚያስከብር ዘብ እንደኾነ ተረዳኹ። ከዚያ ዉጭ ባለው ሰውነቷ መዳፌ እንደልቡ ጋለበበት። በተጣደፍኩ ቁጥር ዝግ እንድል ታስጠነቅቀኛለች። ኾኖም መዳፎቼ የተቀዳጁት ጊዜያዊ ሐሴት እጅግ ለአጭር ጊዜ የቆየ ብቻ ነበር። ተስፈንጥራ በመነሳት የጡት መያዣዋን ትታ ጋውኗን ብቻ በመልበስ ከወገቡ አካባቢ ባለው መቀነት ሸብ አድርጋ አሰረችው።

"በስ፤ ኻላስ! ከዚህ በላይ መቆየት አይፈቀድም!"

ለአንድ ሰዓት ያህል የቆየው ጫዎታችን እየተጠናቀቀ መኾኑን በአረብኛና በአማርኛ አረዳችኝ። ድንገት ምን ያጣድፋታል?፤ ቀድሞ ከነበረኝ መረጃ በመነሳት አንድ

የማሳረግያ ትዕይንት እንደቀረ ለመገመት ቻልኩ። ልክ ነበርኩ፤ እርሷም ነገሩ ሳይገባት አልቀረም።

‹‹ቅር ያለህ ነገር አለ?»

«አው!»

«ምን?»

በአንገቴ አቅጣጫውን ጠቆምኳት። ተራራ አከሷል!

"ያስጨምርኻል!"

" ስንት!"

"መቶ ብር! ድርጅቱ አያገባውም ለኔ ነው የምትሰጠኝ፤ አኬ?"

ለድርድር የሚበቃ አቅም አልነበረኝም።

የጀሚላ መዳፎቿ የደረሱበትን የመጨረሻው የዳሰሳ ጥበብ ተጠቅመው ለስሜቴ ምላሽ ሰጡ።

ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አልን!

ሻወር ቤት ስገባ ቆሻሻ ውስጥ እንድጥላቸው የሶፍት ወረቀቶቹን ሰብስባ የሻወር ጋውኔ ኪስ ውስጥ ሞጀረቻቸው። የሶፍት ወረቀቶቹን መታጠብያ ቤት መጣል እንዳልረሳ ባልጠበቅኹት ኹኔታ ደጋግማና አጥብቃ አስጠነቀቀችኝ። ለምን ይህን ያህል አሳሰባት!? የማንን ሀጥያት ማን ይሸከማል ብላ ይኾን!?

ልብሶቼን ከመስቀያው አውርዳ በቅልጥፍና ከለባበሰች በኋላ ድርጅቱ አይመለከታቸውም ያለችኝን ለእርሷ ብቻ የሚገቡ ክፍያዎችን እንድፈጽም የኪስ ቦርሳዬን አቀበለችኝ። ሦስት የመቶ ብር ኖቶችን ሰጠኋት።

"ሹክረን ሀቢቢ! ደንበኛ እንኾናለን! አትጥፋ!»

እሺ ለማለትም አቅም አጣኹ

«ሌላ ጊዜ ከመጣህ ለሪሴፕሽኖቹ ጀሚላ በላቸው።”

ኮድ መሆኑ ነው።እንደኳስ ድቡልቡል የኾነውን የቤቱን ማብሪና ማጥፊያ ስታሽከረክረው ቤቱ በብርሃን ተንቦገቦገ።በሩን ከፍታ ከመውጣቷ በፊት ልብሶቿ እንዳልተዛነፉ ለመጨረሻ ጊዜ ርግጠኛ ለመኾን ሞከረች።

“እኔ ምልሽ?”

“አቤት!”

“ጀሚላ ምን ማለት ነው?”

“ቆንጆ ወይዘሪት . . .”

ክፍሉ ውስጥ ብቻዬን ቀረሁ። ስሜት ቀሲቃሹ ሙዚቃ አልተቋረጠም። ኾኖም እንደ ከባድ መኪና ጡሩንባ አዋኪ ድምፅ ኾኖ ተሰማኝ። ከፉኛ የጥፋተኝነት ስሜት ኅሊናዬን በረቀሰው። ክፍሉን ለባለተረኛ ዳሳሽና ተዳሳሽ መልቀቅ ነበረብኝ . . .

# ኬሻ በጠረባ

ከዚህ ቀደም የአዲስ ነገር ኀብዕ ዘጋቢዎች በአርቃን ዳንስ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች ከግዑዝ ብረት ጋር የሚያደርጉትን የወሲብ ትእዕይንት ዘግበዋል። በውቅቱ ይህንን ትዕይንት ለማየት ብዙ መቶ ብሮችን መክፈል ግድ መኾኑን ተንትነው ነበር። « በተለምዶ ኬሻ በጠረባ» በሚል ስያሜ የሚጠሩተ ቤቶች ውስጥ ግን ሙሉ የወሲብ ትዕይንቶች ሲከናወኑ ለመስማት እና ተንጠራርቶ ለማየት ኣሥር ብር ብቻ በቂ ነው» ሲሉ የአዲስ ነገር ዘጋቢዎች አብረሃም በጊዜው እና መሀመድ ሰልማን ያዩትን እና የሰሙትን እንዲህ ይተርካሉ።

—— ——

ከ«ዑመር ሰመተር ትምህርት ቤት» እስከ «ኣውቶቡስ ተራ» ባሉ ጥጋ ጥጎች ሕፃናት፣ ወጣቶችና እናቶች ተደርድረው ተቀምጠዋል። ዐይናቸው ውስጥ የገባውን ሰው « አልጋ ይፈልጋሉ?» በሚል በጥያቄ ያዋክቡታል። በዝናማማው እና ውርጭ ባዘለው ምሽት ከአልጋ አከራዮች ጎን ለጎን ራሳቸውን ለገበያ ያቀረቡ ሕፃናት ተደርድረው ፈላጊዎቻቸውን በዐይናቸው ይለማመጣሉ። ምሽቱ ወደ ሁለት ሰዓት እየተጠጋ ነበር። በመንገዱ ዳርቻ ለእራት የተዘጋጁ ምግቦች በተጣዱበት ኾነው ጭሳቸው ቡልቅ ቡልቅ ይላል። ድንች ቅቅል፣ በቆሎ ቅቅል፣ በቆሎ ጥብስ፣ ሻይ በዳቦ፣ ጠላ እና አረቄ ሁሉም በየዐይነቱ ቀርቧል፤ በመርካቶ ጎዳናዎች። ኬክ የሚመስል ነገር ጎዳና ላይ አንጥፈው «ኬክ ኣንዱ አንድ ብር!» እያሉ የሚሸጡ ነጋዴዎችም

ሰው ወደ ሌላው የሚዘሉት በከፍተኛ ኩራትና የማን አለብኝነት ስሜት ነው።

ቁንጫዎቹ እረፍት ስለሚነሱ ምንም ነገር መልበስ አያሰኝም። ለነገሩ የሚለበስም ነገር የለም። በቆጡ መኝታችን ላይ ሦስት ሰኣታት በአሰጨናቂ ስሜት አሳለፍን። የተኛ ሰው ላለመርገጥ እንደ ፈንጂ አምካኝ በጥንቃቄ እየተረማመድን ቤቱን ለቀን ወጣን።

በአካባቢው የሚሰማው ድምፅ የሌሊቱን ጸጥታ ሰላም ነስቶታል። ከአረቄና ከካርታ መጫወቻ ቤቶች የሚወጣው ድምጽ አካባቢውን የማይመሽ የማይነጋ አስመስሎታል። ወደ ደረጃ ሁለት ኬሻ በጠረባ አመራን። ለባሪያው እና እርሱን መሰል ያጡ የነጡ ድኾች በእነዚህ ቤቶች ማደር ትልቅ ፍሰሃ ነው።

በደረጃ ሁለት ኬሻ በጠረባ መኝታ ቤት ውስጥም በባሰ ሁኔታ ቁንጫ፣ ቅማል እና ትኋን የሰው ልጅ ታማኝ ወዳጆች ኾነው አገኘናቸው፤ ደንበኛን እየበሉ እና እያባበሉ ያስተኛሉ። በእነዚህ ቤቶች ለመኝታ ሁለት ብር የመክፈል ግዴታውን የሚወጣ ሁሉ የፈለገውን ጥግ ይዞ መተኛት መብቱ ነው። ሁሉም የራሱን ልብስ እንደ ብርድ ልብስ ለብሶ የመተኛት ግዴታ ተጥሎበታል ። በእነዚህ ቤቶች ማንም ካለ ምንም ልዩነት ማደር የሚችል ሲኾን ስለ ቤቱ አስተያየትም ኾነ ቅሬታ መስጠት ግን ፈጽሞ አይፈቀድለትም። በዚህ ኬሻ በጠረባ ልዩ ደንበኛ የሚኾኑ ደንበኞች የዱቤ አገልግሎት ይሰጣቸዋል።

የኬሻ በጠረባ ሰፈር ሴቶች የአያትነትን ፀጋ የሚጎናጸፉት ከ30 እስከ 35 ዓመት ባለው ዕድሜያቸው ነው። ከ15 ዓመት በታች የኾናቸውን እናቶች እዚህም እዚያም ማየት የተለመደ ነው። «የእነዚህ ልጆች አባቶች እነማን እንደኾኑ አይታወቅም» ይላል አንድ የአካባቢው ተወላጅና ነዋሪ።

## የኮርኒስ አልጋዎች

ከቀድሞው «ፋሲል ፋርማሲ» ጀርባ ባለው 32 ቀበሌ የመኝታ ተጠቃሚ የሚኾን ሰው ደረጃው ከፍ ያለ ነው፤ አንድ አልጋ ከሰባት ብር እስከ አስር ብር ያስከፍላል። « አልጋ አልጋ» የሚሉት የሕጻናትና የእናቶች ድምጽ በየሁለት እና ሦስት ሜትር ርቀት ላይ ይሰማል። 34 ቀበሌን እየሰነጠቅን ወደ ውስጥ ዘለቅን። ብዙ ቤቶች እርስ በእርሳቸው ተዛዝለዋል። አብዛኞዎቹ

አልጋ ቤቶች በብጣሽ መጋረጃ የተከፋፈሉ አልጋዎች አሏቸው። የምንፈልገውን ዐይነት ቤት ስላላገኘን በግምት 12 ዓመት ወደሚኾናት አልጋ አከራይ ጠጋ ብላን እርዳታዋን ጠየቅናት። የስድስተኛ ክፍል ተማሪ የኾነችው አልጋ አከራይ ሥራውን የወረሰችው ከቤተሰቦቿ ነው።

መጀመሪያ ፍርሃት ይነበብባት ነበር። በጨዋታ አብረናት ጥቂት ደቂቃዎችን ስናሳልፍ መሳቅ መጫወት ጀመረች። እኛም ፍቅረኛሞች ወይም ሴት ገዝተው የሚመጡ ጎረምሶች ያሉበት ክፍል ማደር እንደምንፈልግ ሹክ አልናት። እንደ ማመንታት እያለች« እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት መቆየት ይኖርባችኃል» የሚል ምክር ለገሰችን። ጉዟችንን ልንቀጥል ስንል « ሴት ይዘው የሚመጡ ሰዎችን ተከትሎ ከእነርሱ ጎን አልጋ መያዝ ይቻላል» ስትል በለሆሳስ ሹክ አለችን። ተስማማን።

ቀን ቀን በሕዝብ ተጨናንቀው እና ተጣበው የሚታዩት የመርካቶ አውራ ጎዳናዎች ምሽት ላይ ይንቦረቀቃሉ። 24 ሰዓት የወሲብ ሽያጭ የማያቋርጥበት የአውቶቡስ ተራው «12 ቀበሌ» የማታ ተረኞችን በዜሮ አምፖል በተደናገዙ ክፍሎቹ ያስተናግዳል። የወሲብ ሽያጭ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ትንቅንቅ የገጠመ ይመስላል። ሁለታችንም ዋጋ ለማጣራት በተለያየ አቅጣጫ ተሰማራን። የአጭር ጊዜ ቆይታ /short/ በዐስር ብር፣ የአዳር ዋጋ ከ30 እስከ 60 ብር ይዋዥቃል።

በአዲስ ከተማ ት/ቤትና በቴሌው መስሪያ ቤት ግምብ ሥር በርከት ያሉ ሕጻናት፣ጠና ያሉ ባልቴቶች፣ወፍራም፣ቀጫጭን፣ ቀንጆ፣መልከጥፉ ሴቶች በአይነት በአይነቱ ተደርድረዋል። ሴት የፈለገ በዐይኑ ቃኝት እያደረገ ይመርጣል። ልቡ የከጀላትን ሄዶ ዋጋ ይደራደራል። ሰዓቱ ከምሽቱ አራት ሰዓት ኾኗል። ሁለታችንንም የማታው ቅዝቃዜ ውስጣችን ገብቶ እያንዘፈዘፈን ተደራዳሪዎችን በአንክሮ እንከታተላለን። አንዱ ድርድር የተሳካ ይመስልና ይፈርሳል። እንዲሁ ሌሎቹም ከረጅም ውይይት በኃላ የተስማሙ መስለው ድርድሩ ይከሽፋል። እልህ አስጨራሹ የግዥ እና የሽያጭ ድርድር በአንዲት የዐስራ ስምንት ዓመት የሚጠጋት ወጣትና በአንድ ዘለግ ባለ ቀይ ጎረምሳ መካከል ተሳካ። ይህን ጊዜ የቀድሞዋ ልጅ ምክር ቦታውን ስላገኘ ተደሰትን። ተከታተልናቸው። አንዲት ባለ አልጋ ቀለበቻቸው። ሁለቱን ወጣቶች ወደ ቤቷ አስገብታ በሩን በላያቸው ላይ ጠረቀመችው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኃላ በሩ ተከፍቶ ሌላ አልጋ ፈላጊን ፍለጋ ባለቤቷ ብቅ አለች። ከጓደኛዬ ጋር ተያይተን ጠጋ አልናት። «አልጋ ይኖርሻል?» ስንል ጠየቅን። ይኖራል ብላ እየመራች ሁለቱ ወጣቶች ወደ ገቡበት ክፍል ይዛን ገባች። አቅዳችን ሰመረ።

ሦስት በአራት በኾነችው ክፍል ውስጥ የጠላውና የአረቄው ሽታ ብቻውን ነግሷል። በትንሽዋ ክፍል ውስጥ ትንሽ አልጋ የተዘረጋበት ሌላ ክፍል አለች። ከበሩ ትይዩ ወደ ኮርኒስ የሚያስወጣውን መሰላል እየጠቆመችን ምድር ወይስ ቆጥ ላይ? በሚል የምርጫ ጥያቄ አቀረበችልን። ሁላታችንም ቆጡን መረጥን። ቆጡ የቤቱን ግማሽ ያህል ይሸፍናል። በመሰላል ወደ ላይ ስንወጣ ሦስት በካርቶን የተከፋፈሉ ክፍሎችን አገኘን። የቆጡ ክፍል ላይ መቆም ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። ጥሩ ወገብ ያለው አጎንብሶ መሄድ ይችላል። ይህንን ማድረግ ያልቻለ በዳዴ ልጅነቱን እንዲያስታውስ ይገደዳል። የክፍሎቹ ግድግዳም ኾነ በር የተሰራው ከካርቶን ነው። በክፍሎቹ ውስጥ አነስተኛ አልጋዎች ተዘርግተዋል። በካርቶን ግድግዳና በማዳበሪያ የተወጠረው ኮርኒስ አንድ ዜሮ ሻማ አምፖል ለሁለት ክፍል እንዲያበራ ተደርጎ ተሰቅሏል። ከሦስቱ የካርቶን ክፍሎች በመካከለኛው ለመተኛት ወደድን። ከበስተቀኝ ካለው ክፍል ከኮሽታ ጀምሮ እስከ ኮንኮም መቅደድ ድረስ ያሉት ድምጾች ይሰማሉ። ቀድመውን የገቡት ወጣቶች ጋር ጎረቤታሞች ሆነናል። ባንተያይም እንሰማማለን።

«አገርሽ የት ነው?» አላት ወንድየው !

የመጣችበትን ነገረችው። በታውን እንደሚያውቀውና እዚያ ዘመዶች እንዳሉት ይተርክላት ጀመር።

«አሁን የት ነው የምትኖሪው?» አላት በድጋሚ። በርበሬ ተራ ጀርባ 42 ቀበሌ እንደኾነ ነገረችው። ወሬያቸው ደራ። አገር፣ዘመድ፣ ጎጥ ሳይቀር ይጠያየቃሉ፡ ድንገት መንገድ ላይ ለአዳር ተስማምተው የገቡ ሳይኾን የጥንት ወዳጆች መሰሉ። በእርግጥ በኬሻ በጠረባ እፍረት እራሷ ታፍራለች። ብጣሽ መጋረጃ እልያም ቁርጥራጭ ካርቶን ለእፍረት መሸሸጊያ በቂ ናት። አልጋዎቹ ላይ በቁንጫ ያልተሸለ ህይወት የሚገፉ ሰዎች ይርገፈገፋሉ፣ በኬሻዎቹም ቁንጫዎቹ። በስተግራ ያለው ክፍል ሌሎች ወንድና ሴት ሊሰናሰሉ ጉበተውበታል። እነዚህ በደንብ እንደሚተዋወቁ ወሬያቸው ያሳብቅባቸዋል። ትንፋሻችንን አጥፍተን እየሰማናቸው ነው። ወንድየውም በቁጭት « ብሩን አልመለሰልኝም እኮ » ይላታል። « አንተ ለምን መጀመርያ ሰጠኸው?»ትለዋለች። ከእንቁላሉ አጉርሰኝ እስኪ?» ብላ ደግሞ ቆጣ ትላለች። « ለምን ራስሽ አትጎርሺም?» ይላል የሚበላው እንቁላል ንግግሩን እያወከው። እርሱ ቅቅል እንቁላል አዝዋሪ እንደኾነ ገመትን።

በፍቅር መልክ የሚደረግ ስድድብ ከዚሁ ክፍል መሰማት ቀጠለ። በስተቀኝ ያለው አልጋ የማቃሰት ድምፁ እየጨመረ መጥቷል። ቀጥሎ ኮንዶም ከሽፋኑ ሰላቀቅ ጉዞውን ግልፅ እያደረገው ነበር። ወንድየው ፀሎት ነገር አሰማ። ፀሎቱን ሲያደርስ ሳቃችንን ለማፈን ታገልን። በሀጥያት ውስጥም ፀሎት አለ።

በግራና በቀኝ በወሲብ ትኩሳት የሚጎራበቱን ጥንዶች ሹክሹክታቸው እንኳ ከጆሯችን ለመራቅ አቅም አልነበረውም። እርስ በርሳቸው መቃተታቸውን ቀጠሉ።በስተግራ ያለው ክፍል ከምግብ ወደ ፍቅር ዞሯል።

« ካልሲህን ለምን አታጥብም?» አለችው።

« ተጠጊ ወደኔ!» አላት ኮስተር ብሎ። ይኼ ቃል የፍቅር ቋንቋ ነው። ወንዱ በፍቅር ይሳደባል። ከእፍታ በኃላ ቆጧ በወሲብ ሥራ በተጠመዱ አራት ሰዎች ተርገፈገፈች። በወሲብ ላይ ያልተሰማሩ ቲጎራባች ያለፍላጎቱ በወሲብ ቅኝት ይርገፈገፋል። ከግራና ከቀኝ ስሜቶች እንደ ጅማት ከረው መኝታ ቤቱን ሙቀት በሙቀት አድርገውታል። በእነዚህ መኝታ ቤቶች ውስጥ ምንም ስለተጎራባቹ ግድ የሚሰጠው የለም። እንደፈለጉ የሚኾኑት አልጋ የተከራዩት ብቻ አይደሉም። የባለንብረትነት ስሜት ያደረባቸው የሚመስሉት ትኃንና ቁንጫዎቹም በነጻነት ላይ ታች ይላሉ።

በወሲብ የተርገበገቡት ጎረቤቶቻችን ጥቂት አቃስተው ሩጫቸውን አጠናቀቁ። ዝምታ ሰፈነ። ከዚህ በላይ በዚህ ቆጥ ውስጥ መቆየቱን ትርጉም አጣንበት። ቆጡን ወርደን በር ጋር ስንደርስ በሩ ከውጭ ተቆልፎ አገኘነው። የከፋች ያለህ የሚል ጥሪ አሰማን። ነገር ግን ሰሚ አላገኘንም። ምን ማድረግ እንዳለብን ስንማከር የሰማች በታችኛው አልጋ ከወንድ ጋር የተጋደመች ወጣት ራሷን ለእፍታ ከወንድ ክንድ አላቃ ቀና በማለት ከዚህ ሰዓት በኃላ መውጣት እንደማንችል ነገረችን።

«ለምን?»

«በሩ ከውጭ በመቆለፉ የቤቱ ባለቤት ሌላ የአልጋ ተከራይ ለማምጣት ርቃ ወደ ዋናው መንገድ በመሄዷ።» ከስንት ሰዓት ጥበቃና መንቆራጠጥ በኃላ የቤቱ ባለቤት ሌሎች ጥንዶችን ይዛ ተመለሰች። በዚህን ጊዜ ለሠላሣ ደቂቃ ከታገትንበት ክፍል መውጣት ቻልን።

እኩለ ሌሊቱ ተጋምሷል። አውቶቡስ ተራ አሁንም አልተኛችም። «አልጋ አለ አልጋ!» የሚሉት ድምፆች አሁንም አልደከሙም። መንገድ አሳብረን ቀድመን «ሪዘርቭ» ወዳስደረግነው «ኬሻ በጠረባ» ቤት ሄድን። ሴትየዋ አልረሱንም። ሰው ላለመርገጥ እየተሰፈነጠርን ከአንድ ጥግ ተወሸቅን። በዚያ ከእንቅልፍ እና ከድካም ጋር ትግል ገጠምን። ትንሽ እንደማሸለብ ሲለን ትኋን እና ቁንጫ የጀርባችንን፣ የእግሮቻችንን አቅጣጫ መንገኘት ጀመሩ። ጦርነቱን እስከ 10:30 ተፋለምነው። መጨረሻችን ግን ተሸንፎ መውጣት ኾነ። እኛን ለጥቂት ሰዓታት ያስጨነቀንን እነርሱ ሙሉ ሕይወታቸውን እንዴት ኖሩት? ስንል ራሳችንን ጠየቅን። «ኑሮ ካሉት...» የሚለው አገራዊ ቢሂል ምላሽ ሆነን። እኛ ላንመለስ ኬሻ በጠረባን ጥለን ሄድን። የኬሻ በጠረባ ህይወት ግን ይቀጥላል። ሰውና ቁንጫ፣ ቁንጫና ሰው!

*©ይህ ዘገባ ነሐሴ 24 ቀን 2001 ዓ.ም ታትሞ በነበረው አዲስ ነገር ጋዜጣ ሰሻል ፊቸር አምድ ስር ቀርቦ እንደነበረ ይታወሳል።*

# የ<<መመረቅያ ጽሑፎች>> ጥቁር ገበያ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ የጥናት እና ምርምር ውጤቶች ለዘርፈ ብዙ አገራዊ ችግሮች የመፍትሔ አቅጣጫን እንዲጠቁሙ ይጠበቃል። ይኹንና ከትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል ጋራ ተያይዞ አሁን አሁን በለብለብ የሚሰሩ የጥናት ወረቀቶች እንደ ሸቀጥ እየተቸበቸቡ ይገኛሉ። መሐመድ ሰልማን እየደራ የመጣውን የምረቃ ጽሑፎችን የጥቁር ገበያ ሰንሰለት ይተርካል።

---

ከ«አራት ኪሎ» እስከ «ስድስት ኪሎ» ያለው ሰፊ ጎዳና የ«ዕውቀት» ኪሷቸው ገዘፍ ያሉ ሰዎች በብዛት ውር ውር የሚሉበት ሰፈር ነው። የአራት ኪሎው ሳይንስ ፋኩልቲ፣ የአምስት ኪሎው ቴክኖሎጂ ፋኩልቲ፣ የስድስት ኪሎው ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ በድምሩ ከሀያ ሺህ የሚልቁ ዜጎችን በየዕለቱ በዕውቀት ያስታጥቃሉ። በነዚህ ካምፓሶች የታጨቁ ዕጩ ምሁራን የተማሩትን በጽሑፍ እንዲገልጹ በዕውቀት አባቶቻቸው ሲጠየቁ በአካባቢው ወደተበራከቱት የኮምፒውተር ቤቶች ብቅ ይላሉ።

ሁልጊዜም ስጉዳዩ በተጠንቀቅ ላይ ካሉት ኮምፒውተር ቤቶች የተማሪዎቹ «ዕውቀት» በጽሁፍ ተቀምሮ፣በገንዘብ ተመንዝሮ ይሰጣቸዋል። ኮምፒውተር ቤቶቹ ዕውቀት ማማጥ ላይቻሉትም ቢኾን መላ መምታትን ያውቁበታል። ኑሯቸውን የመመረቂያ ጽሑሮችን በመሥራት ላይ የመሠረቱ ግለሰቦችን ስልክ በማፈላለግ ያገናኛሉ። ይህን ጊዜ የ«መመረቅያ ጽሑፎች ጥቁር ገበያ» ይደራል።

## **The thesis Engineer!**

ምስጉኑ የውልና ማስረጃ መሥሪያ ቤት አምስት ኪሎ ይገኛል።ከዚህ ስፍራ ፈጻሚ፣አስፈጻሚ እና አፈጻጸሚ ይፈጣጠማሉ። ከዚህ መሥሪያ ቤት ፊት ለፊት በሚገኙ ኮምፒውተር ቤቶች ውስጥ የመሸገ አንድ ወጣት ምስጉን ኢንጂነር አለ። በይበልጥ በቴክኖሎጂ ተማሪዎች ዘንድ ይታወቃል። አንገብጋቢ ጉዳይ ያለባቸው ሁሉ እርሱ ዘንድ ሲደርሱ ጉዳያቸው ይፈጸማል። በተለይ የዕውቀት ካባቸውን ለመደረብ መመረቅያ ጽሑፍ ብቻ የቀራቸው «ዕጩ ምሁራን»ኢንጂነር አሕመድን በጥብቅ ይፈልጉታል።

የኢንጂነር አሕመድ ስም በዚህ አካበቢ የገነነ ከመኾኑ የተነሳ በአካባቢው በሚገኙ ሱቆች ጎራ ብሎ ለሚጠይቅ ሁሉ «አናውቀውም» የሚል መልስ አያገኝም። «አሁን እኮ እዚህ ነበር! ቆይ እስኪ ይጠብቁ!» ነው የሚባለው፤ የአካባቢው ሕፃናትም ተማሪ የሚመስላቸውን ሰው «ኢንጂነርን ፈልገኽ ነው?» እያሉ ያዋክባሉ።

ኢንጂነር አሕመድ የተመራቂ ተማሪዎችን የመመረቅ ዕጣ ፈንታ በደንብ አድርጎ መቀየስን ያውቅበታል። በ1988 ዓ.ም በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ዲግሪውን ከቴክኖሎጂ ፋኩልቲ ተቀብሏል። እርሱ ዲግሪው ይዞ ከወጣበት ተቋም ዛሬ ለመመረቅ ለሚታትሩ ተማሪዎች ከአነስተኛ ፕሮጀክት እስከ መመረቂያ ጽሑፍ ቀምሮ ያቀርብላቸዋል።በፊዚክስ፣ በማቲማቲክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሲቪል፣ በኤልክትሪካል እና በመካኒካል ምሕንድስና የትምህርት ዘርፎች ብቻ ተወስኖ የነበረውን ሥራውን አሁን አሁን ወደ ሶሻል ሳይንስ ዘርፎችም በማሳደግ በፍልስፍና፣ በአንትሮፖሎጂ፣ በፖለቲካ ሳይንስ እና በሶሲዮሎጂ ዘርፎችም መመረቂያ ጽሁፎችን አዘጋጅቶ ይሸጣል። «ተማሪዎች እየመጡ አግዘን ይሉኛል» ይላል በትሁት ቋንቋ ስለ ስራው ሲገልፅ። የድካሙ ዋጋ የተማሪን አቅም ያገናዘበ እንደኾነ ሲያስረዳ ደግሞ «ተማሪዎች ስለኾኑ ብዙ ብር አልጠይቃቸውም።ለአንድ ስራ እስከ 800 ብር ብቻ አስከፍላቸዋለሁ» ይላል።

ይኹንና ኢንጂነሩ ለድኅረ ምረቃ ተማሪዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ከዚህ ላቅ ያለ ነው። « ቲሲስ» ለመሥራት ቁርጥ ተመን እንደሌለው የሚናገረው ኢንጂነሩ ፡- « የፕሮጀክቱ የገጽ ብዛት፣ የርዕሱ አመቺነት፣ የማስረከቢያ ጊዜ ቅርበትና ርቀት፣ የዋቢ መጻሕፍት አቅርቦት...ወዘተ የዋጋውን ተመን ከፍ እና ዝቅ የሚያደርጉ ግብዐቶች ናቸው።» ይላል። ኾኖም ለኢንጂነር አሕመድ ከሳይንስ ዘርፎች ይልቅ የሶሻል ዘርፎች አስቸጋሪ እንደሚኾኑበት አይከደም። «የሶሻል ሳይንስ ዘርፎችን ጊዜ ወስጄ አንብቤ መሥራት ስላለብኝ ዋጋዬም ከፍ ይላል።»

የኢንጂነሩ ዋነኛ ደንበኞች የግል ኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው። ከእነርሱ በመቀጠል የርቀት ትምህርት ተማሪዎች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ናቸው። ለኢንጂነሩ የመመረቅያ ጽሑፎች ዝግጅት እገዛ የሚያደርጉት ደግሞ ከአራት ኪሎ የሳይንስ እና አምስት ኪሎ ቴክኖሎጂ ፋኩልቲዎች የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው። «እዚያ የሚያስተምሩ ብዙ ጓደኞች ስላሉኝ ለምሠራቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገኝን መፃሕፍት ያቀርቡልኛል።»

ኢንጂነር አሕመድ ከ13 ዓመታት በፊት በኤሌክትሪካል ምሕንድስና በጥሩ ውጤት እንደተመረቀ ለቅጥር ያቀናው በፈረንሳዬች ወደ ሚመራው የኤሌክትሪክ ኩባንያ ነው። «ኤሌክትሪሲቲ ዴ ፍሮንስ» በተሰኘው በዚህ ኩባንያ ባልደረባ ኾኖ የሸራተን አዲስን የውስጥ እና የውጭ «ላይቲንግ ዲዛይን» ሥራዎች በሞያው በመሳተፍ ለስድስት ዓመታት አገልግሏል። በ«ጌላትሊ ሃንኪ»ኩባንያ የ«አይ.ቲ» ዲፖርትመንት ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል ቆይታ አድርጓል። ይህን ሁሉ የሥራ ልምድ ይዞ ግን አገሩን እያገለገለ ያለው የዕውቀት አጠር ተማሪዎችን መመረቅያ ጽሑፍ ሠርቶ በመሸጥ ነው። ይህ ኹኔታ እርሱንም ቢኾን ደስተኛ ያደረገው አይመስልም። ኾኖም «በመናኛ ደሞዝ ተቀጣሪ ከመኾን አሁን ያለሁበትን ሥራ እመርጣለኹ» ይላል ኢንጂነሩ።

ኢንጂነር አሕመድ እንደሚለው ከሆነ የአሁኖቹ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብቃታቸው እምብዛም ነው። ስለኾነም ፈተናዎችን መቋቋም አይችሉም። «አንዳንድ ጊዜ የቤት ሥራቸውን ስሠራላቸው ፈተናም ገብተኽ ብትፈተንልን» ይሉኛል የሚለው ኢንጂነር ያን ግን ፈጽሞ እንደማያደርገው አስረግጦ ይናገራል።

ኢንጂነር አሕመድ ፕሮጀክቶችን እና የመመረቅያ ጽሑፎችን መሥራት ላቃታቸው ተማሪዎች ሠርቶ በመሸጥ ሥራ ላይ ብቻ አልተወሰነም። ከዚህ በተጨማሪ በተግባራዊ የሥራ ሕይወታቸው ሞያቸውን በሚገባ መጠቀም « ያቃታቸው»ምሩቅ ኤሌክትሪካል ኢንጂነሮችን የማገዝ ሥራም ይሠራል። «ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከምሕንድስና ዘርፍ ተመርቀው በመስክ ሥራ ላይ ያሉ ሰዎች አቅም ያንሳቸዋል። ጨርሶ መሥራት ሲያቅታቸው መስክ ድረስ ይዘውኝ ሄደው የሻይ ይሰጡኛል!አግዛቸዋለኹ።» ይላል።

## በባልት የተሞሉ መመረቅያ ጽሑፎች

ለ27 ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር የቆዩት ዶ/ር አማረ አስገዶም ከአንድ ዓመት በፊት «Student's Research Practices in AAU: Reflections on MA Thesis Writing and Defense» በሚል ርዕስ ባቀረቡት የጥናት ጽሑፍ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ በሚሠሩ መመረቅያ ጽሑፎች ላይ ያስተዋሏቸውን ግድፈቶች ጠቁመዋል።

የዶክተሩ ጥናት እንደሚያትተው የሁለተኛ ዲግሪ መመረቅያ ጽሑፎች አንዳንድ ጊዜ በግዥ የተገኙ እና የተማሪዎቹ የጥረት ውጤት ያልኾኑ ናቸው። ተማሪዎቹ ለዚህ የመመረቅያ ጽሑፍ ከዩኒቨርሲቲው የሚሰጣቸውን ከሁለት እስከ ሰባት ሺህ ብር የሚደርስ ገንዘብ የመመረቅያ ጽሁፍ ለሚያዘጋጁ ሰዎች (thesis consultants) ያስረክባሉ። በሌላ ሰው በገንዘብ ያሠሩትን የጥናት ወረቀት ሸምድደው በመምጣትም ለተቋቁሞ /ዲፌንስ/ ይቀርባሉ። ዶክተር አማረ ለዚህ አስረጅ አድርገው የሚያቀርቡት፣ በጥናት ጽሑፎቻቸው ተቋቁሞ (Defense Session) ወቅት ተማሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በኮምፒዩተር «ፖወር ፖይንት» ላይ መመርኮዛቸው ነው። «መብራት ከሄደ ተመራቂዎቹ ድንጋጤ ውስጥ ይገባሉ።ለአንድ ዓመት ጥናት ስለሠሩበት ጉዳይ ከአንደበታቸው እንዴት አንድ ቃል እንኳ ማውጣት ምጥ ይኾንባቸዋል?» ይላሉ ዶክተሩ በግርምት ሣቅ እየታጀቡ።

በዚህ የዶክተር አማረ ጥናት እንደተብራራው ለጽሑፍ የሚኾኑ ጥሬ መረጃዎች (data) የሚሰበሰቡት ቦታው ድረስ በትክክል በመሄድ ሳይኾን እንዲሁ በፈጠራ ነው። ይህንንም ዶክተሩ በ «Cooking Data» የተፈበረከ መረጃ ሲሉ ይጠሩታል። የርዕስ አመራረጥ ላይም ቢኾን ተማሪዎች አዲስ ጉዳይ ከመምረጥ ይልቅ ከዚህ ቀደም በተሠሩና ለመኮረጅ በሚመቹ ጉዳዮች ላይ ማጠንጠን ይመርጣሉ። «ይህም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልኾነ መንገድ ለመኮረጅ ስለሚመቻቸው ነው።»

ተመራቂ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባልተዳሰሱ ርዕስ ጉዳዮች ላይ እንዲሠሩ ሲጠየቁ፣ «ቲቸር፤ ከዚህ በፊት እኮ አልተሰራበትም ይሉኛል» የሚሉት ዶክተር አማረ፣አዲስ ዕውቀትን ከመፈተሽ ይልቅ ‹፣«ከዚህና ከዚያ በተለቃቀሙ የጥቅስ ስብስቦች የተደረቱ እና ግልብ የኾኑ» ወረቀቶች ይቀርባሉ ይላሉ። እንዲህ ዐይነት በባልት የተሞሉ ጽሑፎችን በተደጋጋሚ የታዘቡት ዶክተሩ ዘለግ ላለ ሰዓት ከተከዙ በኃላ «መመረቅያ ጽሑፍ መሥራት ቢቀርስ!» እስከማለት ይደርሳሉ።

## የመመረቅያ ጽሑፍ ኪዮስኮች

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ «ስድስት ኪሎ» ካምፓስ ዋና በር ግርማ ሞገሱን የሚፈታተኑ ቅጥ ያጡ ማስታወቅያዎች ተለጣጥፈውበታል። ከነዚህም አንዱ እንዲህ ይላል። « ሚራክል የቁቶር አገልግሎት፣ አሳይመንት እንሠራለን፣ የመመረቅያ ፕሮጀክቶችን /ጽሑፎችን በተቀላጠፈ ኹኔታ የማማከር አገልግሎት እንሰጣለን...!»

የአዲስ ነገር ዘጋቢ ሜክሲኮ አደባባይ ወደሚገኘው የዚህ ድርጅት መሥሪያ ቤት በመሄድ በአንትሮፖሎጂ ዘርፍ የሁለተኛ ዲግሪ ወረቀት እንዲሠራለት ጠይቆ የመጨረሻ ዋጋው 2500 ብር እንደ ኾነ ተነግሮታል። ከምክረ ሐሳብ (proposal) ጀምሮ እስከ ማጸደቅ እና ተቋቁሞ (defense) ድረስ ሙሉ ሥራው የሚዘጋጀውም በዘርፉ በተመረቀ ሰው እንደሚኾን ተገልፆለታል።

ድርጅቱ ለርቀት ትምህርት ተማሪዎች ጥያቄዎችን በጥራትና በፍጥነት ሰርቶ ያስረክባል። የመጀመርያ ዲግሪ መመረቅያ ጽሑፍ (Senior Essay) በብር 1600፣ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቅያ ጽሑፍ (Thesis) ከ2500 ብር ጀምሮ፣ አነስተኛ ፕሮጀክቶችን ከአንድ ሺህ ብር ባነሰ ዋጋ አዘጋጅቶ ያስረክባል። አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ጽሑፎቹን በመሥራት ወጣት የከፍለ ሀገር የዩኒቨርሲቲ መምህራን ተሳትፎ ያደርጋሉ። ደንበኛው በመመረቅያ ጽሑፍ ይዘት እና ዋጋ ከተስማማ ዳሽን ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ በሚገኘው የድርጅቱ አካውንት ቁጥር ብሩን ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል። በቅድሚያ መከፈል የሚጠበቅበት ግን ግማሽ ያህሉን ብቻ ነው። ይህ የተማሪዎችን መመረቅ ጽሑፎች በመሥራት ዝናን ያተረፈው ድርጅት ወደፊት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹን አዳዲስ ዩኒቨርሲቲ በተከፈቱባቸው የክልል ከተሞች እንደማይከፍት ምን ማስተማመኛ ይኖር ይኾን?

## የጥቁር ገበያው እንድምታ

ዶ/ር አማረ አስገዶም በአሁኑ ጊዜ እየተሠሩ ያሉ የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች ጥናታዊ ጽሑፎች ቱባ (original) ያለመኾን እና በይዘታቸውም ግልብ/ shallow/ የመኾናቸው ሚስጥር የጠቅላላ አገራዊ ትምህርት ጥራት ዝቅጠት አንድ ማሳያ እንደኾነ በጥናታቸው ላይ ይጠቅሳሉ። የዶክተሩ

የጥናት ማጠቃለያ የሚመክረው « የጥናት ወረቀቶች በኩረጃ የሚሠሩ፣አዲስነት የሌላቸው፣ በውሸት መረጃዎች የተቁላሉ (cooked data) መኾናቸውን እያወቅን ስለምን የአገር ሀብት እናባክናለን?» በማለት ስር ነቀል ጥያቄ ያነሳሉ። በጥናታቸው እንደ መፍትሄ የሚያስቀምጡትም የጥናት ጽሑፎችን ሙሉ በሙሉ ማስቀረትና ለቁጥጥር በሚያመቹ ደረቅ ኮርሶች መተካትን ነው። «ሊሆያም ደግሞ አቅም፣ፈቃደኛነትና እና ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎችን ብቻ የጥናት ወረቀት እንዲሠሩ ማገዝ» እንደ አማራጭ ያቀርቡታል። አለበለዚያ «ወረርሽኙ ወደ ፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎች ሊዛመት የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም» የዶክተሩ ስጋት ነው።

አዲስ ነገር በጉዳዩ ላይ ያነጋገራቸው ጥቂት የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች እንደሚናገሩት አማካሪ ተብለው የሚመደቡ የዩኒቨርሲት መምህራን ጭምር አሁን ባለው የትምህርት ጥራት ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሳ የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፎች ጥራት ግድ አይሰጣቸውም፤ የሚሠሩ ወረቀቶችም የተማሪዎቹ የሥራ ውጤቶች እንዳልኾኑ እሳምረው ያውቃሉ። በትምህርት ፋኩልቲ አንድ ዲፓርትመንት ሥር ከዓመት በፊት ተመራቂ የነበረ ወጣት ለአዲስ ነገር ዘጋቢ እንደተናገረው የጥናት አማካሪው የነበሩ መምህሩ ደጋግመው፣« እንደ ጊዜው ከዚህም ከዚያም ብለኽ ጨርስ እንጂ፣ ብዙም አትጨነቅበት» ይሉት እንደነበር ምስክርነቱን ገልጧል።

## የማን የጥናት ወረቀት?

ኢንጂነር አሕመድ እስከ ዛሬ የሸጣቸውን የመመረቅያ ጽሑፎች ብዛት ለመናገር ያዳግተዋል። ኾኖም እርሱ ሠርቶላቸው የተመረቁ ተማሪዎች ከምረቃ በኃላ በጣም ተደስተው ለምስጋና እርሱ ዘንድ እንደሚመጡና እንደሚጋብዙት አይሸሽግም፤«አንዳንዶቹ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጉርሻ ሞቅ ያለ ብር ሸልመውኝ ይሄዳሉ» ይላል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኬኔዲ መታሰቢያ፣ በአራት ኪሎ ሳይንስ ፋኩልቲ እና ቴክኖሎጂ ካምፓስ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በመልክ በመልክ ተደርድረው ከምናያቸው ወረቀቶች ስንቶቹ የኢንጂነር አሕመድ ድርሰቶች፣ ስንቶቹ ደግሞ የ«ሚራክል ቱቶሪያል ሰርቪስ» ሸቀጦች እንደ ኾኑ ከእነርሱ ሌላ ማን ሊናገር ይችላል?

*© ይህ ፅሁፍ ግንቦት 22፤2001 ታትሞ በነበረው አዲስ ነገር ጋዜጣ የትምህርት አምድ ስር ቀርቦ እንደነበር ይታወሳል።*

# ሼ - መንደፈር በመርካቶ

ይህቺ አገር ፈሪሃ -እግዚአብሔር (ተቅዋ) በብዙ የሰፈነባት የምድራችን ክፍል ናት እላለሁ። ሕዝቦቿም ለፈጣሪ ተንበርካኪ እና ጨዋዎች ናቸው ብዬ አስባለሁ። ይህን መግቢያዬን የሚጠራጠር ሰው ካለ በፒያሳ ወይም በመርካቶ እንደ ገብስ ተሰጥቶ  የሚቸረቸረውን የወርቅ ብዛት ጎራ ብሎ ይመልከት። ነፍሷን ይማርና ዛሬ በሕይወት በሌለችው “አዲስ ነገር ጋዜጣ” ላይ “ኢትዮጵያዊ ድኻ ለምን አይሰርቅም” የሚል ውብ መጣጥፍ ማንበቤ ትዝ ይለኛል። ያ ጽሑፍ  ለኢትዮጵያዊያን ጨዋነት የፈሪሀ-እግዚአብሔርን መላምት እንደ አንድ አመክንዬ ይቀበለዋል።

ንቅሳት እንኳ የመሰረቅ ብቃት አላቸው የሚባሉት የመርካቶ ቀማኞች “ኪስ ሲያወልቁ” ያገኙትን መታወቅያ እና ጠቃሚ ሰነድ ለባለቤቱ የመመለስ ጥሩ ባህል እንዳላቸው ነዋሪዎች ይመሰክራሉ፤ ስርቆታቸው ቢከፋም ቢሰፋም ሰው እስከመግደል አይሄድም። በጎረቤት ኬንያ እንደሚስተዋለው ለአንድ ሞባይል አንድ ነፍስ የመቅጠፍ አንጀት የላቸውም። የእንጀራ ጉዳይ ኾኖባቸው እንጂ ባይሰርቁ ደስ የሚላቸው ይመስለኛል። የአገሬ ሌቦች ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደረባቸው ለመኾናቸው “ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ” የለኝም የምለውም ለዚሁ ነው። ኢትዮጵያ በሁለቱም ታላላቅ ሃይማኖቶች ቅዱሳን መጻሕፍት ላይ ተጠቅሳለች፤ ለያውም በተደጋጋሚ። አሜሪካም ኾነች እንግሊዝ ይህን  ዕድል አላገኙትም። አሜሪካ ለከፋቸው መጠለያ መኾን የጀመረችው ገና በቅርቡ ነው። አገሬ ኢትዮጵያ ግን ያኔ ጥንት በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የነቢዩ

ተዋደው ኖረዋል፡፡(ተቻችለው የሚለው ቃል ምንኛ ይጎረብጣል!) እያወራሁ ያለሁት የእኔን ዘመን እንጂ የአያቶቼን ዘመን እንዳልሆነ ግን ልብ በሉልኝ፡፡ የአያቶቼ ዘመን ለሙስሊሞች መልካም ጊዜ አልነበረም፡፡ ያ ስሜት ግን ዛሬን ማበላሸት ያለበት አይመስለኝም፡፡ በእኔ እድሜ የነበረው የሁለቱ ሀይማኖቶች ወንድማዊነት ታሪክ የድሮ ታሪክ እንያደፈርሰው መፈቀድም የለበትም ባይ ነኝ፡፡

ሙስሊምና ክርስቲያን በአገሬ ተዋደው ለመኖራቸው ደግሞ የእኔ የልጅነት ትውስታ በራሱ በምስክርነት መቅረብ የሚችል ነው፡፡ ከእኒያ የልጅነት ወዳጆቼ መሀል አሁን ብዙዎቻችን ከሃይማኖት መንሸራተት ጀምረናል፡፡

እንዳንዶቻችን በተቃራኒው አምርረናል፡፡ አሁን "ሆያ-ሆዬ" ፍፁም ክርስቲያናዊ ተግባር እንደኾነ ሲሰበክ እሰማለኹ፡፡ ከሃይማኖቴ ውጭ ሌላ ወዳጅ እንዳላፈራ እንተጎታለኹ፡፡ በየኢጋጣሚው የማነባቸው አዳዲስ መንፈሳዊ መጻሕፍትም ስለ ፍቅር የሚሰብኩበት ቃላት ጎድለውባቸዋል፡፡ ይልቁንም መጪው ዘመን በሃይማኖቴ ላይ አደጋ የሚያንዣብብበት እንደሚኾን የሚተነብዩ እና ነቅቼ እንድጠብቅም የሚያስጠነቅቁ ናቸው፡፡

በተቃራኒው ጎራ የሚጻፉ መጻሕፍትም በተመሳሳይ መልኩ ተናዳፊ ናቸው፡፡ ሃይማኖትን የሚያክል የማይጨበጥ ነገር ቤተ-ሙከራ አስገብተን መረመርነው፣ ዘረዘርነው፣ ደረስንበት፣ «የእኛ ነው ልክ»የሚሉ ቀሳውስት ውዝግብ የሚያስነሱ ነጥቦችን መርጠው በማንሳት ሰሞኑን ከሰማይ የተላኩ፣ ልዩ፣ የተቀቡና የበቁ ሰባኪ ለመሆን ይታትራሉ፡፡ ከቤተ-ሙከራው ሲወጡም ብዙ አማኝን የሚያስቀይም ውጤት ይዘው እኛን ብቻ ስሙ ሲሉ ይንጎራደዳሉ፡፡ ያንኑ በመጽሐፍ ፣ በሲዲ፣ በቲ-ሸርት ካልታተመልን ይላሉ፡፡የኔዋ የአሁኗ መርካቶ በዚህ ሁሉ ተቃርኖ የተሞላች ናት፡፡ በዚህ አመት በጋራ የተጀመሩት የፍልሰታ እና የረመዳን ፆሞች ደግሞ ተቃርኖውን አጉልተው እያሳዩኝ ነው፡፡ በመርካቶው ሼ- መንደፈር፡፡

## ረመዳን እና ፍልሰታ - የሁለት ሳንቲም አንድ ገፅታ

መርካቶ ዜጎች ለአውዳመት አስቤዛ ሲገዙ፣ አማኞቿ በበኩላቸው በፆም ምክንያት ልብ ሲገዙ ግርግሩ ትንፋሽ ያሳጣታል፡፡ በተለይ በፆም ወቅት መርካቶ በተሽከርካሪዎች ላይ ተንቀሳቃሽ

ቤተ-ክርስቲያኖችን እና መስጊዶችን ማስማራቷ የተለመደ ነው፡፡ በድምፅ ማጉያ ሰባኪዎች አቅሏን ትስታለች፡፡ መንዙማ እና መዝሙር፣ ዱአዋ እና ስብከት ልክ ባጣ የ«ሞንታርቦ» ላንቃ አፍ አውጥተው "ካሴት ግዙንና ትድናላችሁ" ተማጽኖ ያቀርባሉ፡፡ ገነት እና ጀነት የሚገባውን ምዕመን ቁጥር ለማሳደግ በየፊናቸው የ«ሞንታርቦ» ድምፅ ይጨምራሉ፡፡ በድምፅ ጉልበት መንግስተ-ሠማያት ይወረስ ይመስል፡፡

የ16 ቀናት ዕድሜ ያለው የፍልሰታ ፆም ከሁዳዴ ቀጥሎ ምዕመናኑን ወደ ቤተክርስቲያን ደጃፎች የሚጠራ ነው፡፡ ነጠላ ያጣፉ ሴት ምዕመንት በእያሌው ወደ ደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ይጎርፋሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ15ኛ ቀኑን ያስቆጠረው የረመዳን ፆም ቁጥራቸው ከፍ ያለ ሙስሊም ምዕመናንም ወደ ታላቁ አንዋር መስጊድ በገፍ ይጠራል፡፡ በዚህ ወቅት የቀሳውስቱ ቆብ እና የሙስሊም ኮፍያ፣ የምዕመኑ ነጠላ እና የሙስሊም ጀለቢያወአባያ ተጣምረው ወደ ጎረቤታሞቹ አንዋር እና ራጉኤል ይገባሉ፡፡ መለየት እስኪያስቸግር ይቀላቀላሉ፡፡ አብረው ይተማሉ፡፡ ትዕይንቱ በተለይም ዘወትር አርብ የተለየ ግርምትን ይፈጥራል፡፡

በአንዋር መስጊድ እና በቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን አጥሮች መካከል ያለው ርቀት አንድ መኪናን ብቻ ማሳለፍ የሚያስችል ነው፡፡ በእነዚህ የአምልኮ ስፍራዎች የሚገኘው ሕዝብ ደግሞ አጥሮቹን አልፎ የሚፈስ ነው፡፡ በመኾኑም ምዕመናኑ በዐቢይ የጸሎት ወቅቶች በዙርያቸው የሚገኙትን የተሽከርካሪ ጎዳናዎችን ለመጠቀም ይገደዳሉ፡፡

በተለይም አንዋር መስጊድ በረመዳን የጁምዐ ስግደት የምዕመናኑ ቁጥር በአራት እና አምስት እጥፍ ስለሚጨምር የመርካቶን ሲሶ በጸሎት ስፍራነት ለመጠቀም ይገደዳል፡፡ በደቡብ በኩል እስከ "ሲኒማ ራስ"፣ በምዕራብ እስከ "ጣና ገበያ" አንዳንዴም እስከ "ምዕራብ ሆቴል"፣ በሰሜን እስከ "ጎጃም በረንዳ" እንዲሁም በምሥራቅ እስከ አሜሪካን ግቢ ድረስ ይዘልቃል፡፡ ይህ ኹኔታ ከሚፈጥራቸው አስገራሚ ትዕይንቶች አንዱ ሲጋጆቹ የራጉኤልን ቤተክርስቲያን ዙርያ አጥር ለመጠቀም መገደዳቸው ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ነጠላ እና አባያ፣ ጥምጣም እና ጀለቢያ ባይፈቅዱትም ትከሻ ለትከሻ፣ መላ ለመላ ለመቆም ይገደዳሉ፡፡

ዘወትር ምሽት በረመዳን ወር የሚሰገደው የ‹‹ተራዊህ›› ስግደት ዘለግ ያለ ሰዓትን ይወስዳል፡፡ አማኞች መኪናዎቻቸውን በሁለቱም የእምነት ስፍራዎች ዙርያ እየኮለኮሉ ያቆሟቸዋል፡፡በአንዋርና በራጉኤል ዙርያ፡፡

ኩታ ገጠሞቹ የእምነት ሰፍራዎች የመኪና እስላምና ክርስቲያን መለየት ስለማይችሉ ሁኔታውን ሊቃወሙ አይቻላቸውም። ሁኔታውን ይበልጥ አስገራሚና ምናልባትም በአለም ብቸኛው የሚያደርገው ሙስሊም ምእመናን የተራዊህ ሶላት ሲሰግዱም የራጉዔልን አጥር ተደግፈው መሆኑ ነው። መስገጃዎቻቸው የሚዘረጉበት ከልል የራጉዔልን ሕንፃ በረንዳዎች ጭምር አካሎ ይይዛል። ዘወትር ምሽት ይህንን አስገራሚ ክስተት ባስተዋልኹ ቁጥር በካሜራ ቀርጾ ለማስቀረት ይዳዳኛል፤ ተሳክቶልኝ ባያውቅም። ይህ ሁኔታ እኔን እንደሚደንቀኝ ያህል የሚደንቀው ሰው ብዙም አያጋጥመኝም። ይህ አስገራሚ ክስተት ከሆኑ አመታት በኃላ ይቀጥላል ብዬ አልገምትም። ስለዚህ ሰዎች ወደ ስፍራው እየመጡ መገረም አለባቸው የሚል ጠንካራ አቋም ሳላዳብር አልቀረሁም።

የጁምዐ ስግደት ላይ ሃይማኖታዊ ዲስኩር (ኹጥባ) በአሲጋጁ (ኢማሙ) አማካኝነት ይቀርባል። አንዳንድ ጊዜ/ ወይም ብዙውን ጊዜ/ በተመሳሳይ ከራጉዔል የቅዳሴ ዜማ ይለቀቃል። አስር ሜትር የማይሞላ ርቀት ካላቸው ከእነዚህ ኩታ ገጠም የእምነት ስፍራዎች በድምፅ ማጉያ የሚስተጋቡት ድምፆች እርስ በርስ ስለሚራበሹ ምእመናኑ ሁለቱንም ከማዳመጥ ውጭ ምርጫ ያጣሉ። አንዱን ነጥሎ ማዳመጥ ምርጫ ስላልሆነ። ብቻ ከሁለቱም ጎራ ያሉ አማኞች ይህ ኹኔታ የሚፈጥርባቸውን እውነተኛ ስሜት ባላውቅም ለእኔ ግን ትርጉሙ የትየለሌ ይኾንብኛል። በዐረብኛ እና በግዕዝ ወደ አምላክ የሚተላለፉ ተማጽኖዎች?

የቅዱስ ራጉዔል ቤተክርስቲያን እንደ ብዙዎቹ አቻዎቹ አጥሩን አስታኮ ያስገነባው ግዙፍ ሕንፃ ፎቅ ለደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉዔል ትምህርት ቤትነት ሲያገለግል ምድሩ ላይ ያሉት ቤቶች ደግሞ በአመዛኙ የንግድ ቤት ኾነው ያገለግላሉ።

በእነዚህ ሱቆች የሞባይል መለዋወጫ፣ በስተ ምዕራብ ባሉት ሱቆች ሻንጣ እና ብርድ ልብስ፣ ኦርቶዶክስ ዘ-ተዋህዶ መዝሙር ቤቶች እና በስተ ምሥራቅ ባሉት ሱቆቹ ደግሞ ኢስላማዊ ቁሳቁሶች የሚሸጡባቸው ናቸው። ልብ በሉ፣ በራጉኤል ሱቆች ኢስላማዊ ቁሳቁሶች ነው ያልኩት። በዚሁ የራጉኤል ሕንፃ ላይ የሚገኘው ዘመናዊው "ሄኒ-ፔኒ ካፌ" ለረመዳን ኢስላማዊ ምግብ እና መጠጦችን ያቀርባል። ባለቤቱ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ነው ሲባል ሰምቻለሁ፤ ኾኖም ማረጋገጥ አልቻልኩም። እውነት ከኾነ ግን የሶስት እምነቶች «ሀትሪክ» ተሰራ ማለት ነው። በቅዱሰ ራጉኤል ሀንፃ በሚገኝ የፕሮቴስታንት ምግብ ቤት

ሙስሊሞች ፆማቸውን ሲገድፉ -ሶስታ!

ይህ የቅዱስ ራጉዔል ሕንፃ የአርክቴክት ዲዛይኑ የመስቀል ቅርጽ እንዲኖረው ተደርጎ የተሠራ ነው። ኾኖም በሥሩ ከሚገኙት ሱቆች ውስጥ አባያ ( ሙስሊም ሴቶች የሚለብሱት ጥቁር ቀሚስ)፣ ኒቃብ (ፊትን በከፊል የሚሸፍን) ሻሽ፣ ሂጃብ (ጸጉርን የሚሸፍን) ፣ ቡርቃ (ከዐይን በስተቀር መላ ሰውነትን የሚሸፍን) እንዲሁም ጀለቢያ እና መስገጃዎች ይሸጡበታል። ይህ ኹነት ለአንዳንዶች ከቢዝነስ ፍልስፍና ከፍ ያላለ ትርጉም ላይሰጣቸው ይችላል። ለእኔ ግን ትርጉሙ የትየሌለ ነው።

ድህነታችን እና ባህላችን ተጋግዘው የፈጠሩት ጥብቅ ጉርብትና ማኅበራዊ ሕይወታችንን ይጫኑታል። ይህ ኹኔታ በሃይማኖት መሥመሮችም የሚገለጥበት ጊዜ አለ። ሙስሊም እናቶቻችን «ሐኒ መምሬ ቤት ጠበል ቅመሱ» ሲባል ከመሄድ አይቦዝንም። ሰርጎቻችን ከሁለቱም ሀይማኖቶች የተወከሉ በጎችና በሬዎች ካልተሰዉበት ሙሉእ ሆኖ አይቆጠርም። እድሮቻችን ሀይማኖቶቹ ያበጁትን መስመር ገሸሽ የሚያደርጉ ናቸው።

ከክርስቲያን አብሮ አደጎቼ ጋራ የነበረን ወዳጅነት አንድ ጊዜም ቢኾን በሃይማኖት ስሜት የተቀኘበት ወቅት ትዝ አይለኝም። አንዳንድ ጓደኞቼ አሁንም ድረስ የኢስላም አቡጊዳ የኾኑትን የዐረብኛ ፊደላትን እና ጥቂት የቁርዐን አንቀጾችን በቃላቸው ማነብነብ እንደሚችሉ አስተውያለኹ፤ እንደ እኔ ከሙስሊም ቤተሰብ ለወጡ ብዙ ዜጎች «ቄስ ትምህርት ቤት» ሙዋዕለ-ሕፃናት እንጂ የክርስትያን ተቋም ኾኖ ተሰምቶን አያውቅም ነበር።

ይህ ስሜት በአዲሱ ትውልድ እየተሸረሸረ ይመስለኛል። የአሁን ሙስሊም ወዳጆቼ አገራዊ ከኾኑ ጉዳዮች በፊት ለአረብ ሕዝቦች አለኝታነት ይሰማቸዋል። ይህን እንደ ስኅተት ባላየውም ከስሜታቸው ጀርባ ያለው ምስል ግን ያስፈራኛል። ቤታቸው ውስጥ አሁን አሁን የማያቸው መጻሕፍትም ኾኑ ሲዲዎች የጽዮናዊት እሥራዔልን ሤራ እንዴት መበጣጠስ እንደሚቻል የሚያትቱ፤ አልያም ደግሞ ሌሎች ሃይማኖቶች እንዴት ኢስላምን ለማጥፋት ቀን ተሌት እየሠሩ እንደኾኑ ለማሳመን የሚጥሩ ናቸው። በየሳምንቱ አርብ የሚወጡ መንፈሳዊ ጋዜጦችም ቢንላደን በኔቶ ሠራዊት ላይ ያደረሰውን ጥፋት ተጋኖ የሚዘገብበት ሚዲያ ነው።

ለምሳሌ አንዋር መስጊድን እና ራጉዔል ቤተ-ክርስቲያንን በሚለዩት አጥሮች መሀል ባለው

ጎዳና እነዚህ አስፈሪ ጭብጥ ያላቸው የኅትመት ውጤቶች እንደ ቆሎ ይቸረቸራሉ፤ ከሁለቱም ጎራ። ይህንን ጽሑፍ ለማሰናዳት በሰፍራው ባንዣበብኩባቸው ቅጽበቶች ብቻ ያየኋቸውን የኅትመት ውጤቶች ብዘረዝር ፍርኀቴ ይብልጥ ግልጽ የሚኾን ይመስለኛል።

“የኢየሱስ ማንነት ተደረሰበት…

“ሚዛኑ ቢጠፋ ወርቁ ጠፋ፣ ሴቶችን የበደለ ክርስቲያን ወይስ ኢስላም”

“ኢየሱስ ነቢይ ወይስ ፈጣሪ”

“ቁርዐንን ማን ደረሰው”

“የኢየሱስ ማንነት ለእስላሞች መልስ”

የመርካቶ የአንዋር መስጊድ እና የደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ፍጥጫ፣ ፍቅር እና ተቃርኖ የመላ አገሪቱን ስሜት አይወክልም ለማለት ያዳግታል። እየቀጨጨ ያለ አብሮነት፣ እየጎመራ የሚመስል የሌላውን የማንኳሰስ አባዜ፣ የእኔን ብቻ ስሙኝ የሚለው ውትወታ፣ ጠበብ ያለ ሃይማኖታዊ አቋም ወዘተ …።

በቅርቡ የ“ሚሊቴሪ ተራ” ነጋዴዎች እከሊዮን ማኅበር አባላቱን በራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ ስብሰባ ይጠራቸዋል። በሚያስገነቡት ሕንፃ ጉዳይ ላይ እንዲመክሩ። አንዳንድ የማኅበሩ አባላት ታድያ ሙስሊሞች በመኾናቸው የሙስሊም ቆባቸውን አድርገው ወደ ስብሰባው ይገባሉ። ሰብሳቢዎቹም ያሉት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር በመኾኑ ቆባቸውን እንዲያወልቁ ይጠይቃሉ። ሙስሊም አባላትም “ይህን ካወቃችኹ ለምን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰበሰባችሁን?” በሚል ስብሰባውን ረግጠው ይወጣሉ። አንዳንዶችም ለፀብ ይጋበዛሉ። እንዴት መታገስ ተሳናቸው?

ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ሃይማኖታዊ ፉክክሩ እና ትንኮሳው የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት ጭምር የጠየቀ ነበር። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደኅንነት አማካሪ አቶ አባይ ፀሐዬ ትኩሳቶችን ለማርገብ ላይ ታች ሲባዝኑ አይተናል። ጥምቀት ከሀይማኖታዊነቱ ይልቅ የጡንቻ ማሳያነቱ ጎልቶ እየወጣ ነው። የህዝብ በሆኑ ድልድዮችና ስልክ እንጨቶች ላይ « እመን እንጂ አትፍራ፣ አንድ ሀይማኖት አንድ ጥምቀት...» ፣« ኢትዮጵያ የዚህ እምነት ደሴት ናት» የሚሉ ባነሮች መሰቀያ ይሆናሉ።

በነዚህ ወቅቶች አስፋልቶች፣ ድልድዮች ግድግዳዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ ይገደዳሉ። የኢድ ክብረ በዓላትን ለማክበር አደባባዮች በቂ ሆነው ሳለ ሁሉም ጎዳናዎች ሰልመው ካልታዩ በዓሉ የሚጓደል ይመስል ለጠብ ለመጋበዝ እጀታን መሰብሰብ ይስተዋላል። የሁለቱም እምነት ተከታዮች በሃይማኖታዊ ክብረ-በዐሎቻቸው ላይ ተከታዮቻቸውን ሆ- ብለው አደባባይ እንዲወጡ በማባበል እግረ መንገዳቸውን ጡንቻቸውን ለማሳየት ይጠቀሙበታል። አንዳንዴ ከሃይማኖታቸው መሠረታዊ አስተምህሮዎች ጭምር በሚጣረስ መልኩ አሰጸያፊ ቃላት ጨዋ በሚመስል መንገድ ተለዋውጠው ለአደባባይ እንዲበቁ ይደረጋል።

የክሩሴድ ጦርነት ከተት የታወጀ እስኪመስል ሁለቱም እምነቶች ዛቻን ያዘሉ ጽሑፎችን በአልባሳት እያተሙ ለአደባባይ አብቅተዋል። ይህች ደሴት እኔ ከምከተለው ሃይማኖት ሌላ ለማስተናገድ ቦታ የላትም ሲሉም ያወጁ ነበሩ። ይህን መሰሉን ነገር ስመለከት አብሮነታችን በቋፍ ያለ መስሎ ይሰማኛል፤ ‹‹ በድሮ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ እስላምና ክርስቲያን በአንድ ላይ ተዋደው ይኖሩ ነበር» ሊባል የሚችልበት ጊዜ ቅርብ ሆኖ ይሰማኛል። እንዲህም አሰባለኹ። የ‹‹ሼ-መንደፈር›› ታሪካችን ዘፈን ብቻ ኾኖ ሊቀር ይችላል፤ አላህ እና እግዚአብሔር ካልታደጉት በቀር።

*©ይህ ፅሁፍ ኢ.ኢ.ኢ በነሐሴ 2010 የአዲስ ነገር ድረ ገፅ ላይ*
*በእንግሊዝኛና በአማርኛ ታትሞ እንደነበረ ይታወሳል፡፡*

# ጆዝቢ.tude

በተማሪነት ዘመኑ የተጨበጨበለት ጆዝባ እንደነበር ያምናል፤ የቀድሞው የዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የጂኦግራፊ ተማሪ ፀብዮት ሙላቱ። ኾኖም ፀብዮት «ጆዝባ» የሚለውን ጥሬ ቃል ለመበየን ይቸገራል። ቃሉ ዘመን ተሻጋሪ እንደኾነና ነገር ግን በዘመናት ውስጥ ትርጓሜው እየተለወጠ እንደመጣ ይገምታል። ፀብዮት ለዚህ እንደማሳያ የሚጠቅሰው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአንድ መድረክ ሲጋራ ማጨስ እንዴት እንደጀመሩ የገለፁበትን ኹኔታ በማስታወስ ነው። « እኔ ሲጋራ የጀመርኩት ጆዝባ እንዳልባል ነበር...» ሲሉ ለወጣቶች ተናግረው ነበር በአንድ ወቅት። ይህ የሚያሳየው ቃሉ በእነ መለስ የተማሪነት ዘመን የነበረው ትርጓም « ፋራ»፣ «ነገር ያልገባው»፣«ያልነቃ » ወዘተ ማለት እንደነበርና በተቃራኒው አሁን ቃሉ በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ ያለው ትርጉም ግን « ነገር ዓለሙ የተገለጠለት፣ ኾኖም ግን ሁሉን የተወ፣ ደንታ ቢስ» የሚል ኾኖ እናገኘዋለን። የዘመኑ ጆዝባ ነኝ ብሎ ያወጀው ፀብዮት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአጭሩ የዩኒቨርሲቲ ዘመን ቆይታቸው «ጆዝባ» እንደነበሩ ይገምታል። «አርሳቸው ሩቅ ለሚመስሉ ጉዳዮች የሚሰጡት ጥልቅ ትንታኔ፣ንግግር አዋቂነታቸው፣ የተራውን ሰው ቋንቋ

መናገራቸው፣ በጀዝባነት ሕይወት ማለፋቸውን እንድንጠረጥር ያደርገኛል» ይላል ለድፍረቱ ይቅርታ እየጠየቀ። ይህ ትንታኔው በራሱ ግን ዐብዮት የተዋጣለት ጀዝባ መኾኑን የሚያሳይ ይመስላል።

## What is < < ጀዝባ > > ?

ጀዝባ ለብዙዎች ድፍን ያለ አሉታዊ ትርጓሜ ይኑረው እንጂ ቃሉ ከዚህ ከፍ ያለ ትርጉም አለው። በዩኒቨርሲቲዎች በተለይም በክልል ዩኒቨርስቲዎች የሚኖሩ የራሳቸው የኾነ የተለየ ባህል፣እሴትና የአኗኗር ዘይቤን የሚከተሉ ጥቂት የተማሪ ስብስቦችን የሚወክል ነው። በአንድ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኙ በሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ውስጥ የጀዝቦቹ ቁጥር ከሀምሳ አይዘልም። የጀዝባ ኮሚኒቲ አባላት ይነስም ይብዛ በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ መኖራቸው ግን አያከራክርም።

ስሟ ለዚህ ፅሁፍ ሲባል የተቀየረላትና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋከልቲ ተማሪ የነበረችው መዓዛ ተስፋው ጅዝባና «ከፍርሃት ለመሸሽ ሲባል በተራ ነገሮች መመሰጥ ነው» ስትል ትበይነዋለች። ከሲሳይ ንጉሱ « ሰመመን» ከተሰኘው ተወዳጅ መፅሐፍ ጀምሮ «ካምፓስ» እና «ካምፓራዲ»ን የመሰሉ የፊልም ጥበቦች ጭብጣቸው በዩኒቨርሲቲ ሕይወት ላይ የሚያጠነጥን ስለነበረ በዩኒቨርሲቲ ሕይወት በተለምዶ «ጀዝባ» ተብለው የሚጠሩትን እነዚህን የተማሪ ቡድኖች እውነተኛ ማንነት እና ሕይወታቸውን ለማንፀባረቅ ሙከራ አድርገዋል። በጅዝብና ሕይወት ስድስት ዓመታትን ላጠፋው ዐብዮት ሙላቱ ግን «ሙከራዎቹ አልተሳኩም»። ምክንያቱም «ጅዝብናን ይኖሩታል እንጂ አይገልፁትማ» ሲል የጀዝባ ህይወት ረቂቅነቱን ይሰብካል። እንደ ዐብዮት ትንታኔ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ «ሀሴና እንጂ ሌላ ተቆጣጣሪ የለም»። አንድ ተማሪ ከቤቱ ርቆ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ የሃይማኖት አክራሪነትን፣የጉብዝና ምጥቀትን፣የፖለቲካ ጽንፍን ለመያዝ ወይም ላለመያዝ ለመጀመርያ ጊዜ ሙሉ ነፃነትን ይጎናጸፋል። « የዚህ ነፃነት የመጨረሻ አጽናፍ ግን ጀዝባነት ነው»። ለመቀሌ ዩኒቨርሲቲዋ መዓዛ ተስፋው ጀዝብና ከቤተሰብ ድንገት ከመለየት በኋላ ለተፈጠረ ፍርሃት መሸሸጊያ ነው የምትለውም በዚህ የተነሳ ነው። ዐብዮት በበኩሉ የመዓዛን ፍርሃት « ጥግ መያዝ» ይለዋል። «በዩኒቨርሲቲ ከተንሰራፋው የብቸኝነት ሰቆቃ፣ የኢኮኖሚ ድቀት፣የእምነት እና የብሔር ውዝግብ፤ ከዚህ ሁሉ ዶፍ ለመጠለል ጥግ የምትይዘው ጀዝባ በመኾን ነው።

ጀዝባ ኮሚኒቲን ለመቀላቀል መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። አንደኛውና ዋንኛው «ብቅድመሁኔታ የሚያምን ሰው አለመሆን ነው።» እንደ ጀዝቦቹ ገለፃ ከኾነ « ይችን አጭር ህይወት ለመኖር የሰው ልጆች ቅድመ ሁኔታም ድኅረ-ሁኔታም ማስቀመጥ የለባቸውም።»

## የዐብዮት አጭር የጅዝብና ታሪክ

ዐብዮት ሙላቱ በ1994 ዓ.ም ወደ ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ሲቀላቀል የነገው ልሂቅ የመኾን ተስፋን ቋጥሮ እንጂ በጅዝብና ማእበል እመታለሁ የሚል ሐሳብ ሽው እንኳ ብሎበት አያውቅም ነበር። ውጭ ሳለ ስለ ዩኒቨርሲቲ የሳለው ምስል በእውን አልከሰትልህ ሲለው ግን ሁነኛ መደበቂያን ፈለገ። ጀዝባ ከመሆኑ በፊት ጫትና ቢራ የምሬት ጣዕም እንዳላቸው ብቻ ያውቅ የነበረው ዐብዮት የኋላ ኋላ ግን በነርሱ ለመዘፈቅ በቃ። ያለ እነርሱ ሕይወት እንዴት እንደምትኖር አልገባህ አለው። ሰዎች በእንጀራና ዳቦ ህይወታቸውን ሲገፉ ሲያይ ጤንነታቸውን ተጠራጠረ። « ቶሎ በፍቅሩ የወደቅኹለት ነገር ቢኖር ጅዝብናን ነው» ይላል ቁዘም ብሎ።

እንደ ዐብዮት ሙላቱ ከጥብቅ የኃይማኖት ተቋማት የመጡ ኹሉ በጅዝብና ሕይወት ተማርከው እጅ ሰጥተዋል። ዐብዮት ሁለት ሁለት የቤተክርስቲያን ነጠላ ይዘው መጥተው በጅዝብና ሕይወት የተሳቡ ወዳጆቹን ያስታውሳል። እሱ «ነጠላቸውን የሰቀሉ ወዳጆቼ» እያለ ነው የሚጠራቸው።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኅብረተሰብ ሥነ-ልቦና መምህር የኾኑት አቶ ታደሰ አወቀ ዩኒቨርሲቲዎች የተቀራረበ የአኗኗር ዘይቤ ስላላቸው የባሕርይ መወራረስን እና ሽግግርን ፈጣንና ቀላል እንደሚያደርገው ያስባሉ። አራት ዓመት አብሮ በአንዲት ክፍል ውስጥ መኖር፣ ራስን ከሌሎች ጋር ማስማማትን( social conformity) ያስከትላል። ይህም ለጀዝባ ኮሚኒቲ መበራከት ጉልህ ምክንያት ሆኗል።

«ጀዝባ ለመኾን የሚጠበቅብህን ማድረግ ሳይኾን መተው ነው» ይላል ዐብዮት ሙላቱ የጀዝባነትን መለኪያዎች ሲዘረዝር። «የከረረ እምነትህን መተው፣ዙርያህን ችላ ማለት፣ ቤተሰብህን መተው፣ ማህበረሰቡ ዋጋ የሰጠውን ጉዳይ ዋጋ መንሳት፣ «ክላሶችህን መቅጣት»ና መርሳት፣ በመጨረሻም ራስህን መርሳት ለጅዝብና ማዕረግ ያበቃል።» « ፂምና ፀጉር እንደሚያድጉ ከመርሳት የበለጠ ምን እፎይታ የሚሰጥ ነገር ይኖራል?» ሲል

ይጠይቃል፣ዐብዮት። የጅዝብና ከበብን ለመቀላቀል አያሌ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። አዲስ ገቢ ተማሪዎች ቀድሞ ስለ ዩኒቨርሲቲ የሳሉት የገዘፈ ምስል በአውን አልታይ ሲላቸው ወኔያቸው ይሟሸሽል። የመማርም ሆነ የመደራጀት ፍላጎታቸው ይኮላሻል። ጀዝብና በዚህን ጊዜ እቅፏን አሙቃ ትቀበላቸዋለች።

ጅዝብና በታሪካዊ የዩኒቨርሲቲ የተማሪ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚናፈቁትን «የተማሪ ልሂቃን» መስሎ ለመገኘት የሚደረግ መፍጨርጨር አድርገው የሚመለከቱትም አልጠፉም። ሌሎች ደግሞ «ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተማሪዎች መካከል ከሚነግሰው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፉክክር ከሚፈጠር የሥነ-ልቦና ቀውስ መሸሸጊያ አድርገው ያስቡታል። የሚፈልጉትን የትምህርት ዓይነት ለማጥናት አለመቻል ብቻውን ጀዝባ ኮሚኒቲን ለመቀላቀል በቂ ምክንያት ተደርጎም ይወሰዳል። የማህበረሰብ ስነልቦና መምህሩ አቶ ታደሰ ግን በቂ ጥናት ሳይካሄድ የመንስኤ መላምቶችን መደርደር ፋይዳው አይታያቸውም።

## Kinds of ጀዝባs

ጀዝቦች « አንድም ለየቅልም ናቸው» ይላል ዐብዮት።ጭራሽ የማይቅሙ ጀዝቦች እንዳሉ ኹሉ ለ«ጀበና» (ማለዳ ለአይን መከፈቻ ያህል የሚቃም) ማልደው በ«ቃጢራ» (አዳር ሙሉ መቃም) አድረው 24 ሰዓት የማይፎርሹ «ጂኒየስ ቃሚዎች» ሞልተዋል ይሰኛል። ጥልቅ ፍልስፍናን የሚያራምዱ አንደበተ ርቱዕ ጀዝባዎች እንዳሉ ኹሉ ሕይወታቸው በጥምና ብቻ የተሞላ« የስከኑ ጀዝቦችም አሉ። ዐብዮት ለዚህ እንደማስረጃ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ይማር የነበረ ጀዝባ ወዳጁን ይጠቅሳል።« በዩኒቨርሲቲ በቆየባቸው ዓመታት በፍቅር ጫቱን ገዝቶ ሲገባ እንጂ ድምፁን ሰማን የሚል አታገኝም» ይላል ለዓመታት ከግቢው ማኅበረሰብ ተኳርፎ የኖረውን ጀዝባ ወዳጁን እያስታወሰ። ይህ ወጣት « አትረብሹኝ፤ ራሴን ፍለጋ ላይ ነኝ፣ » ይል እንደነበር ይገልፃል። በጅማ ዩኒቨርስቲ በተመሳሳይ ሕይወት ውስጥ ቆይታ የነበረው ተሾመ እየለ በእርሱ ዘመን የነበሩ ጀዝቦች ኹሉም ራሳቸውን የጣሉ እንዳልነበሩ ያስታውሳል። ኤም ጂ (Gentlemen Jezbas) ተብለው በምህፃረ ቃል የሚጠሩና ራሳቸውን በመንከባከብ የሚታወቁ የጀዝባ «ሴክቶች» እንደነበሩ ተሾመ ይናገራል። ቁጥራቸው አነስተኛ ቢኾንም ሴት ጀዝቦች በኹሉም ዩኒቨርስቲዎች መገኘታቸው አልቀረም። ሴት ጀዝቦች ጫት ወደ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ለማሳለፍ ሰፊ ዕድል ስላላቸው ለወንድ ጀዝባ ባልደረቦቻቸውም ጭምር ይተርፋሉ።

እንደ ብዙዎቹ ወንድ ጀዝቦች ራሳቸውን በከፋ ኹኔታ ባይጥሉም እንደ ሴትነታቸው ግን እምብዛምም ሲሽቀረቀሩ አይታዩም። ከአቻዎቻቸው መገለል ስለሚደርስባቸው ወንዶችን ብቻ የቅርብ ጓደኞቻቸው ለማድረግ ይገደዳሉ።

## Virtues of ጀዝባ

ዑበዮት ሙላቱ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ እንደጀዝባ በቆየባቸው ስድስት ዓመታት አያሌ መጽሐፍትን አንብቧል። የተለያዩ ቤተ-እምነቶችንም ጎብኝቷል። ከሁዳዴ እና ከረመዳን ፆም በከፊል ተሳትፏል።የዐማኑኤል ቤተክርስቲያን ስብከቶችን፣ የጁምአ ስግደቶችን፣ የፕሮቴስታንት ተማሪዎችን የአዳር ፀሎት፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የቅዳሜ ከሰዓት ቅዳሴዎችን ተካፍሏል። ይህ ሁለንተናዊነት በኹሉም ጀዝቦች ዘንድ የሚንፀባረቅ ጠባይ ባይኾንም ወጥ ኃይማኖት ያለው አጥባቂ ጀዝባ ማግኘት ግን አዳጋች ነው። በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በተደጋጋሚ በሚያገረሹ የብሔር እና የሃይማኖት ግጭቶች ላይ ጀዝቦች ያላቸው ሚናም ገለልተኛ ነው። በፖለቲካ እቅስቃሴዎችም ቢኾን ጀዝቦች ስለ ጉዳዩ ሰፊ እና ጥልቅ ትንታኔዎችን ይሰጡ ይኾናል እጂ መሪ ተዋናይ ኾነው «የትጥቅ ትግሉንም ኾነ የጎዳና ላይ ነውጡን» አይቀላቀሉም።

ጀዝቦች ተጋግዞ የመኖር ድንቅ ባህልም አላቸው። መጫምያ፣በተለይም ከፍት ጫማዎችን፣ እንዲሁም የውስጥ ሱሪ ሳይቀር በጋራ የመጠቀም ልምድን አዳብረዋል። ብዙዎቹ ጀዝቦች ሸፍን ጫማ ከማድረግ ይቆጠባሉ። በነጠላ ጫማ ሱሪያቸውን እየረገጡ የማይቆረጧቸውን ፂምና የራስ ፀጉራቸውን ያለማቋረጥ እየፈተሉ ስለሚታዩ ግቢ ውስጥ እነርሱን መለየት ለማንም አስቸጋሪ አይሆንም። « ለትምህርት፣ ከሰው ጋር ላለህ ግንኙነት፣ ለንፅህናህ፣ለማንነትህ ...ለዚህ ኹሉ ተጠንቅቀህ መኖር ነፍስህን ሲጨንቃት ጀዝባ ትኾናለህ» ትላለች የመቀሌ ዩኒቨርሲቲዋ ጀዝባ መዓዛ።

## ጀዝቦች እንደብርቅዬ እንስሳት

የማርሽት አስፋው ጅማ ዩኒቨርሲቲ በቆየችባቸው አራት አመታት የነበሩትን ጀዝቦች አሁንም ድረስ ትናፍቃቸዋለች። በሱስ መተብተባቸው ባትወድላቸውም ቀልድ አዋቂነታቸው እና አንባቢነታቸው የዩኒቨርሲቲ ህይወቷን ያጣፈጡላት ቅመሞች አድርጋ ትመለከታቸዋለች። ከዩኒቨርሲቲ ውጭ እነሱን የሚመስል ሰው የትም አለማየቷን ለመግለፅ /endemic/ ብርቅዬ

በማንበብ ላይ እንደነበር ያስታውሳል።

## ድኅረ-ታሪክ

ስድስት ዓመታትን በጅዝብና ያሳለፈው ዐብዮት ሙላቱ ዛሬ የሲቪክስ ትምህርት መምህር ነው። አሁንም ድረስ በሰዓቱ ቁርስ መብላት ያቅተዋል። ትምህርት ቤት ማልዶ መገኘት አይኾንለትም። በበቂ ኹኔታ እንኳ ለመንጠራራት የማትመቸው የዛሬዋ ቤቱ ቀጥተኛ የዶርም ሕይውቱ ቅጂ ናት። ዛሬም ፍራሹ ለረባ አንሶላ አልታደለችም። ዐብዮት የተከራያት ጎጆ ውስጥ ጎላ ብሎ የሚታይ እቃ ካለ እሱ ፍሪጅ ብሎ የሚጠራው «ኮሞዲኖ» ነው። ቤቱ ለመጣ እንግዳ «ከፍሪጅ ምን ይምጣልህ?» ብሎ ኮሞዲኖዋን ሲከፍት ቀዝቃዛ ቢራ የሚጠብቅ ካለ የዋህ ነው። የዐብዮት ፍሪጅ/ኮሞዲኖ/ ውስጥ የተደረደሩት ከዩኒቨርሲቲ ሕይወቱ ጀምሮ ያሰባሰባቸው ከሽያጭ የተረፉ አያሌ መጻሕፍት ናቸው። ዐብዮት ከጀዝባ ተማሪነት ወደ ጀዝባ መምህርነት በአንድ እርከን ያደገ ይመስላል።

© ይህ መጣጥፍ ጥቅምት 29፤2001 ታትሞ በነበረው
አዲስ ነገር ጋዜጣ የሰሻል ፊቸር አምድ ቀርቦ እንደነበር ይታወሳል።

# ከአዲግራት እስከ ዛላንበሳ፤

## ቁርጥራጭ ታሪኮች

አዲግራት ነው ያለሁት። 35 ኪሎ ሜትሮችን ወደ ሰሜን ፈቀቅ ብል ኤርትራ ገባሁ ማለት ነው። ጥሎብኝ አሥመራን እናፍቃታለሁ። አይቻት ግን አላውቅም። "የማያውቁት አገር እንዴት ይናፍቃል?!" አትበሉኝ። ተረቱ የማይሰራበት ጊዜ ሳይኖር አይቀርም። ናፍቆቴን በከፊል ለማስታገስ ወደ ድንበር መጠጋት አማረኝ። ወደ ዛላንበሳ። ያ ከመኾኑ በፊት አዲግራትን ለአጭር ቀናት መቃኘት ይኖርብኛል።

ስለ አዲግራት "አዲግራት ሳንድስቶን" ከሚለው የሰባተኛ ክፍል የኅብረተሰብ ትምህርት የዘለለ እውቀት እንደሌለኝ እረዳለሁ። ያን እነስተኛ እውቀት ከቀሰምኩ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በኋላ በዚህች ዝምተኛ ከተማ እገኛለሁ። የተለየ ስሜት አላደረብኝም። አዲግራት ምኗ ያስደምማል?

ከጦርነቱ በኋላ አዲግራት ታመመች አሉ፣ ልክ ድሬዳዋ ከባቡሩ መቆም በኋላ እንደሆነችው። ነግቶ እስኪመሽ ታዛጋለች። እንደ ጅማ ፍጹም ባታንቀላፋም፤ እንደ አዋሳ ፍጹም ባትነቃም፤ አዲግራት በእኩሌቀን እንቅልፍ ሽለብ እያደረገ የሚመልሳት ከተማ ሆነች። ብዙ የኢትዮጵያ ከተሞች ቢያንስ ሙዚቃ በስማቸው ስለሚዜምላቸው ለጊዜውም ቢሆን ውብ መስለው በሰው አእምሮ የመሳል እድል አግኝተዋል። በዚህ ረገድ ደሴን የሚስተካከል የለም። አዲግራት

ግን ለዚህም አልታደለችም። ሟቹ የጥበብ ሰው ኢያሱ በርሄ አንድ የማስተዛዘኛ ሙዚቃ እንዳዜመላት ሰምቻለሁ። ከዚያ ውጭ ስለእርሷ ስራዬ ብሎ ያዜመ እውቅ ዘፋኝ ያለም አይመስለኝም፤ ምን ብሎስ ያዜማል?

አዲግራት ዜመኞችን አላፈራችም ማለት ግን አይደለም። "የሰሜኑ ቴዲ አፍሮ" እየተባለ የሚሞካሸው ሰለሞን ሃይለ ትውልዱ አዲግራት ነው። ከዓመት በፊት "ቆሪበልኪለኹ" የተሰኘው አልበሙ በመላው ትግራይ ብሔራዊ መዝሙር እስኪመስል ከጫፍ ጫፍ ተደምጦለታል። የአዲስ አበባ ታክሲዎችም በዚህ ሙዚቃ እንደልብ ትርፍ ሰው ጭነዋል። አዲግራት ደግሞ የጆሮ ታምቡሯ እስኪበጠስ የልጇን ዜማ ደጋግማ ታስደምጣለች። ልጅ አይጠገብም አይደል?! በዋና መንገዱ ዳርቻ የተሰየሙ የሙዚቃና የኤሌክትሮኒክስ ሱቆች የሳጤ ልብስ ሳጥን የሚያካክል ድምጽ ማጉያዎችን ከደጃቸው አኑረው ይህንኑ የሰለሞን ሀይለን ጥኡም ሙዚቃ ነጋ ጠባ ለከተማዋ ያስተጋባሉ።

በነገራችሁ ላይ በአዲግራት ቆይታዬ የቴዲ አፍሮ ፖለቲካዊ መልእክት አላቸው የሚባሉ ሙዚቃዎችን እንደልብ ሲደመጡ አስተውያለሁ። ለምሳሌ በከተማዋ እምብርት የሚገኘው "ኢትዮ ሙዚቃ ቤት" "በ 17 መርፌ በጠቀመው ቁምጣ፣ ለለውጥ ያጎፈረው ዘፋን ላይ ሲወጣ..." የሚለውን ዜማ ከፍ ባለ ድምፅ ደጋግሞ ሲያስደምጥ ለመስማት ችያለሁ። ከዓመታት በፊት ይመስለኛል ከአዲስ አበባ መቀሌ ስጓዝ በአውቶብስ ውስጥ ይኸው ሙዚቃ በመከፈቱ በተጓዦች መሀል ውዝግብ ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሳለሁ። በመጨረሻም ሾፌሩ ሙዚቃውን እንዲዘጋው ተገዶ ነበር። አሁን ፖለቲካዊ መቻቻል ነግሶ ይሁን የፖለቲካ ግለቱ ተቀዛቅዞ ብቻ ቴዲ አፍሮ በአዲግራት እንደልቡ ይፈነጫል። እርሱ መድረክ ላይ ለመዝፈን ሳንሱር የሚያደርጋቸው ሙዚቃዎች በአዲግራት አደባባይ እንደልብ እንደሚከፈቱ ቴዲን የምታውቁ ሹክ በሉት። አዲግራት ሙሉ በሙሉ በተራራ መከበቧ፣ ተስማሚ የአየር ንብረት መጎናፀፏ፣ በበለስና ብርቱካን ምርት መታወቋ፣ በከፉ ከመነሳት ያዳኗት ውስን ውበቶቿ ናቸው። በተለይ የአዲግራት ጉንዳጉንዲ ብርቱካን ጣእሙ ዘላለማዊ ነው። አዲግራትን የረገጠ ብርትኳኗን ሳይሸምት እንዲወጣ አይመከርም። በኢትዮጵያ ትልቁ የመድኃኒት ፋብሪካ የሚባለውና "የትእምእት" (ኤፈርት) እህት ኩባንያ የኾነው "አዲስ መድኃኒት ፋብሪካ" ሌላው የአዲግራት ኩራት ነው። ሻእቢያ በአየር ሊደበድበው ከእንዴም ሁለቴ ቋምጦ ሰቶታል።

## ወልዋሎ

'ለአዲሳባ "ሸገር" የሚል የዳቦ ስም ከሰጠን ለአዲግራት ምን እንላለን?' ወልዋሎ" ነው መልሱ። ይህ ስም በከተማዋ ሁሉም ነገር ላይ ተፅፎ ይታያል። "ወልዋሎ ፀጉር ቤት"፣"ወልዋሎ እንዳ-ባኒ" (ዳቦ ቤት ማለት ነው)፣ "ወልዋሎ ሙዚቃ ቤት"፣ "ወልዋሎ ጥህሎ ቤት"... "ወልዋሎ ከረንቡላ"...የወልዋሎ ነገር ማቆምያ የለውም። ከ ወልዋሎ የተረፉት አገልግሎት መስጫዎች ደግሞ "አግአዚ" በሚል ነው የሚጠሩት። "አግአዚ" በአዲግራት ከተማ ከትምህርት ቤት እስከ ቡና ቤት ያለ ማንኛውም ድርጅት ሊጠራበት የሚችል ስም ነው። አግአዚ ቡቲክ፣አግአዚ ኢንተርኔት፣ አግአዚ ትምህርት ቤት፣አግአዚ መሸታ ቤት...ወዘተ

በከተማዋ የሚገኘው ቁጥር አንድ የምሽት ክለብ "ፍሪ -ዞን" ይባላል። ለመዲናችን አዲስ አበባ እንኳ የሚመጥን ዘመናዊ ክለብ ነበር። ሆኖም ክለቡ ከከተማዋ በብዙ እርምጃ በመቅደሙ ይመስላል በገበያ እጦት ተዘግቷል። የዛሬን አያድርገውና አዲግራት የምቀች-ያበደች፣ አሸሼ ገዳሜ የሚባልባት ከተማ ነበረች አሉ። የድንበር ጦርነት ጉሮሮዋን ዘጋው። ብዙዎቹ ነዋሪዎቿም ተሰደዱ፣ ወደ መቀሌ፣ወደ አዲሳባ።

ጉራጌዎችና አዲግራቶች በኢትዮጵያ የሰሜንና የደቡብ ዋልታ ጫፍ የሚገኙ ሕዝቦች ናቸው። ሕይወታቸው ግን እንደመገኛቸው አይራራቅም። አንድ ትግሬ እሳት የላስ ነጋዴ ከሆነ ትውልዱ አዲግራት እንደሆነ ትጠረጥራለህ። በአብዛኛው ግምትህ ልክ ሆኖ ታገኘዋለህ። "ንሱ እኮ ወዲ አዲግራት እዩ" ከተባለ በቢዝነስ እየገሰገሰ እንደሆነ ይገባኻል። ወልዋሎዎች "የትግሬ ጉራጌዎች" የሚባሉትም ለዚሁ ነው። አዲሳባ "ሃያ ሁለት" በሚባለው ሰፈር ዞር ዞር ስትል የሚያፈጡብህ ብዙዎቹ መለሎ ሕንፃዎች በትግራይ ተወላጆች የተያዙ ናቸው – ከትግራይም በአዲግራቶች። የሳትኮን ባለቤት አቶ ሳሙኤል ተኽላይ የአዲግራትን አፈር ፈጭተው ነው ያደጉት።

በቀድሞ ጊዜ ለኤርትራ ንግድ እንቅስቃሴ የደም ዝውውር መሆን የቻሉትም አዲግራቶች ነበሩ ይባላል። ኤርትራዎች አዲግራቶችን "ኢጋመ" ይሏቸዋል። ስድብ መሆኑ ነው አሉ። አንድን ጉራጌ "ጉራጌ" ብሎ እንደመሳደብ። አንድ አዲግራታዊ ወዳጅህ የ"ኢጋመ ልጅ ነኝ" ሲልህ ግን በታላቅ ኩራት ነው። በአዲግራት ምድር "ኢጋመ" የሚለው ቃል የኩራት ምንጭ ነው። "ጓል ኢጋሜ" የሚል ጽሑፍ ለጥፈው የሚንቀሳቀሱ ባጃጆችን በከተማዋ በብዛት አይቻለሁ።

የአዲግራቱ ወዳጄ የዚያን ጊዜ የዘሙቱ ተማሪዎች ብዙዎቹ እንዳለቁ ነግሮኛል፤ "የተረፉት ግን አሁን መከላከያ ውስጥ ጥሩ ቦታ ተሰጥቷቸዋል።" ይላል። በጦርነቱ ለመሳተፍ የሄዱ አባወራዎች ደግሞ እንደ ምንዳ የአካበቢው ህዝብ ተራ በተራ ማሳቸውን እንዲያርስ፣ ቤታቸውን እንዲከባከብ ይገደድ ነበር። የአዲግራት ወዳጄ ጨምሮ እንዳወራኝ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ለሟች ቤተሰቦች መርዶ ማርዳት ሲጀመር አዲግራትና አጎራባች የገጠር ሰፈሮቿ ወደ ትልቅ ድንኳንነት ተቀየሩ። በእያንዳንዱ የሰፈር ጎዳና የለቅሶ ድንኳን መትከል ግድ ነበር። የድንኳን ተራ ያልደረሳቸው ሜዳ ላይ ለቅሶ ለመቀመጥ ተገደዋል። እስካሁንም ትርጉሙ ላልገባን ጦርነት አዲግራትና ዙርያ ገብ የገጠር ቀበሌዎቿ ከሌሎች ከተሞች በበለጠ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል።

የአዲሳባ ህዝብ ይህን ጦርነት በአመዛኙ በቴሌቪዥን መስኮት እና በአለምነህ ዋሴ ድምፅ ነው የተከታተለው ማለት ይቻላል። የከፈለው ዋጋ ከትግራይ ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

ሰሜን ምእራብ ትግራይ ሰመማ በሚባል አካባቢ ተወላጅ የኾነ ወጣት እንዲህ አለኝ።

« ያኔ 8ኛ ክፍል ነበርኩ። በጦርነቱ ምክንያት ቀን ቀን ሻእቢያ እንዳትደበድበን በመፍራት የምንማረው ማታ ማታ እንዲሆን ተደረገ። እየተማርን እያለ ሚሊሻዎች ክፍላችን ድንገት ዘው ብለው ይገቡና ከኃላ ወንበር የተቀመጡ ጎረምሶችን ሰብስበው ይዘዋቸው ይሄዳሉ። እንዲህ እንዲህ እያሉ ክፍላችንን ባዶ አደረጉት። እኔም ተወስጄ ሰውነቴ ቀጫጫ ስለነበረ ነው የተረፍኩት። አስተማሪያችን ሁልጊዜም ክፍል ሲመጣ ሽጉጡ ይዞ ነበር የሚመጣው፤ ለጥንቃቄ። ሽጉጡን ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጥና በቾክ ያስተምረናል። ሲጨርስ ሽጉጡን ይዞ ይወጣል።»

«የተወሰኑ የክፍል ጓደኞቼ ከማሰልጠኛ ጣብያ እያመለጡ ጠፉ። ብዙዎቹ ግን በጦርነቱ አልቀዋል። ያኔ ወደ ግንባር ያልሄድን ልጆች የመጀመርያ እርዳታ አሰጣጥ ትምህርት ተሰጥቶን ቀን ቀን የቆሰሉ ወታደሮችን ቁስል ስናሽግ እንውል ነበር።»

« የሰፈራችን ሰው በጦርነቱ ምክንያት ተኳርፎ ነበር። ምክንያቱም ለሚሊሻዎች "የኔ ልጅ ጦር ሜዳ ተወስዶ የእከሌ ጎረምሳ ለምንድነው የቀረው?" እያለ አንዱ በአንዱ ላይ መጠቋቆም በመጀመሩ ሰው እርስ በእርስ ተባላ። የታፈሱ ወጣቶች የሚጫኑት «ሸዊት» በሚባል መርሴዲስ

የጭነት መኪና ላይ ነበር። እናቶች ልጆቻቸው ወደዚህ የጭነት መኪና ሲጫኑባቸው እያለቀሱ መኪናውን ሲከተሉት ትዝ ይለኛል።»

«ከጦርነቱ በኃላም ሚሊሻዎች የአካባቢውን ሰው "ለቅሶና ተዝካራችሁን በአንድ ዳስ በአንድ ላይ ፈፅሙ" በማለት ማስገደድ ጀመሩ። ነዋሪው ደግሞ በተናጥል በፈለግነው መልኩ ማድረግ መብታችን ነው በሚል ተቃወመ። "ልጆቻችንን አስጨርሳችሁ እንደገና በተዝካራችን ልታዙ ያምራችኃል እንዴ?" በሚል በተነሳ ቅራኔ በአካባቢው ከረር ያለ የርስ በርስ ግጭት ተፈጥሮ ነበር።»

## ቆንጆዎቹ እናቶች

እንደ አዲግራት ብዙ የኔ ቢጤዎች ያየሁበት ከተማ እምብዛምም ነው። ፒያሳ በሚባለው የከተማዋ እንብርት "ወልዋሎ ካፌ" በረንዳ ላይ ተሰይሚያለሁ። ማኪያቶ ፉት እያልኩ ለአመል ያክል ያያዝኩትን የጉዞ መጽሐፍ እያገላበጥኩ፤ በአንድ ዐይኔ ከተማዋን እታዘባለሁ። ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል በዚህ ሁኔታ ተቀመጥኩ። በቆይታዬ ምፅዋት የሚጠይቁን ለማኞች ቁጥር በአእምሮዬ ለማስላት ሞከርኩ። ከሰላሳ ይልቃሉ። ከእነዚህ መካከል እጅግ የበዙቱ እድሜያቸው የገፉ የትግራይ እናቶች ናቸው። "ይርደአኹም" የምትለዋን ቁልፍ ቃል ያላወቀ እንግዳ በእያት ቅድመ እያት የኔ ቢጤዎች ያልተቋረጠ ተማፅኖ ስሜቱ ሊረበሽ ይችላል። መላው ትግራይ እንዲሁ ነው። በትግራይ ከተሞች በተዘዋወርኩባቸው ግዜያት ሁሉ ቅስም የሚሰብር፣ ስሜት የሚረብሽ ክስተት የሚገጥመኝ ትግራዊ እናቶችን ስመለከት ነው። በሚሞቀው ፈገግታቸው ውስጥ መከራ ይታያል። በቆንጆ ፊታቸው ግንባር ላይ ረዥም የእድሜ መሰመሮች ይጎላሉ። መሰመሮቹ የእድሜ መስመር ብቻ አይመስሉም። ዘርፈ ብዙ የዘመናት ችግራቸውን ያሳብቃሉ። በክልሉ ለዓመታት የተካሄዱ ጦርነቶቹ ልጆቻቸውን፣ ሀብታቸውን፣ ተስፋቸውን ነጥቀዋቸዋል። ብዙ ጦርነቶች፣ ብዙ የፍትሕ እጦቶች፣ ብዙ ረሀቦች፣ ብዙ በደሎች የማያልቁ የሚመስሉ፣ እስከአሁንም ያላለቁ። ስልጣን የያዙ ልጆቻቸው እንኳ ሊፈቱት ያልቻሉት ዉዝፍ እዳ።

"ወልዋሎ ካፌ" ደጅ ላይ መሰየሜን አትርሱ። ከለማኞቹ ጎን ለጎን ከዋናው አስፋልት ላይ ጥቂት የአእምሮ ህመምተኞች ይታዩኛል። እኔ ከተቀመጥኩባት "ወልዋሎ ካፌ" ትይዩ የከተማዋ ዝነኛ "እብድ" በእንጨት የሰራውን የጦር መሳርያ እያቀባበለ በመተኮስ ራሱን ያዝናናል።

ስለዚህ "አብድ" ብዙ ማወቅ ፈለኩኝ። ወታደር እንደነበረና በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት መካፈሉ ተነገረኝ። ከዚያ በላይ ስለሱ የሚያውቅ አላገኘሁም። ወልዋሎ ካፌን ለመልቀቅ ሂሳብ ስከፍል "አብዱ" የእንጨት ጠመንጃውን ወደ እኔ አቀባብሎ እየተኮሰ ነበር።

## ወዲ ገሰሰ

ወዲ ገሰሰ አለማያ ዩኒቨርሲቲ አብሮኝ የተማረ ወጣት ነው። የአራት ዓመት የዲግሪ ትምህርቱን ለመጨረስ 7 ዓመት ፈጅቶበት ነበር።ዩኒቨርሲቲ እንደገባ የአሉላ አባነጋ የቅርብ ዘመድ እንደሆነ በማስወራቱ ስሙ በዩኒቨርሲቲው ገነነ። ሁለተኛ ዓመት ስንደርስ ደግሞ "አፄ ዮሃንስ አራተኛ የእናቴ የቅርብ ዘመድ ናቸው" ሲል ዘር ቆጥሮ፣ ፍሬሽማን ላይ የወሰደውን የኢትዮጵያን ታሪክ አጣቅሶ ተሟገተ። በዚህም የብዙ ተማሪዎች መጠቋቆሚያ ለመሆን በቃ። ከተማሪ ዐይን ለመሰወር ግን ሱስ ውስጥ መደበቅ ነበረበት።ወዲ ገሰሰ በከፍተኛ የጫትና የአደገኛ እፅ ሱስ ከመጠቃቱ በፊት ይፈጥራቸው በነበሩ ቀልዶቹ ይታወቅ ነበር። በእርሱ ስም የተመዘገበች ቀልድ ዛሬም ድረስ አትረሳም። ላካፍላችሁ።

በአለማያ ዩኒቨርሲቲ አብዝተው ስለ አሳ ሀብትና ስለ አለማያ ሀይቅ ይጨነቁ የነበሩ ዶክተር ነበሩ። ዶክተር ብሩክ ይባላሉ። ሌሊት ሌሊት እየተነሡ በአለማያ ሀይቅ ላይ ምርምር ያደርጉ ነበር። ዘወትር ለዓሳ ሀብት እንደተጨነቁ ነው የኖሩት። ወዲ ገሰሰ ታድያ አንድ ወቅት ላይ በአገሩ የአዲግራት ልጆች "ፈተና እየደረሰ ነው፤ አጥና፤ ኋላ ይቆጭሃል" የሚል ምክር ሲለገሰው እንዲህ አለ፦ "who cares about the dead fish except Dr. Brook."

ዶክተር ብሩክ ዛሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም ምክትል ዲን ናቸው። ወዲ ገሰሰ ግን በአዲግራት ከተማ ቪዲዮ ቤት ቆሞ ፊልም ይተረጉማል። ዲግሪ ይዘህ እንዴት ይህን ስራ ትሰራለህ አልኩት። "who cares about the dead fish…" አለኝ፣ ሲጋራውን ፊቴ ላይ እያቦነነ። ወዲ ገሰሰ ይህንን አባባሉን እስከዛሬም አልተወውም ማለት ነው። ወደ "አብደት" ሰፈር እያመራ ለመሆኑ ቅንጣት ታክል አልተጠራጠርኩም። ወዲ ገሰሰ የዘመኑን ወጣቶች ይወክላል። መሄጃ ያጡ፤ ግራ የተጋቡ፣ ራዕያቸውን የተነጠቁ ወጣቶች። ዲግሪ ይዘው ፊልም ቤት ቆመው የህንድ ፊልም የሚተረጉሙ ወጣቶች። who cares about the dead fish ….!

## የእነ አርከበ ቤት

አዲግራት "ፒያሳ" እያለች የምትጠራው ሰፈሯ በብዙ ለማኞች፣ በብዙ ሙዚቃ ቤቶችና በጥቂት የአእምሮ ህመምተኞች የተሞላ ነው። በዚህ ሰፈር አንድ ባለአንድ ፎቅ ቀይ ቡኒ ሕንፃ ይታያል። የቀድሞ የ "አግአዚ ትምህርት ቤት" ተማሪዎች "አልሙናይ ኅብረት ጽ/ቤት" ነው። በቀድሞው ዘመን ትግራይ ውስጥ የትምህርት እድል ለማግኘት ሦስት ቦታዎች ብቻ ነበሩ። አቶ መለስ የተማሩበት የእድዋው ንግሥተ ሳባ፣ እያሱ በርሄ የተማረበት የመቀሌው አፄ ዮሃንስ እና የአዲግራቱ አግአዚ ናቸው። እንደተነገረኝ ከሆነ የአዲግራቱ "አግአዚ ትምህርት ቤት" የአሁኖቹን ትላልቅ ባለስልጣናት አስተምሯል። አቶ ስዩም መስፍን፣ ሜጀር ጀነራል ሀየሎም አርአያ/ሽሬ አዲ ነብሪድ ቢወለድም/ ፣ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖም / ሰነዶች አስመራ እንደተማሩ ቢመሰክሩም/፣ አቶ ታደሰ ሀይለ፣ አቶ አርከበ እቁባይ ወዘተ የዚሁ ትምህርት ቤት ፍሬዎች ናቸው። ዶ/ር ቴዎድሮስ የአስመራ ልጅ ናቸው የሚለው ወሬ የሚያመዝን ቢሆንም አዲግራቶች ግን የኛ ልጅ ናቸው ይላሉ።

የተወዳጁን የቀድሞ የአዲሳባ ከንቲባ የአርከበ እቁባይን ቤት እናሳይህ ሲሉኝ በዙርያው ‹‹አርከበ ሱቆች›› አይጠፉም ብዬ ለራሴ ቀለድኩ።ብዙም አልተሳሳትኩም። የነአርከበ ቤት በዋናው የአዲግራት መንገድ በስተቀኝ "እስላም መቃብር" ፊት ለፊት ይገኛል። 500ካሬ ላይ ያረፈ በድንጋይ ርብራብ የታጠረ የገጠር ቤት ነው። ዙርያውን ተሸንሽኖ ለሱቆች ተከራይቷል። "ጂኤም ፀጉር ቤት"፣ "ፍስሀ ክሊኒክ"፣ "ቲዜድ መስታወት ስራ"፣ እና አንድ ስም ያልተሰጠው ፑል ቤት የነአርከበን ቤት ተከራይተው ይነግዱበታል። የአቶ አርከበ ወንድም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቤቱን ይቆጣጠር እንደነበረ ተነግሮኛል። አቶ አርከበ ልምድ የቀሰሙት ከቤታቸው ኖሯል።

እንደ መቀሌ ሁሉ በአዲግራትም የአቶ መለስ ምስል ያለበትን ነገር መጠቆም ቀላል ነው። ብዙ ነዋሪዎች የርሳቸው ምስል ያለበትን ቲሸርት ለብሰው ይታያሉ፤ ምፅዋት ጠያቂዎችን ጨምሮ። ባጃጆች ላይ "ረኽቦም እድሜ ለአቶ መለስ" የሚል ጽሑፍ ተመልክቻለሁ። ፀጉር ቤት ውስጥ የፀጉር ቁርጥ አይነቶችን በሚያሳዩ ፖስተሮች መሀል የአቶ መለስ ግርማ ሞገስ ያለው ፎቶ ተሰቅሎ አስተውያለሁ።

እነአርከበ ቤት ከፊሉ ለፑል ቤት እንደተከራየ ነግርያችሁ ነበር። በዚሁ ፑል ቤት ጎራ

ብዬ ከአዲግራት ልጆች ጋር ፑል በገጠምኩ ጊዜ ያየሁትም ይህንኑ ነው። በፑል ቤቱ ግድግዳ ዙርያ ብዙ የምእራቡ አለም የራፕና የሂፕሆፕ ዜመኞች ፎቶ ተለጥፏል። አነ አር ኬሊ፣ብሪትኒ ስፒርስ፣ 50ሴንት፣ ጂ ዩኒት፣ ጀኔት ጃክሰን፣ ጀኒፈር ሎፔዝ፣ ሻኪራ፣ ቢዮንሴ፣ ጄይዚ ወዘተ ሰውነታቸውን ተገላልጠው የተነሷቸው ባለቀለም ፎቶዎች ተሰቅለዋል። በእነዚህ መሀል የአቶ መለስ ፎቶ ሰርጎ ገብቷል።

ይህ የአቶ መለሰ ፎቶ የሚገኘው "ማርያም ጠብቂኝ" የሚል የቅድስት ማርያም ፎቶ ስር መሆኑ ነገሩን ይበልጥ አስገራሚ ያደርገዋል። አቶ መለስ ካፖርት ለብሰው ሞባይል እያናገሩ ይታያሉ። "እመቤቴ ጠብቂልኝ" የሚል ትርጉም እንዲኖረው ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። የአቶ መለስን ፎቶ ከቅድስት ማርያም ምስል ስር የማስቀመጡን ነገር ኢንተርኔት ለመጠቀም በገባሁባቸው ሁለት ካፌዎች ውስጥም ተመልክቻለሁ። የተሰጠኝ ማብራርያ እኔው እንደገመትኩት አይነት ነው። "እመቤቴ እንድትጠብቅልን ነው" ብላኛለች አንዲት በጽሕፈት ሥራ የምትተዳደር ሴት። ነገሩ ሰምና ወርቅ ይሁን አይሁን ግን ለማረጋገጥ አልቻልም።

አዲግራት የቀድሞው ውጭ ጉዳይ ሚነስትራችን የአሁኑ የቻይና አምባሳደራችን  የክቡር አምባሳደር ስዩም መስፍን አገር ናት። የአቶ ስዩም መስፍን አማቾች ደግሞ በአዲግራት ቁጥር አንድ ዝነኛ ጠጅ ቤት አላቸው። ‹እንዳ ግራዝማች በርሄ ጠጅ ቤት› ይባላል። የአዲግራት ነዋሪዎች « እንዳ ግራዝማች ንኺድሞ ሜስ ንስተ» እያሉ ይቀጣጠራሉ። አዲግራት ዜሮ ሽድሽተ በሚባለው ሰፈር ከማዘጋጃ ቤቱ ትንሽ  ገባ ብሎ ይገኛል።

የአቶ ስዩም መስፍን ባለቤት ወይዘሮ ፈለገ በርሄ ይባላሉ። ታዋቂው ኢኮኖሚስት ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በርሄ የአቶ ስዩም መስፍን ባለቤት ወንድም ናቸው። ሁለቱም የግራዝማች በርሄ ልጆች ናቸው። የአዲግራቱን ጠጅ ቤት አሁን ማን እንደሚያስተዳድረው ግን ማወቅ አልቻልኩም።

በ«እንዳ ግራዝማች በርሄ ጠጅ ቤት» ምን በመሰለ የማር ጠጅ ፖለቲካን ማወራረድ የተለመደ ነው። ነጣ ያለ ጋቢ ያጣፉ አዛውንት የማር ጠጃቸውን በብርሌ ይዘው የደደቢት በረሃ ትዝታዎቻቸውን ሲተርኩ አፍ ያስከፍታሉ። በነ ግራዝማች ጠጅ ቤት ማን ምን ይኹን አይታወቅም። ቆንጥር ገመገሙ ሳይበግራቸው በረሃ ለበረሃ ተዋግተው ከደርግ ነፃ

ያወጡህ ሰው ከጎንህ በአግዳሚ ወንበር ቁጭ ብለው በጥሞና እየጠጡ ሊኾን ይችላል። ልብ በል! የታገሉት ሁሉ ሚኒስትር አልኾኑም። አንዳንዶቹ ዛሬም ቀላል ህይወትን ይመራሉ። ከነዚህ መሀል አንዳንዶቹን እንዳ ግራዝማች ጠጅ ቤት ኢታጣቸውም።

## <u>የአዲግራት ኃይማኖት</u>

በኢትዮጵያ በዕድሜ አንጋፋው ከሚባሉት የካቶሊክ ካቴድራሎች ውስጥ አንዱ የሚገኘው በአዲግራት ነው። ለከተማዋ ግርማ ሞገስ አላብሷታል። አባ ወልደ ሥላሴ ተስፋዬ ይባላሉ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ። በአክብሮት ተቀብለው አስተናገዱኝ። ወደ መቅደስ ይዘውኝ ገብተው የሎሬት ሜተር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን ድንቅ ስእል አስጎበኙኝ። ስእሉ በመቅደሱ የፊት ለፊት ግድግዳ በትልቁ ተዘርግቶ ይታያል። አርቲስት አፈወርቅ ይህንን ስእል የሰራው በ1967 ሲሆን ግማሽ ብር ብቻ ተከፍሎት ቀሪውን በበጎ ፍቃደኝነት ነው እንደሰሩት ተነገረኝ።

አንጋፋው ካቴድራል በ1947 ነው ግንባታው የተጀመረው፤ የሚገርመው ካቴድራሉ በ1960 ሲመረቅ የእስልምናና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በግ አርደው ደግሰዋል። ያኔ የተጀመረው የሃይማኖቶቹ ወንድማማችነት ዛሬ አድጎና ተመንድጎ በሚያስገርም ደረጃ ላይ ይገኛል።

ለምሳሌ አባ ወልደ ሥላሴ ቢሮ ስትገቡ በወርቃማ ቀለም የተጻፈ የምስክር ወረቀት ታያላችሁ። "አላሁ አክበር" የሚል ቃል በጉልህ ተጽፎበታል። ትገረማላችሁ። የአዲግራት ሙስሊሞች አንዋር መስጊድን ሲገነቡ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የገንዘብ መዋጮ እና ሌሎች ድጋፎችን በማድረጓ የተሰጣት የምስክር ወረቀት ነው።

አዲግራት የሚገኘውን የጎልጎታ መድኀኔዓለም ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ማን ያሠራው ይመስላችኋል? ከሙስሊምና ከካቶሊክ አማኞች የተውጣጣ ኮሚቴ ከኦርቶዶክስ ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን ነው ያነፁት። ይህ በጆሮዬ የሰማሁት፣ በካሜራው ያስቀረሁት እውነታ ነው። ሦስቱ ኃይማኖቶች "መድኀን ለድኅነት ሕይወት" የተሰኘ ማኅበር በጋራ መሥርተው ይንቀሳቀሳሉ። አቅም ያጡትን ይደግፋሉ። ቤተ እምነቶችን ያስገነባሉ። የተቸገሩ ይጠራሉ። እኔ በጎበኘኋቸው ጊዜ የደርግ ተጎጂ ቤተሰቦችን በይቅርታው ጉዳይ በማነጋገር ሥራ ተጠምደው ነበር። አባ ወልደ ሥላሴ ጠረጴዛቸው ላይ አንድ ደብዳቤ

አንስተው አሳዩኝ። ያን ቀን ሙስሊሞች ለምሳ ግብዣ እርሳቸው እንዲገኙላቸው የላኩት ደብዳቤ ነው።

አባ ወልደ ሥላሴ በአዲግራት ካቴድራል ከሎሬት አፈወርቅ ስእል ባሻገር በትንሽ የመስታወት ብልቃጥ የተቀመጠ ነገር አሳዩኝ።ለቤተክርስቲያኑ በረከት ሲባል ከማዘር ቴሬሳ ሰውነት ተወስዶ የተቀመጠ የስጋ ቁራጭ ነበር። በብዙ ሀገራት ባሉ ካቴድራሎች ይህ የማዘር ቴሬዛ የስጋ ቡራኬ ይገኛል።

ማዘር ቴሬሳ ሶስት ጊዜ ኢትዮጵያን እንደጎበኙ ተነግሮኛል። ከዓመት በፊት የመቀሌ ደንቦስኮ የካቶሊክ ማእከልን ስጎበኝ ያገኘኋቸው በእድሜ የገፉ ህንዳዊት መነኩሲት እንደነገሩኝ ከሆነ ከማዘር ቴሬሳ ጋር ሆነው መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ጎብኝተውታል። በሕዝቦቹ ላይ በደል እንዳያደርስ በግልጽ ተማጽነውትም ነበር። የቅድስት ማርያምን ምስልም በስጦታ መልክ ሲያበረክቱለት "ኃይለማርያም የሚለው የስምህ ትርጉም 'የማርያም ኃይል' ማለት ስለሆነ ነው ይህንን የምሰጥህ" ብለውት ነበር። "መንግሥቱም በስጦታው እጅግ ተደሰተ" ብለውኛል መነኩሲቷ።

አዲግራት መሞካሸት ካለባት በሃይማኖት ተከታዮቿ መልካም የእርስ በርስ ቁርኝት መሆን ይኖርበታል። ሙስሊሞች ቤተክርስቲያን ሲሰራ እገዛ አድርገዋል። ካቶሊኮችና ኦርቶዶክሶች የማህሌት ቅዳሴን ተራ በተራ አንዱ የአንደኛው ቤተ መቅደስ በመሄድ ያካሂዳሉ። መስጊድ በማሰራት ፍቅራቸውን ገልፀዋል። ይህንንም በአዲግራት ቆይታዬ እውነት መሆኑን አረጋግጫለሁ። አባ ወልደ ሥላሴን ተሰናብቼ ስወጣ "ኢትዮጵያን ወደፊት የሃይማኖት ግጭት ያሰጋታልን?" ብዬ ጠየቅኳቸው። በዝምታ ተዋጡ። ያሳሰባቸው ነገር ያለ ይመስላል።

## <u>ጉዞ ወደ ዛላንበሳ</u>

አዲግራት በቃችኝ።አሁን ወደ ኤርትራ መጠጋት ይኖርብኛል።የአዲግራቱ ወያላ "ዛላንበሳ! ዛላንበሳ! ሀደ ሰብ ዛላንበሳ!" እያለ ጮኾ ተጣራ። ተጠጋሁት። "እተው እተው…ቀልጥፍ" አለኝ። ተሳፈርኩኝ። ከአዲግራት ወደ ዛላንበሳ ለመሳፈር 10 ብር መያዝ በቂ ነው። ሚኒባሱ እኔ ከተቀመጥኩበት የኋላ ወንበር ስር ኩልል ያለ ድምፅ የሚያወጣ ስፒከር ተገጥሞለታል። በስፒከሩ ኤርትራዊው አብረሃም አፈወርቂ ለብቻው ነግሶበታል፤ ኢሳያስ

አፈወርቂ በአሥመራ ብቻቸውን እንደነገሡት አይነት። "ሰማይ፣ ፈቅረይ፣ ፊቪክ በሊ፣ ሚስጥር ፊቅሪ፣ ሀደራ፣ ሸኮር ...." የተሰኙትን ዜማዎች እያከታተለ ይጫወታል።

የታከሲው መጋረጃ "ይከፈት-አይከፈት" በሚለው ክርክር ውስጥ ከጎኔ ከተቀመጠው ጎልማሳ ሰው ጋር ተግባባሁ። በትግርኛ የተጀመረው ትውውቃችን እኔ ቋንቋው ላይ ባሳየሁት መደነቃቀፍ ወደ አማርኛ ተሸጋገረልኝ። ጎልማሳው ሰው ጥርት ያለ አማርኛ ይናገራል። ፋታ አልሰጠሁትም። በጥያቄ አጣደፍኩት። መልካም ሰው ነው። በግራና ቀኝ የምናልፋቸውን ተራራዎች እያመለከተ ስምና ወርቃቸውን፣ ታሪክና ገድላቸውን፣ አንድ በአንድ ተረከልኝ። በከፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" ቅፆች ብቻ እውቀው የነበረውን የአሲምባ ተራራን በስተቀኛችን በርቀት አመላከተኝ። የአይጋ ተራራዎችንም እንዲሁ። በወጋች መሀል ከኤርትራ ጋር ያደረግነውን ውጊያ አነሳሁበት። "እንደሚባለው ብዙ ሰው ሞቷል እንዴ?" ፈራ ተባ እያልኩ ጠየቅኩ።

ምላሹን በለበጣ ፈገግታ ብቻ ገለጸልኝ። ለተወሰነ ርቀት በዝምታ ከተጓዝን በኋላ አንዲት ኮረብታ አመላከተኝ። "እዚህች ጋ ብቻ አንድ ሻለቃ አልቃለች።" ለወታደራዊ ቋንቋዎች ባእድ ስለሆንኩ አንድ ሻለቃ ስንት ወታደር እንደምትይዝ መጠየቅ አሳፍሮኝ ሐዘኔን ጭንቅላቴን በመወዝወዝ ገለጽኩለት።

"ያችን ደግሞ አየሃት? ሻዕቢያ ብዙ ሕይወት ከፍሎባታል፤ ያችን ደግሞ እያት ትንቅንቅ ነበር፤ ፈንጅ ቀብረውብን መከራ አበሉን። ይችን አየሃት? 'ፋፂ ከተማ' ትባላለች። ይህ የምታየው ተራራ ደግሞ 'አምባህይወት' ይባላል። ሲተረጎም 'ታደጋቸው' እንደማለት ነው። ይህ ተራራ ባይኖር ኖሮ በዚህች ከተማ አንድም ሰው አይተርፍም ነበር። ሻእቢያ በተደጋጋሚ በአየር ሲደበድባት ተራራው ከለላ ሆኖ ነው ሕዝቡ የተረፈው። ...ያችን ደግሞ..እያት ...ወዲያ ማዶ....ይችን ኖ...ኖ ይችኛዋ ኮረብታ.... አየሃት አይደል... እዛ በአንድ ሌሊት ያለቀው....ደግሞ....።"

ጎልማሳው ሰው ከታክሲው በስተግራና በስተቀኝ እንደ ፔንዱለም እየወዘዘወዘ ተራሮቹን አስቃኘኝ። የሁሉም ተራራች ገድል ጦርነት ነው። ሞት ነው፤ እልቂት ነው። በሚኒባሷ ውስጥ አብረሃም አፈወርቂ ውብ የፍቅር ዜማ[illegible] በሚስረቀረቅ ድምፁ ያዜማል። እርሱ ፍቅርን ያዚም እንጂ አድማጮቹ የሚግር[illegible] ሲግባቡ የኖሩትም በአመዛኙ በጦርነት ቋንቋ ነው።

ሚኒባሷ የሰሜን አቅጣጫን እንደያዘች በአብረሃም አፈወርቂ ዜማ ታጅባ ነጎደች። ከጎኔ የተቀመጠው ጎልማሳው ሰው ከፋፂ ከተማ ትንሽ ኪሎ ሜትር ወደሰሜን እንደተጓዝን "እኔ መውረጃዬ ደርሷል፣ ደህና ሁን" ብሎ ተሰናበተኝ። ምስጋናዬን ሳልጨርስ ሰውየው በሚገርም ቅልጥፍና ከታከሲው ዱብ ብሎ ወረደ። ምድረ በዳ ላይ። " በዚህ ምድረ በዳ ይህ ሰው ምን ይሰራል? ስል ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። በመስኮት አሻግሬ አየሁት። ጥቂት ወታደሮች በተጠንቀቅ ሰላምታ ሲሰጡት ተመለከትኩ…በ..ር…ቀ…ት።

## ኦሮማይ !

ዛላንበሳ ደርሻለሁ። ከአንድ ኢትዮጵያዊ ቤት ጓሮ ቆሜያለሁ፤ ብታምኑም ባታምኑም ኤርትራን በቅርብ ርቀት እያየኋት ነው። ድንጋይ ተነባብሮ የተሠሩ የኤርትራ ቤቶች ቁልጭ ብለው ይታዩኛል። አንድ አነስተኛ የኤርትራ ቤተክርስቲያንም ጉልላቷ ይታየኛል። እንደ ትግራዊ አረኛ "ሰማእንዶ!" እያልኩ ጮኽ ብዬ ብጣራ እንኳ አቤት! ሊሉኝ የሚችሉ ኤርትራውያን አይጠፉም። በአንድ ኢትዮጵያዊ ቤት ጓሮ ቆሜ በቅርብ የማያት ሆኖም የማልረግጣት፣ የማልነካት ይህች የኤርትራ ደቡባዊ የገጠር ከተማ "አምበስተገለባ" ትባላለች። ቢያንስ በፎቶ ምስሏን ለማስቀረት ተጣደፍኩኝ። ካሜራዬ ይህችን የገጠር ከተማ እጅግ አቅርቦ አሳየኝ። እንደ ልጅ ቦረቅኩ። በካሜራዬ ሌንስ ውስጥ የአምበስተገለባ ልጆች ሲጫወቱ ይታዩኛል። አንድ ትምህርት ቤት፣ አንድ ቤተ ክርስቲያን ቁልጭ ብለው ይታዩኛል። የሌላ አገር ሰዎች፣ የጎረቤት አገር ሰዎች፣ የኤርትራ ሰዎች መባላቸው ፍፁም ሊዋጥልኝ አልቻለም።

«አምበስተገለባ» ቅርቧ የገጠር ከተማ ትሁን እንጂ እኔ ከቆምኩበት በስተሰሜን በ24 ኪሌ ሜትር ርቀት ደግሞ "ሰንአፍ" ትገኛለች ተብያለሁ፤ ከእኔ በ140 ኪሌ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ከተማ ማን የምትኾን ይመስላችኃል?! አሥመራ።

ዛላንበሳ በጦርነቱ ለኤርትራ እጇን ሰጥታ ነበር። የኃላ ኃላ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰች። ኾኖም ዛላንበሳ ፈርሳ የተገነባች ከተማ ናት፤ ለዚያውም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እርዳታ። በጦርነቱ ሻእቢያ ያፈራረሳቸው ቤቶች አሁንም ፍርስራሻቸው ተከምሮ ይታያል። የተወሰኑ አዳዲስ ቤቶች ተገንብተዋል። ለአንድ ፈርሶ ለነበረ ቤት 60 ሺህ ብርና ከዚያ በታች እርዳታ ተደርጎ ነው ከተማዋ ዳግም ነፍስ የዘራችው። በከተማዋ አንድዬ አስፋልት ላይ ታች ሲሉ የሚታዩት የመከላከያ ዩኒፎርም የለበሱ ሰዎች ናቸው። የከተማዋ የቤት

መኪናዎች ደግሞ የወታደር "እራል" መኪኖች ናቸው። የከተማዋ ሊስትሮዎች ሲጠርጉ የሚውሉት ረዥሙን የወታደር ከስክስ ጫማ ነው። ከተማዋ ከ10 ዓመት በኋላ እሁንም ቢኾን ከጦርነቱ መንፈስ የተላቀቀች አትመስልም።

በዛላንበሳ ትልቁ ሆቴል "ኢትዮጵያ ሆቴል" ይባላል። ጎራ አልኩኝ። ለዚህች ጦርነት ወኔዋን ለሰለባት ከተማ ትልቁ ሆቴል ይሁን እንጂ በምንም መመዘኛ ከሻይ ቤት ከፍ ያለ ግርማ ሞገስ እንኳ የለውም። ነጭ ጋውን የለበሱ ሙሉ ፀጉራቸው ከለበሱት ነጭ ጋውናቸው ጋር ፍጹም የሚስማማ አንድ አዋቂ ሰው ተጠጉኝ። "ታይ ክእዘዝ" አሉኝ። የሆቴሉ ባለቤት ናቸው። ተስተናጋጅ ስለሌለ አስተናጋጅ መቅጠር አላስፈለጋቸውም። ራሳቸው ታዘው፣ ራሳቸው ሠርተው፣ ራሳቸው ያመጡታል። አይተ ጣእመ ለምለም እንደሚባሉ ግድግዳ ላይ በስማቸው ከሰቀሉት የትግርኛ ጥቅስ ተረዳሁ። « "ሲመከሩት እምቢ ያለ መከራ ይመከረዋል" አይተ ጣእመ ለምለም» ትላለች ጥቅሷ። የራሳቸውን አባባል በራሳቸው ሆቴል ግድግዳ ላይ ከነሙሉ ስማቸው ለጥፈውታል።

ያዘዝኩትን ለመሥራት ተፍ ተፍ እያሉ ወሬ ማውራት ጀመሩ። እያወሩ መሥራት ይችላሉ። እየሰሩ ደግሞ ያወራሉ። የሚያወሩት ሰው የናፈቁም ይመስላሉ። በቤቱ ያለኔ ማንም እየተስተናገደ አልነበረም።

"አቦይ! እዚህ ያለምንም ዲሽ የኤርትራ ቲቪን ማየት ይቻላል የሚባለው እውነት ነው?" አልኳቸው። መልስ ሳይሰጡኝ እጃቸውን በፎጣ ጠራርገው የቲቪውን የርቀት መቆጣጠርያ ነኩት። የኤርትራ ቲቪ አንዳንድ የልማት ዜናዎችን በጭፈራ አጅቦ እያቀረበ ነበር። "ዙርያውን የምታየው እኮ ኤርትራ ነው፣ ከየት ነው የመጣኸው ? የመጣህበት ሚኒባስም የኤርትራን አስፋልት ረግጦ ነው'ኮ ያለፈው፤ ወደከተማዋ ለመግባት ሌላ አስፋልት ስለሌለ ነው መንገዱን የኛ ወታደሮች የሚቆጣጠሩት" አሉኝ።

ቆየት ብለው የቲቪውን ድምፅ አጠፉና ከጎኑ የተደቀነውን ሬዲዮ ነካኩት። የትግርኛ ዜማዎች መኾንኮንድ ጀመሩ። ለካንስ የኤርትራ ኤፍ ኤም ነበር። ከአሥመራ የሚተላለፈው "95.00 ኤፍ ኤም አሥመራ" ዛላንበሳ ካረፍኩበት «ኢትዮጵያ ሆቴል» ኩልል ባለ ድምፅ ይሰማል።

በሙሉ ለመመለስ ፍቃደኛ ሆነው የእነርሱን ኩብቶች እየነዱ መሄድ ችለዋል። አልጀርስ የማያስኬድ ድርድር፤ አብዱልአዚዝ ቡቶፍሊካ የማያውቁት ስምምነት፤ የመለስና ኢሳይያስ ፊርማ የማያስፈልገው ስምምነት፤ በየቀኑ በዛላንበሳ ድንበር ይካሄዳል።

ባሳለፍነው መስቀል ደግሞ እንዲህ ሆነ። በዚህች ደቡባዊ የኤርትራ ቀበሌ አቅራቢያ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊት ልጃቸው እና ጥቂት ቤተሰቦቻቸው ለመስቀል በዓል ሊጠይቋቸው ከአዲስ አበባ ይመጣሉ። አገር አማን ባሉበት ድንገት የኤርትራ ወታደሮች አምስት የቤተሰቦቻቸውን አባላት አፍነው ይወስዳሉ። እናት ከፉኛ በሐዘን ተዋጡ። ምንም ማድረግ አልተቻለም። በስንተኛው ቀን በኤርትራ ቲቪ ታዩ ተባለ። ‹‹ከኢትዮጵያ ጠፍተን መጥተን ነው…ተጨቁነን ነው ያመለጥነው...›› ወዘተ እያስባለ ያ መከረኛ የኤርትራ ቲቪ ያናዝዛቸዋል። ከዚህ ክስተት በኋላ ድንበሩ አካባቢ በፀጉረ ልውጦች ላይ ጠበቅ ያለ ክትትል ይካሄድ ጀምሮ ነበር።

## ኢትዮ - ኤርትራዊው የትራክተር ሾፌር

ይህ ታሪክ የተፈጸመው በ2000 ዓ.ም ነው። ጥቂት የውጭ ሚዲያዎችም ዘግበውታል። የኤርትራ መንግሥት አንድ ትራክተር ከነሾፌሩ ድንበር አካባቢ ያለውን ጋሻ መሬት እንዲያርስ ይልከዋል። ሾፌሩ  ወደ ኤርትራ ከመሰደዱ በፊት የአዲግራት ልጅ ነበር፤ ካቻማሊ የሚል ታርጋ የተለጠፈበት ኢትዮ-ኤርትራዊ። ኾኖም በሰላሙ ጊዜ በአዲግራት ቤተሰብ አፍርቷል።

ድንበር አካባቢ መሬቱን እያረሰ ሳለ ታድያ ኢትዮጵያዊ ቤተሰቦቹ ናፈቁት። በናፍቆት ሰከረ፤ ትራክተሯን ቀስ እያለ ወደ ፊት ነዳት፤ ድንበር የሚያርስ መስሎ ማርሽ ቀየረ። ትራክተሯን እያከነፈ ወደ ኢትዮጵያ መሬት ገባ። የኤርትራ ወታደሮች በተኩስ እሩምታ አጣደፉት። የትራክተሩን ግዙፍ ጎማ ጋሻ አድርጎ አመለጠ።  የኢትዮጵያን ምድር ረገጠ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ደግሞ የሽፋን ተኩስ ሰጡት። ከእጃቸው ያፈተለከው ኢትዮ-ኤርትራዊው ሾፌር የኤርትራ ድንበር ጠባቂዎችን ክፉኛ አስቆጣ። በዚህ የተነሳም ምንም እንኳ ሾፌሩ ኢትዮጵያ ቢገባም የተኩስ ልውውጡ ግን ሊበርድ አልቻለም። በመጨረሻ የዚህ ትራክተር ድራማ 37 የኤርትራ ወታደሮችና ሁለት የኢትዮጵያ ወታደሮችን ሕይወት እንዲጠፋ ምክንያት ሆነ።

## የአሥመራ ናፍቆት

የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም፤ ከአሥመራ በቀር። ይህችን ሕልም የመሰለች ከተማ ሳስብ ከፉኛ የእኔነት ስሜት ይወረኛል። ሁሌም እንደማውቃት እንጂ እንደማላውቃት ተሰምቶኝ አያውቅም። የእኔ እንጂ "የእነርሱ" ሆና አይሰማኝም። ደግሞም የእኔ ነበረች፤ የእኔም ትሆን ይሆናል፤ ማን ያውቃል? ሃምሳ ዓመት?…መቶ ዓመት?…ሁለት መቶ ዓመት? ምናልባትም ለዓለም ህዝቦች ድንበር የማያስፈልግበት ዘመን ይመጣ ይኾናል።

የ"አሮማዩ" ጸጋዬ "የባህር እንቁ" የሚላትን ከባህር ጠለል በላይ በ7500 ጫማ ከፍታ የምትገኘዋን አሥመራን አውቃታለሁ፤ የዘንባባ ጫካዎቿን፤ እንደ "ገዛ ባንዳ"፣ "ሰንበል ጉዳይፍ"፣ "ገጀራት ማይ ወላጮ"፣ "እዳጋ ሐሙስ"፣ "ማይ ተመናይ"… ያሉ ውብ ሰፈሮቿን በበዓሉ ግርማ ጽሑፍ አሳምሬ አውቃቸዋለሁ። ጸጋዬ አሥመራ ውስጥ ያልወሰደኝ ቡና ቤት አለ እንዴ? ሰካራም አድርጎኝ ነበረ'ኮ። ስለዚህ አሥመራን አታውቃትም አትበሉኝ። አሥመራ ልትናፍቅህ አትችልም አትበሉኝ።

አሁን እንሆ ድንበር ላይ ቆሜ ጠረኗን እየማግሁ ነው። ለካንስ ወደ ድንበር መሄድ ናፍቆት ያፋፍማል እንጂ አያስታግስም። ከድንበር አንጋጥቼ ያየሁሽ  ሰሜናዊ ፅብቅቲ አሥመሪና!

ዛላንበሳ ጠረፍ ላይ ሆኜ የበዓሉ ፍቅር የነበረቸው- ፊያሜታ ስትስቅብኝ የተሰማኝ መሰለኝ። "አባቴ ይሙት ደደብ ነህ!" እያለች።

*From the Library of*

**ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ**

**FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES**

# ከመጻሕፉ የተወሰዱ

ስብሐት "ትኩሳት" ብሎ በጠራው መጽሐፉ ጀርባ ምን አለ? "ወጣት ሁን" አለ፡፡ ቢመርህ "ሪቮሉሽን" ታስነሳለህ፣ እጅግ ቢመርህ ራስህን ታጠፋለህ...፡፡ ለማንኛውም ወጣት ሁን፡፡ እኔ ግን እልሻለሁ፣ ወጣት መሆኑን ሁን፣ ነገር ግን ራስህን ከማጥፋትህ በፊት ፒያሳ ሂድ፤ ሐሳብህን ልትቀይር ትችላለህ፡፡ ለመሞትም ቢሆን የፒያሳን ያህል መልካም ሰፈር የለም፡፡ ቀባሪ አታጣም፤ በፒያሳ ሰው ባያይህ ማዘጋጃ ያይሻል፡፡

— —

በአዲስ ነገር ቤት ሌላው የጦርነት ግንባር ይከፈት የነበረው ዘወትር እሁድ/አንዳንድ ጊዜም ሰኞ/ ይካሄድ በነበረው የኢዲቶሪያል ስብሰባ ላይ ነበር፡፡...የአዲስ ነገር ባልደረቦችን በዚህ ስብሰባ ውስጥ ማየት የምር ያስጨንቃል፡፡ ከዚህ የኤዲቶሪያል ስብሰባ መጠናቀቅ በኋላ እንዲያ የተነታረኩ ባልደረቦች በሰላም ማኪያቶ ሲጠጡ ማየት ደግሞ ፈገግ ያሰኛል፡፡ ተመሳሳይ ፓርላማ ለሀገሬ መመኘት ይፈቀድልኝ ይሆን?

—

ኢቴቪ በሰፈሬ ስራ አጥ ወጣቶች ዘንድ «ቁጨ» በመባል ይታወቃል፡፡ «ቁጨ» ማለት በግልፅ የሚታይን ነገር ድርቅ ብሎ መካድ፣ማበል፣ ማስተባበል ማለት ሲሆን ቃሉ ይበልጥ በቁማር ጫወታ ላይ ይዘወተራል፡፡

— —

በአጻጻፍ ይትበሃሉ መሐመድ ተራ ዘጋቢ፣ የጉዞ ጸሐፊ፣ ታዛቢ ሆኖ ይታያል፤ አንዱን ብቻ ግን ሆኖ አያውቅም። ይበልጡንም ደግሞ መሐመድ የሚጽፋቸውን ነገሮች በአካል አይቶ ብቻ ሳይሆን ሞክሮ/ኖሮ ጭምር የሚጽፍ በመሆኑ ተአማኒነቱን ከጥርጥር በላይ ያደርገዋል። "ይህማ ሊሆን አይችልም" እንዳንለው የሚጽፈው እዚያው ሆኖ ነው፣ እየኖረ፡፡

**መስፍን ነጋሽ**

/የቀድሞው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር/

29.00 ብር

ዋጋ፡- ሃያ ዘጠኝ ብር (29.00 ብር)

የገፅ እና ሽፋን ዲዛይን - ባሴ
አድራሻ፡-ስልክ፡ 0911-93-00-51
ኢ-ሜይል፡- basse444@gmail.com

**Etafzer p.p.plc**

አከፋፋይ፡- ሊትማንጀኔራል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
አድራሻ፡-አራት ኪሎ ቅ/ስላሴ አዲሱ ህንፃ
ስልክ 0911-89-94-68 ፡ 0111242566

ዋጋ፡- ሃያ ዘጠኝ ብር (29.00 ብር)